
# አራተኛው አስደናቂ ታሪኮች



NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ከጳውሎስ ኞኞ

# ማውጫ

ትርፍ አካል ያላቸው ሰዎች ........................................ 4
ነፍስ ትመጣለች? ........................................ 19
ቀን ይጨልማል? ........................................ 32
ሜሲ እና ክርስቲና ........................................ 39
አሣነባሪ ........................................ 48
ውሻ ........................................ 56
ስለደራሲው በጥቂቱ ........................................ 98

የተላከ ከጳውሎስ ኞኞ

ይድረስ ከመጽሐፌ አንባቢዎች፤

እንዴት ከረማችሁ?

ደኅና መሆናችን ደኅና ነገር ነው።

ይሄን አራተኛውን የአስደናቂ ታሪኮች መጽሐፍቶቼን ተከታይ አቀረብኩላችሁ ባለፉት በሦስቱ አስደናቂ ታሪክ መጽሐፍቶች መቅድም ውስጥ ብዙውን ነገር ተናግሬ ስለጨረስኩት አሁን በዚህኛው መጽሐፌ የምጽፍላችሁ ብዙ የመግቢያ ንግግር የለኝም በዚሁ በቃኝ።

የማትረሱት ነገር አሁንም ቢሆን በዚህ መጽሐፌ ውስጥ ያለውን ዘመን አቆጣጠር እንደሌላዎቹ መጽሐፍቶቼ ሁሉ በዚህም የተጻፈው ዘመን በሙሉ እንደ ኤሮፓ ዘመን አቆጣጠር ነው፤ ለምን እንደማደርግም ከዚህ በፊት በወጡት መስሐፍቶቼ ገልጫለሁ።

እግዚአብሔር ተርፎ ከሚቀር ዕድሜ ካልነፈገን በአምሰኛው የዚህ ተከታይ መጽሐፍ እስትንገናኝ እስከዚያው ደህና ሁኑ።

# ትርፍ አካል ያላቸው ሰዎች

ትርፍ አካል ያላቸው ሰዎች እንዴት እንደሚፈጠሩ በ3ኛው አስደናቂ ታሪኮች መጽሐፌ መቅድም ውስጥ ባጭሩም ቢሆን ስለገለጽሁ አሁን በዚህ ቦታ ለምንና እንዴት እንደሆነ አልገልጽም። በዚያው መስሐፍ መቅድም ውስጥ ትርፍ አካል ካላቸው ሰዎች በሐል የጥቂቶቹን አሁን አነብቦታለሁ።

ትርፍ አካል ሰዎች መሐል አንዱ ላዛሩስ ጆኔስ ባፕቲስታ ኮሎራዶ ነው፤ ይህ ነው፤ ይህ በ1617 ዓ.ም በስዊዘርላንድ ውስጥ በጄኔቫ ተወለደ። ኮሎራዶ በመላው ኤሮፓ እየተዘዋወረ ለሕዝብ ታይቷል፤ በታላላቅ ሳይንቲስቶችም ተመርምርዋል።

ኮሎራዶ በደረቱ ላይ ከጡቱ አጠገብ መንትያ ወንድሙ የበቀለበት ወይም የተጣበቀበት ሰው ነው። ይህ ሰው እንደ ተወለደ ክርስትና ሊነሳ ቤተ ክርስቲያን ሲወሰድ ቄሱ «ሁለቱም ፍጡር ናቸውና ሁለቱም መጠበቅ አለባቸው» ስላሉ ደረቱ ላይ የበቀለው ፍጡና ደንበኛው ፍጡር አብረው ተጠመቁ፤ ትልቁ ሰው ላዛሩስ ተብሎ ሲሰየም በደረቱ ላይ የተጣበቀው ግማሽ ሰው ደግሞ ጆኔስ ባፕቲስታ (ዮሐንስ መጥምቁ) ተብሎ ተሰየመ።

የአካል አፈጣጠር ሊቅ የሆኑት ባርቶሊኑስ ስለዚህ ሰው በጻፉት ጽሑፋቸው «……ሙሉ አካል የሌለው ትንሽየው ወንድሙ አንድ እግር ብቻ አለው፤ ይሄም ሙሉ ቅልጥምና ጫማው (መርገጫው) ነው፤ ይህ እግር ቁልቁል ተንጠልጥሏል፤ ሁለት እጆችም አሉት፤ ግን በእያንዳንዳቸው እጁ ላይ ያሉት ጣቶች 3 ሦስት ናቸው፤ ይህ ቅጥያ ፍጡር አፍና ጆሮም አለው፤ ግን ምንም ዓይነት ምግብ አይመገብበትም፤ ምግብ የሚያገኘው ትልቅ ወንድሙ ላዛርሱ ከሚባለው ምግብ ነው።

«….ይህ ትንሽ ወንድም በሚተኛበት ጊዜ ከአፉ ለሀጭ ይወጣል፤ የዚ ተጣባቂ ወይም ትንሽ ወንድም ርስ ትክክለኛ የሰው ራስ ሆኖ በጠጉር የተሸፈነ ነው፤ ዓይኑ ግን ዝግ ነው፤ ትንፋሹም ደካማ ነው፤ የዶሮ ላባ ወደ አፉና አፍንጫው ዘንድ ሳስጠጋለት መጠነኛ እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፤ አፉ እየተከፈተ ይገጥማል፤ ምንም ጥርስ የለውም…..» ብለዋል።

ላዛሩስ ሙሉ ሰው ያልሆነ ወንድሙ በላዩ ላይ ከመጣበቁ እብስተቀር ፍፁም ጤነኛ ሰው ነው፤ ሚስት አግብቶም ብዙ ልጆች አስወልዷል፤ ላዛሩስ ከቤት ውጪ በሚሄድበት ጊዜ ትንሽ ተጣባቂ ወንድሙን በካባ ሸፍኖት ይሄዳል።

ሌላው ባለ ትርፍ አካል በ1783 ዓ.ም በቤንጋል የተወለደው ልጅ ነበር። ይህ ልጅ ትርፍ ራስ ነበረው፤ በሮያል ፊሎዞፊካል ሶሳይቲ አባል የሆኑት ስር ኢቨራርድ ሆም በ1791 ዓ.ም ስለዚያ ልጅ በጻፉት ሪፖርት «የልጁ አካላ በትክክለኛ አፈጣጠር የተፈጠረ ነው፤ ራሱ ግን ሁለት ነው፤ አንደኛው ራስ በአንደኛው ራስ ላይ የተደረበ ነው......»

«ልጁ የስድስት ወር ዕድሜ ሲሆነው ራሶቹ በሙሉ በጥቁር ጠጉር ተሸፈኑ......ይዚህ ልጅ ወላጆች ድሆች ስለነበሩ ልጁን ይዘው በካልካታ (ሕንድ) ከተማ መንገድ ላይ እየተዘዋወሩ ምፅዋት ይለምኑ ነበር፤.....»

«በሁለቱም ራሶች ላይ ያሉት ዓይኖቹ የሚዘዋወሩት እኩል ነው፤ እንባ የሚወጣው ከላይኛው ራሱ ዓይኖች ብቻ ነው፤ ከታችኛው ራስ ዓይኖቹ ግን ፈጽሞ እንባ አይወጣም፤......ዕድሜው ከሁለት ዓመት ጥቂት በለጥ እንዳለ እናቲቱ ልጅዋን ትታ ውሃ ፍለጋ ሔዳ ስትመለስ ልጁን ኮብራ የሚባለው መርዘኛ እባብ ነክሶ ሞቶ አገኘችው......» በማለት ዝርዝር ሁኔታውን ጽፈዋል።

ሌላዋ ባለ ትርፍ ገላ ወይዘሮ ሉዚ ናት፤ ሉሲ ባለ አራት እግርዋ ወይዘሮ እየተባለችም ትጠራ ነበር። ሉሲ የተወለደችው በፈረንሣይ አገር በ1869 ዓ.ም ነው፤ የሉሲ ትርፍ 2 እግሮች የተፈጠሩት በሌሎቹ ደንበኛ እግሮች መሐል ነው እነዚህ ትርፍ ሁለት እግሮች ከደንበኛዎቹ ያጠሩ ናቸው፤ ሉሲ በሁለት ትርፍ እግሮችዋ አትሔድባቸውም ግን እግሮችዋን ሲነኳት የት ቦታ እንደተነካች ትናገራለች፤ ሉሲ እነዚሁኑ አራት እግሮችዋን ይዛ ሁለት ጤናማና ሙሉ አካል ያላቸው ልጆች ወልዳለች።

ሌላው በአሮፓና በአሜሪካ እየተዘዋወረ ለሕዝብ ሲታይ የነበረው ላሉ ነው፤ ይህ ከእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የተወለደው ላሉ በ1874 ዓ.ም በሕንድ አገር ኡድ በተባለ ቦታ ተወለደ፤ ላሉ ከደረቱ ታችኛ ክፍል ላይ

የተጣበቀ መንትያ ነበረው፤ ላሉ ለወላጆቹ ከአራት ልጆች ሁለተኛው ሲሆን ሌላዎቹ ልጆች በሙሉ ጤነኞች ነበሩ፤ ላሉ በ1894 ዓ.ም በፊላደልፊያ ውስጥ ሚስት አገባ፤ ለትርኢት በሚዞርበት ቦታ ሁሉ ከሚስቱ ጋር አብረው ይዞሩ ጀመር።

ላሉ ላይ የተጣበቀው መንትያ ከላሉ ደረት ላይ በራሱ በኩል ነው፤ ይህ ተጣባቂ ግማሽ ሰው ሁለት እጆችና እግሮች አሉት፤ በነዚህ አካሎች ላይ የጎላ ደም መዘዋወር አይታይም፤ ግን አካሉ ከአንድ ቦታ ሲነካ የመነካቱን ስሜት ላሉ ይናገራል፤ ምክንያቱም ከላሉ አካል ጋር የተያያዘ የደምና የነርቭ መገናኛ አላቸውና ነው።

ይህ በላሉ ላይ የተጣበቀ መንትያ ደህና የሆነ የሽንት መሽኚያ (የወንድ ብልት) አለው፤ ጠጉሩም እንደማንኛውም ሰው ጠጉር ነው፤ ይህ የተጣበቀ ግማሽ ሰው ራሱን ችሎ በራሱ ትእዛዝ ሽንቱን መሽናት ይችላል፤ ቢሆንም ላሉ ይቆጣጠረዋል፤ እንዲህ ያሉ መንትዮች አብዛኛውን ጊዜ የሚፈጠሩት በተመሳሳይ ጾታ ነው፤ የላሉ አለቃ ወይም በየአገሩ እያዞረ ገንዘብ በማስከፈል ለሕዝብ ያሳየው የነበረው ሰው ተመልካችን ለመሳብ ተጣባቂውን የሴት ቀሚስ ያለብስ ነበር።

ሌላዋ ትርፍ ገላ የነበራት ቤቲ ሉ ዊልያምስ ናት፤ ግቤቲ ቆንጅዬ የሆነች ባለ ጥቁር ቆዳ ናት፤ በመልከዋና በጨዋታዋም በብዙዎች ዘንድ የተወደደች ነበረች፤ ከቤቲ በስተግራ ጎንዋ የበቀለችው ሙሉ አካል የሌላት መንትያዋ ሴት ናት ይቺ መንትያ ሁለት እግሮችና አንድ ያልተሟላ እጅ አላት፤ የመንትያዋ እጅ የበቀለውም ከመንትያዋ ቂጥ ገደማ ነው።

ይህች ውብ የነበረች ሴት ምግብ በምትበላት ጊዜ ለአንድ ሰው ከሚገባው በላይ ትበላለች፤ ይህም የተጣባቂዋን ጭምር እንደሆነ ሊቃውንት ተናግረዋል ምክንያቱም ተጣባቂዋ በዚያው፤ ባለችበት ሁኔታ ታድጋለችና ነው፤

ቤቲ በአስም በሽታ ምክንያት በ1955 ዓ.ም ሞተች፤ ቤቲ ለሕዝብ እየታየች በሳምንት ሁለት ሺህ የኢትዮጵያ ብር ገደማ ታገኝ ነበር፤ በምታገኘውም ገንዘብ አንድ ታላቅ የእርሻ ቦታ ገዝታ አባትዋን፤ ወንድሞቿንና እህቶቿን በአንድነት በዚያ አኑራቸው ነበር።

እንደ ቤቲ ዓይነት በጎ በኩል ግማሽ አካል ያህል ያለው መንትያው የተጣበቀበት ጂን ሊቤራ ነው፤ ጂን ሊበራን እያዞረ ለሕዝብ ያሳየው የነበረው ሰ ወይም በዚህ ተግባር ዝነኛ የነበረው ተጣባቂውን ጃኩስ ብሎ ሰይሞት ነበር። በዚህም ምክንያት አንዳንድ ጸሐፊዎች ጂን ሊቤራን ሲጠሩ ጃኩስ እያሉ ቅጥልያውን ስም እየጨመሩ ነው።

ጂን ሊቤራ በ1884 ዓ.ም በኢጣሊያ አገር በሮማ ከተማ ተወለደ ጂን ሊቤራ ወላጆቹ ከወለዱዋቸው አሥራ ሦስት ልጆች መሐል አራተኛው ልጅ ነበር፤ ባርኑም ለተጣባዊቅ ባወጣለት ስም ልሂደውና ጃኩስ ቂጥ ጭን፤ እጆችና እግሮች አሉት፤ የእጁም ሆነ የእግሩ ጣቶች ከነጥፍሮቻቸው የተሟሉ ነበሩ፤ ከወንድሙ ከጂን በሚያገናኘው ምግብም ጠንካራ አጥንት ያለው ነበር፤ ጃኩስና ጂን በስሮችም (ነርቭ) የተገናኙ በመሆናቸው ጃኩስ ሲነካ የት እንደተነካ ጂን ይናገራል።

ጂን በጎኑ ላይ ጃኩስ ተጣብቆ ከመንዘላዘሉ በስተቀር ፍፁም ሙሉና ጤነኛ ሰው ነበር። ሚስት አግብቶም የአራት ልጆች አባት ሆንዋል።

እዚህ ላይ አንድ የማስታውሳችሁ ነገር አለ። በሦስተኛው መጽሐፌ መቅድም ላይ እንደገለጽኩት እንዲህ ዓይነቱ አወላለድ በማየትም ሆነ በመስማት ሊመጣ ያለ መቻሉን ነው። ለጂን ላይ የተጣበቀውን መንትያ ሁልጊዜ ታየዋለች፤ ገላውን ስታጥብም ታገላብጠዋለች። በጂን ላይ የተጣበቀ ትርፍ አካል መኖሩን በሚገባ ታውቃለች ታያለችም። ግን የወለደቻቸው ልጆች በሙሉ አካል ያላቸው ጤነኞች ነበሩ። ይህ እንግዲህ በአገራችን ሲነዛ የነበረውን አጉል ልማድና አምልኮ ያጠፋልናል፤ ሌሎችንም ብዙ ማስረጃዎች ከዚህ መጽሐፌ ዘሮች ውስጥ ያገኛሉ። ይህን ከነገርኩ በኋላ ወደ ፍራንክ ሌንቲኒ ታሪክ ልውሰድዎት።

ሌላው ባለ ትርፍ ገላ ፍራንክ ሌንቲን ነው የፍራንክ ደግሞ ትንሽ ለየት ያለ ነው፤ ፍራንክ ሌንቲኒ ባለ ሦስት እግሮች ጌታ ነበር። የፍራንክ ሌንቲኒን ታሪክ ሳይሆን ፎቶ ግራፍ በአንደኛው የዚህ መጽሐፌ ዘር አውጥቼዋለሁ፤ የዚያን ጊዜ ከመግለጫው በስተቀር ዝርዝር ታሪኩን አላገኘህም ነበርና ነው።

ፍራንክ ሌንቲኒ ሦት እግሮች ይኑሩት እንጂ በሦስተኛው እግሩ አይሄድበትም ነበር። ምክንያቱም ከሁለቱ እግሮቹ ጋር የማይስተካከል አጠር

ያለ ነበርና ነው። ሐሪ ሌዊስተን እንደፃፈው «ሦስተኛ እግሩን እንደ በርጩማ በማድረግ ይጠቀምበታል፤ በዕድሜዬ ካየኋቸው ሰዎች ሁሉ በፈለገበት ቦታ ወንበር ሳያስፈልገው መቀመጥ እይሚችል ሰው እሱ ብቻ ነበር፤ 3ኛ እግሩ በመጠኑ አጠር ያ በመሆኑ የሚራመድባቸውን ሁለት እግሮች ለማሳረፍ ሲፈልግ በ3ኛው እግሩ ይቆማል፤ 3ኛው እግሩ ወንበር ሲሆንለትም ሁለቱ እግሮቹ ተዝናንተው የማረፊያ ጊዜ ያገኛሉ፤ ይህን 3ኛ እግሩን የሚጠቀምበት ለመቀመጫነት ብቻ ሳይሆን ኳስም ይመታበታል.....» ብሏል።

ፍራንክ ሌንቲኒ በኢጣሊያ አገር ሲሲሊ ውስጥ በምትገኝ ሮሶሊኒ በተባለች አምባ በ1889 ዓ.ም ተወለደ ወላጆቹ ከወለዷቸው አሥራ ሁለት መሐል አንደኛው ነው፤ አሥራ አንዱ ልጆች ሙሉ አካል ያላቸው ሲሆኑ ፍራንክ ሌንቲኒ ብቻ ባለ ሦስት እግሮች ጌታ ነው፤ እናቲቱ ይሔን ልጅዋን በምታሳድግበት ጊሌ እያየቸውም ሆነ ስለሱ እያሰበች ሌላ ባለ 3 እግር ወይም አካለ ጎደሎ አልወደችም።

የፍራንክ ሌንቲኒ 3ኛ እግር የበቀለው ከብልቱ አጠገብ ነው፤ እንደማንኛዎችም እግሮቹ ሁሉ ከዳሌው አጥንት ጋር የተገናኘ ነው፤ ይህ 3ኛ እግር ለብቻው ይጠር እንጂ ሌላዎቹ ሁለት እግሮችም ትክክል አልነበሩም፤ አንደኛው እግሩ ከአንደኛው እግሩ በአንድ ኢንች ያጥራል፤ 3ኛው እግር ደግሞ ከረጅሙ እግር 3 ኢንች ያጥራል።

የፍራንክ ወላጆች ፍራንክን እንደ ወለዱ በሕፃንነቱ ዘመን ይዘውት ወደ አሜሪካ አገር ሄዱ፤ ወላጆቹ 3ኛ እግሩ በኦፕሬሽን እንዲለያይላቸው ፈልገው ነበር፤ ሐኪሞች ባደረጉት ጥናት ይህ እግር ከአካሉ ጋር ግንኙነት ስላለው ልጁ ኦፕሬሽን ተደርጎ እግሩ ቢወጣለት አደጋው ለሞት ያደርሰዋል፤ ባይባልም ሽባ (ፓራላይዝ) ይሆናል ስላሉ በኦፕራሲዮን የእግሩ መውጣት ጉዳይ ቀረ።

ፍራንክ ሌንቲኒ አደገና ከልጆች ጋር ለመጫወት ይወጣ ጀመር፤ ልጆቹ ይሄ ትርምስምስ እግሩ እያሉ ይሸሹና ይስቁም ጀመር፤ ፍራንክ ያለው ዕድል ከዳር ሆኖ የልጆቹን አጨዋወት ማየት ብቻ ሆነ፤ በዚህም ምክንያት ብስጭቱ እየበዛ ሔደ፤ ከሕዝብ ተለይቶ መኖርን ወይም ሞትን ይመርጥ ጀመር፤

ወላጆቹ ግን ብስጭቱን እንዲተውና ዓለም ተለዋዋጭ መሆኑን ይነግሩታል፤ ያጽናኑታል፤ አንድ ቀን ታላቅ ሰው እንደሚሆንም ይነግሩታል።

አንድ ቀን ወላጆቹ ፍራንክን ይዘው አከለ ጎደሎ ልጆች ከሚያድጉበት ኢኒስቲቲውት ወሰዱት በዚያም በያይነቱ ችግር ያሉባቸው ልጆች አሉ። በዚያም ውስጥ ያሉ ሴቶችና ወንዶች ልጆች በምን ዓይነት ጨለማ ኑሮ እንደሚኖሩ ፍራንክ አሰበ ደንቆሮዎች ዲዳዎች፤ እጅ የሌላቸው እግር የሌላቸው ልጆች ሁሉ በዚያ ተሰብስበው ባየ ጊዜ ፍራንክ «የኔ የተሻለ ነው፤ አያለሁ፤ እሄዳለሁ እጨብጣለሁ፤ እስማለሁ፤ እናገራለሁ ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ አልበሳጭም» አለ። አድጎ ሀብታም ከሆነም በኋላ ሲናገር «……እነኛን ልጆች ካየሁ ወዲህ ብስጭቴን ተውኩ፤ የኔ ኑሮ ምን ያህል አስደሳች እንደሆነም እስካሁን ድረስ እየገመትሁ እደስታለሁ……» ብሏል።

ከዚያ በኋላ ፍራንክ 3ኛ እግሩን በወዳጅነት ተቀበለው፤ ያሠራውም ጀመር። «ምን ጎደለብኝ እሔዳለሁ፤ እዘላለሁ፤ ብስክሌት እነዳለሁ፤ ፈረስ እጋልባለሁ፤ በበረዶ ላይ ሸርተቴ እጫወታለሁ፤ የግል አውቶሞቢሌንም እነዳለሁ፤ በውሃ ውስጥ እዋኛለሁ፤ እንዲያውም በውሃ ዋና ከሌሎች ሰዎች የተሻልኩ ነኝ፤ ምክንያቱም ተጨማሪውን እግሬን በሥራ ላይ አውለዋለሁና ነው……» በማለት ይናገራል።

«ለመሆኑ ጫማ ስትገዛ እንዴት ነው?» ብለው ሰዎች ጠየቁት፤ «እንዲህ ነው» አላቸው «ሁለት ጥንድ ጫማ ይተርፈኛል፤ አንድ ወዳጄ አለ፤ ያ ወዳጄ በአጋጣሚ ምክንያት የቀኝ እግሩን ስለ ተቆረጠ የተረፈውና የሚሔድበት የግራ እግሩ ብቻ ነው፤ ስለዚህ ያን የሚተርፈኝን የግራ እግር ጫማዬን ለዚያ ወዳጄ እሰጠዋለሁ፤ ሁለት ጥንድ ጫማዎች እገዛለሁ፤ አደርጋለሁ፤ በጎ አድራጎትም እሠራበታለሁ» ብሎ መልሷል።

ሌላው እየተደጋገመ የሚቀርብለት ጥያቄ «ስትተኛ ይሄ 3ኛው እግርህ ያስቸግርሃል ወይ?» የሚለው ነበር። «አያስቸግረኝም በጎኔም ብተኛ በጀርባዬም ብተኛ ምንም አያስቸግረኝም» በማለት ይመልሳል።

ፍራንክ ሌንቲኒ ሚስት አግብቶ የአራት ወንድ ልጆችና የአንዲት ሴት ልጅ አባት ለመሆን በቅቷል። ያን ትርምስምስ እግር የምታውቀውና

የሚተረማመስባት ሚስቱ ከወለደቻቸው ልጆች አንድም አካለ ጎደሎ ወይም ትርፍ ገላ ያላቸው ልጆች አልወለደችም ሁሉም ባለ ሙሉ አካል ነበሩ።

ፍራንክ ሌንቲኒ በአሜሪካ አገር በወተርስ ፊድል ባለው መኖሪያ ቤቱ ከቤተሰቡ ጋር ሲኖር በ77 ዓመት ዕድሜው በ1966 ዓ.ም ሞተ።

ባለ ሦስት እግሩ ፍራንክ ሌንቲኒ አስደናቂ ፍጡር ቢሆንም ከእሱ በተሻለ ሁኔታ የተፈጠረችው ወይዘሮ ማርትሌ ኮርቢን ደግሞ አራት እግሮች ነበሩዋት። ወይዘሮ ማርትሌ በብዙ ሥፍራዎች እየተዘዋወረች ለሕዝብ ታይታለች፤ ወይዘሮ ማርትሌ የምታወቅበት ቅጥል መጠሪያዋ «ባለ አራት እግሯ የቴክሳስዋ ወይዘሮ» የሚል ነበር በፎቶ ግራፍ ላይ ተቀምጣ የምትታየው ወይዘሮ ማርትሌ ሁለት እግሮችዋ መረኢት ሲነኩ ሁለቱ ከመሐል ተንጠልጥለው ይታያሉ። እነሱም የልጅ እግር ይመስላሉ፤ ወይዘሮ ማርትሌ ደንበኛ እግሮችዋን በረጅም ሹራብ (ካልሲ) ሸፍና ጫማ ብታደርግም፤ አጫጭር ሁለት እግሮችዋንም በረጅም ሹራብ (ካልሲ) አልብሳ ጫማ ታደርግባቸዋለች።

የወይዘሮ ማትሌ ሁለት ትርፍ እግሮች የበቀሉት ከጭኖችዋ መሐል ነው፤ በዚህም ምክንያት ሁለት የግብረ ሥጋ መገናኛ ወይም መሽኚያ ብልት ነበራት። ባል አግብታም አምስት ጤናማ ልጆች ወልዳለች። እነዚህ ልጆች የተወለዱት ሦስቱ በአንደኛው ብልቷ ሲሆን ሁለቱ ደግሞ በሌላው ብልቷ ነው።

በእንግሊዝ አገር በኬንት ውስጥ ቢደንደን በተባለ ቦታ ሁለት የተጣበቁ ሴቶች ተወልደው ነበር። እነዚህም ሴቶች የቢደንደን ወይዘሮዎች በመባል የታወቁ ናቸው። የተወለዱት በ1100 ዓ.ም ነው፤ በጥንት ዘመን ሰዓሊዎች እነዚህን የተጣበቁ ወይዘሮዎች በሳሉዋቸው መሠረት የተጣበቁት እንደ ቻንግና ኢንግ (ታሪካቸው በ3ኛው መጽሐፌ ውስት አለ) ነው። እነዚህ የተጣበቁ ሴቶች አንደኛዋ ኢሊዛ ስትባል ሌላዋ ደግሞ ሜሪ ቹልከርስት ተብላለች። እነዚህ ልጆች የተወልዱት ከጤናማ ወላጆች ነው።

በ1134 ዓ.ም አንደኛዋ ተጣባቂ ሞተች በዘመኑ የነበሩ ሐኪሞች ማችቷን ገንጥለው በማውጣት ያልሞተችዋን በሕይወት ለማኖር ወሰኑ፤ ያልሞተችዋ ግን «.....አይሆንም አብረን አንደ መጣን አብረን እንሄዳለን፤

.......» ብላ መለያየቱን ተቃወመች ከስድስት ሰዓት በኋላም እህቷን ተከተለች፤ ሞተች።

እነዚህ የተጣበቁ መንትዮች ግማሽ ጋሻ መሬት ነበራቸው በሚሞቱበት ጊዜ ይህ መሬታቸው እንዲከራይና በየዓመቱ በሚገኘው በኪራዩ ገንዘብ በያመቱ የፋሲካ ዕለት ጥቢኛ (ዳቦ) እየተዘጋጀ እንዲታደልላቸው ተናዘዙ፤ ይህም ኑዛዜያቸው የጸና ሆኖ እስከ ዛሬ ድረስ በቢደንደን ቤተ ክርስቲያን ይሠራበታል። ይህም ኑዛዜ ሳያቋርጥ ሲሠራ 850 ዓመት ሊሆነው ነው።

ሌላዎቹ ተጣባቂዎች ራዲካና ዶዲካ ናቸው። እነዚህ ተጣባቂዎች በኤሮፓ በኤግዚቢሽን ለሕዝብ መታየት የጀመቱ በ1890 ዓ.ም ነው፤ እነዚህ ልጆች የተጣበቁት በሆዳቸው ነው፤ የተጣበቁበትም ሥፍራ አሥር ሳንቲም ሜትር ያህል ነው፤ ሁለቱም፤ ሴቶች ናቸው፤ እነዚህ ልጆች በ1888 ዓ.ም በሕንድ ውስጥ አሪሳ በሚባል ቦታ ተወለዱ፤ እንደ ተወለዱ ያገሩ ሰዎች ወላጆቻቸው በእርኩስ መንፈስ የእለከፉ ናቸው በማለት አሠሩዋቸው። በ1892 ዓ.ም ልጆቹ በፈረንሣይ አገር ካፒቴን ኮልማን የተባለ እንዲህ ያሉ ፍጥረቶችን ለሕዝብ ገንዘብ እያስከፈለ የሚያሳይ ሰው ይዞአቸው ተገኙ።

ራዲካም ሆነች ዶዲካ ጨዋዎች ነበሩ፤ በሚተኙበት ጊዜ አንደኛዋ በጀርባዋ ስትተኛ ሌላዋ ደግሞ በጎንዋ መተኛት ነበረባት አንደኛዋ ምግብ ስትመገብ ሌላዋ ያልበላቸው ትጠግብ ነበር። ለአንደኛዋ መድኃኒት ሲሰጥ ሌላዋ መድኃኒት ያልተሰጣት መድኃኒቱ ይደርሳታል፤ በጤንነትና በጥሩ ሁኔታ አደጉ።

ዶዲካ ታመመች፤ ሐኪሞች ሕመምዋን ሲመረምሩ የሳምባ በሽታ ሆኖ አገኙት፤ ዶዲካ ከዚህ ከለከፋት በሽታ ስለማትችል ሐኪሞች በኦፕራሲዮን ለያዩዋቸውና ዶዲካ ሞተች፤ ራዲካ ድና ሁለት ዓመት ለብቻዋ ከኖረች በኋላ በዚያው እህቷን በገደለው የሳምባ በሽታ ተለክፋ ሞተች።

የተጣባቂዎች ጉዳይ ከተነሣ አንዴ ልጨርሳቸውና ሌላዎቹ ዝነኛዎቹ ተጣባቂዎች ደግሞ ሮዛና ጆሴፍ ብላዜክ ናቸው፤ እነዚህ ልጆች በ1878 ዓ.ም ጥር 20 ቀን በቼኮዝሎቫኪያ፤ በቦሄሚያ ውስጥ እስክሬይጆቫ በተባለ ቦታ ተወለዱ። እነዚህ ልጆች የተጣበቁት በቂጣቸው በኩል በመሆኑ ለሁለት

ያላቸው ቂጥ ወይም መቀመጫ አንድ ብቻ ነው፤ ግን ለየብቻው የሰገራ መውጫና የሽንት መሸኚያ ብልት አላቸው።

እናቲቱ በሃያ ሁለት ዓመት ዕድሜዋ እነዚህን ልጆች ስትወልድ ያለ ምንም ችግር በሰላም ወለደቻቸው፤ ልጆቹም ከፍ ሲሉ አካሔዳቸውን ማስተካከል አጥንተው ደረጃ እስከ መውጣትና መውረድ እስከ መቻል ደረሱ።

በ1891 ዓ.ም በፓሪስና በለንደን ከተሞች በኤግዚቢሽን ውስጥ ለሕዝብ መታየት ጀመሩ፤ ጆሴፋ ጭምትና በአድራጎትዋ ሁሉ ዝግተኛ ነበረች፤ ሮዛ ግን በቀላሉ መለፍለፍ የምትችል ጠንካራና ሁለገብ ነበረች። የአንድ ሰርከስ ኃላፊ የነበሩት ሲኞር ሳልታሪኖ ስለ እነዚህ ልጆች በጻፉት አስተያየት «……ደስ የሚሉና የሚያሳዝኑም ናቸው፤……አንደኛዋ ጋር በምትጣላበት ጊዜ «እንዲህ ካላደረግሽ እለይሻለሁ» ታላታለች……» ብለዋል። የእነዚህ ልጆች የደም መዘዋወር ግንኙነት እንዳለው ሐኪሞች ተናግረዋል፤ ለአንደኛይቱ የሚሰጥ መድኃኒት ሌላዋንም ይነካታልና ነው።

ወደ ሲኞር ሳልታሪኖ አስተያየት ልመልሶትና ሲኞር ሳልታሪኖ በጻፉት አስተያየት «.......በ1890 ዓ.ም እነዚህ ኮረዳዎች ቂንቂን አሉና ባል ማግባት ያስፈልገናል አሉ፤ በሰርከስ ውስጥ እየታዩ ገንዘብ አጠራቅመው ነበርና ለሁለት አንድ ወንድ ወደው አገቡ ሰውየው ሁለቱንም በአንድነት በሚስትነት ያገባው ለገንዘባቸው ብሎ ነው፤.......ብዙ ጥቅም አለው፤ በሴቶቹ የሚገኘው ገቢ ገንዘብ ሳይከፋፈል ያዝበታል፤ ሁለት ምሲቶችም ስላሉት ከሌላው ወንድ የተለየ ነው፤ ሁለት ሚስቶች የሚያገቡ ወንዶች ቢኖሩም እንደ እነኛ ሁለት አማቶች የሉትም……» ብለዋል። በ1910 ዓ.ም ሚያዝያ ወር ዕድሜያቸው ሃያ ሁለት ዓመት ሲሆን በፕራግ ከተማ ውስጥ ሮዛ ወንድ ልጅ ወለደች፤ አልፈውት በመጡት ገጽ ባለው ፎቶ ግራፋቸው ላይ ሮዛ የወለደችው ልጅ አብሮአቸው ቆሞ ይታያል።

በ1922 ዓ.ም ወደ አሜሪካ ሔዱ፤ በቺካጎ እንዳሉ የመተንፈሻ አካላቸውን ታመሙና ቄስት ኢንድ ሆስፒታል ገቡ፤ በዚያ ሆስፒታል የማይለያቸው አስታማሚ የሮዛ ልጅ ፍራንዝ ነበር፤ እነዚህ እህትማማቾች

መጋቢት 30 ቀን 1922 ዓ.ም ሲሞቱ የተዉት ሀብት አራት መቶ ሺ የኢትዮጵያ ብር ነበር።

ሌላዎቹ ተጣባቂዎች ማካ እና ዳካ ናቸው እነዚህ ሩሳውያን ልጆች በ1961 ዓ.ም አሥራ አንድ ዓመት እንደሆናቸው አንድ መግለጫ ወጥቶ ነበር። ሮበርት ቶኬት በጻፉት ስለ ሆሜስ ፌኖሜንስ በተባለው መጽሐፎች ስለነዚህ ልጆች ሲገልጹ «……እነዚህ ልጃገረዶች ሁለት እግሮች አሉዋቸው ትክክለኛ የሆነ ሳይሆን እጭር የሆነ ሦስተኛ እግርም አላቸው፤ እያንዳንዳቸው በየአቅጣጫው ያለውን እግር ይቆጣጠራሉ ወይም ያዛሉ። እነዚህ ልጆች በመስኮ ክሊኒክ በፕሮፌሰር አኖኪኒ ቁጥጥር ሥር ነበሩ……» ብለዋል።

በዚህ ቦታ የተጣባቂዎችን ሐተታ ለመጨረስ አንድ ልጨምርልዎት። በ1908 ዓ.ም በፊሊፒን ደሴት የተወለዱት ተጣባቂዎች ጎዲኖ ወንድማማቾች እየተባባሉ ይጠሩ ነበር፤ አንደኛው ልጅ ሲምፕሊቺዮ ሲባል ሌላው ሉቺዮ ይባላል። እነዚህ ልጆች የተጣበቁት በደረታቸው አጠገብ ነው።

እነዚህን ልጆች አቶ ቴዎድሮስ ያኮ ወደ አሜሪካ አገር ወስደው እያስተማሩ አሳደጉዋቸው በተለይ በስፖርት በኩል ዝነኞች ነበሩ፤ በውሃ ዋና ፤ በገፍልፍ እና በቴኒስ ጨዋታ የተወደዱና ዝናቸው የገነነ ነበር። ዕድሜያቸው ሃያ ዓመት ሲሆን ፊሊፒኖ እህትማማቾች የተባሉትን ሴቶች አገቡ፤ በጋብቻቸው ሰሞን ከጫጉላ ሽር ሽር ሲመለሱ በጋዜጠኞች ተጠይቀው «…….ችግር የለም ሌላው ሰው እንደሚያስበውም አይደለንም ሁሉም ነገር በትክክል ተከናውኗል። አራታችንም እንዋደዳለን…….» ብለዋል።

በ1936 ዓ.ም ዕድሜያቸው ሃያ ስምንት ዓመት ሲሆን ሉቺዮ በኒሞኒያ (ብርድ) በሽታ ተያዘ፤ ሲምፕሊቺዮ ባይታመምም ከወንድሙ መለየት አይችልምና አብረው ተኙ፤ አንድ ቀን ሲምፕሊቺዮ ለጋዜጠኞች ሲናገር «…….ከወንድሜ ጋር በሆስፒታል ውስጥ ተኝተው ነበር፤ ለሊት አንድ ነገር ወረረኝ ምን እንደ ሆነ አላውቅም ይህን ነገር ለወንድሜ ለመንገር ልቀሰቅሰው ነካ ባደርገው ቀዝቅዟል ወዲያው ደውል ደውዬ ነርስዋ ስትመጣ ወንድሜ መሞቱን ነገርኳት…….» ብሏል።

ይህ ከሆነ በኋላ ሐኪሞች በሚያስቸኩል ተሰብሰው ሟቹን ካልሞተው ለመለየት የኦፕሬሽን ሥራ ጀመሩ፤ ቀናቸውና ኦፕራሲዮኑ በጥሩ ሁኔታ አለቀ። ያልሞተው ወንድምም ብቻውን መኖር ጀመረ፤ ከጥቂት ቀናት በኋላ ሜኔጃይትስ በሽታ ለከፈውና ወንድሞ በሞተ በ11ኛው ቀን ሲምፕሊችዮም ሞተ። የኔም ወሬ አለቀ።

በአሜሪካ አገር በማሳቹሴትስ ውስጥ በባርንስታብል ይኖሩ የነበሩት ዶክተር አብነር ሐርሴይ በክረምትም ሆነ በበጋ ለብሰው የሚተኙት 12 ብርድ ልስቦችን ነው።

ከ1709 እስከ 1762 ዓ.ም የነበሩት የሩሲያው ንግሥት ቀዳማዊት ኤልሳቤጥ በልብስ ማስቀመጫ ሳጥናቸው ውስጥ 15.000 ልብሶች ነበሩዋቸው። እነዚህ ልብሶቻቸው በሙሉ ቀለማቸው ጽጌረዳማ (ሮዝ) መልክ ብቻ ያላቸው ናቸው።

በ1840 ዓ.ም ተወልደው በ1910 ዓ.ም የሞቱት እስኮትላንዳውያን አቶ ዊልያም ጎርዶን ለ40 ዓመታት በያመቱ 3 ጊዜ ሦት መጽሐፍ ጽፈዋል።

በስፕሩስ ነዋሪ የነበሩት አቶ ዊልያም ሌድ ፎርድ ከሚስታቸው ጋር የተጋቡበት 81ኛ ዓመት ሲያከብሩ የሚስትዮዋ ዕድሜ 101 ዓመት ሲሆን የባልዮው 102 ዓመት ነበር።

በ1807 ተወልደው በ1897 የሞቱት እንግሊዛዊው ሰር ይስሐቅ ሆልደን የታወቁ ሱፍ ፋብሪካ ያላቸው ሀብታም ሰው ነበሩ። በመሐከለኛው ዘመናቸው ጀምረው በየቀኑ የሚበሉት ምግብ አንድ ዓይነት ብቻ ነበር። ይሄውም የተጠበሰ ፍሬ፤ ከሙዝ የሚሠራ ብስኩት፤ አንድ ብርቱካንና ሃያ የወይን ፍሬዎች ብቻ ነበር። ይህ ምግብ የሚበሉት ቁርስና እራታቸውን ብቻ ነው። በዚህ ዓይነት አመጋገብ 48 ሰዓት ቆይተዋል። ምንም ሕመም ሳያውቃቸው 91 ዓመት ኖረው ሞቱ።

በ1732 ዓ.ም ሕንድ ሐገር የሚካሄደው ራጃድሂራጅ ራናጂ ሽሪፕሩዝ ስማቸው በርዝ ማኔው ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ነው። በአጻጻፋቸው 32 ፊደላት አሉበት። በዚያ እኚህ ገዢ «ስሜ በሚጠራበትም ሆነ በሚጻፍበት

ጊዜ ሙሉ ስሜ 108 ጊዜ እንድትጽፉ ወይም እንድትናገሩ» ብለው አወጁ። ራሳቸውም ቢሆኑ ፊርማቸውን 108 ጊዜ ስለሚፈርሙ ጸሐፊያቸው 107 ፊርማ ይፈርምና ለ108ኛው ለእሳቸው ያቀርባል። የእኚህን ሰውዬ የስም አጻጻፍ ጽፌ በሙሉ ላሳይዎች ነበር። ግን ብቻውን ሁለት ገጽ ያህል ስለጨረሰ ተውኩት። 3456 ፊደላት አሉበት።

በእንግሊዝ አገር ስካርጊተን ውስጥ ነዋሪ የነበሩት አቶ ጆርጅ ፍሊንደር ከፈረስ ጫማ ብቻ አንድ ትልቅ ቋሚ ሐውልት ሠርተው ነበር፤ ለሐውልቱ መሥሪያ የደረደሩት የፈረስ ጫማ ብዛት ሰላሳ አምስት ሺ ነው።

በቱርክ ውስጥ የሚገኘው አንጎራ የሚሉት ፍየል 115 ሳንቲ ሜትር ያህል ርዝማኔ ያለው ጠጉር ያበቅላል።

በኒውዮርክ ከተማ ነዋሪ የነበሩት ወይዘሮ ማርጋሬት ሄይስ በታች ከንፈራቸው አንቻቸውን መንካት ይችላሉ።

በ1867 ዓ.ም ተወልደው በ1911 ዓ.ም የሞቱት አሜሪካዊው ደራስ ዳቪድ ግራሃም ፊሊፕስ በአሥር ዓመት ውስጥ 29 መጽሐፍት ጽፈዋል፤ እነዚህን ድርሰቶቻቸውን በሙሉ የጻፉዋቸው በማተሚያ ቤት ውስጥ ባለ ረጅም የፊደል ለቃሚዎች ጠረጴዛ ላይ ወረቀታቸውን አድርገው ከለሊቱ 8 ሰዓት እስከ አሥር ሰዓት ድረስ በመቆም ነው።

በጀርመን ሀገር በፍሬይበርግ ባለ የመቃብር ቦታ የአንዲት የተኛች ሴት ሐውልት ያለበት መቃብር አለ፤ በመቃብሩ ላይ የሴትዮዋ ስም የለ፤ በመቃብሩ ላይ የሴትዮዋ ስም የለም፤ የማን መቃብር መሆኑም አይታወቅም ግን ለሁለት መቶ ዓመታት ጊዜ በመቃብሩ ላይ በየቀኑ አዳዲስ አበባ ይደረግበት ነበር።

በ1655 ዓ.ም ተወልዶ በ1727 ዓ.ም የሞተው ፈረንሳዊው ሀብታም ፊሊፕ ደ ቬንዶም ማታ አምታ በቤቱ ውስጥ ከመጠን በላይ እስኪሰክር ድረስ ይጠጣና ወደ መኝታው የሚወስደው በሰው ነው፤ በዚህ ሁኔታም በየቀኑ ማቋረጥ ሰላሳ ዓመት ሙሉ በመስከር ኖር ስካሩን ሞት ገላገለው።

በእስፔን ውስጥ ኩራና በተባለ ቀበሌ የሚኖሩ የባላገር ሴቶች ገበያቸው ከመንደራቸው 32 ኪሎ ሜትር ይርቃል፤ እነዚህ ሴቶች ዶሮ ለመሸጥ ገበያ በሚሄዱበት ጊዜ ሃያ ያህል ዶሮዎችን በዕቃ ላይ አድርገው በራሳቸው ላይ በማኖር በእጃቸው ሳይዙ መጓዝ ይችላሉ፤ ዶሮ ስትፈራገጥ ብትውል ዕቃው ከራሳቸው ላይ አይወድቅም።

ከ1633 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1638 ዓ.ም ድረስ በኔዘርላንድ ምክትል አስተዳዳሪ የነበቱ ዉተር ቫን ትዊለት ቁመታቸው 5 ጫማ ከ6 ኢንች ሲሆን የሆዳቸው ዙርያ ክብ 6 ጫማ ከ5 ኢንች ነው። እኚህ ሰው በቀን ውስጥ አሥራ ስድስቱን ሰዓት ስድስቱን ሠዓት የሚያሳልፉት በመብላትና በመተኛት ብቻ ነበር።

የፎቶግራፍ ጥበብ ለመጀመሪያ ጊዜ ተገኝቶ በ1826 ዓ.ም የተነሳው ፎቶ ግራፍ ይሔ ነው፤ ጥበቡን እግኒሴፎር ኒፐሲ የተባለ ሰው ነው፤ ፎቶው የተነሳው በፈረንሳይ አገር ቻሎን በተባለ ቀበሌ ነው በኒውጊንያ ውስጥ ማንኛውንም የግብርና ሥራ የሚሠሩት ሴኦች ናቸው፤ ወንዶቹ ያለባቸው ሥራ ሴኦቹ ሲሠሩ ወንዶቹ በአጠገባእችው መቆም ነው።

በአሜሪካ አገር በኦሐዮ ውስጥ አሽላንድ በተባለው መንደር ላይ መጋቢት 12 ቀን 1890 ዓ.ም በሰማይ ላይ የአንድ ከተማ ምስል (ማራሽ) ታይቷል፤ ከተማው በመሬት ላይ ያለው ከ30 ኪሎ ሜትር ርቅት ላይ ነው።

የፖላንድዋ ንግሥት ራድዚዊል በ1910 ዓ.ም በኢጣልያ አገር በሮም ከተማ ለሚደረገው የበረዶ መንሸራተት ውድድር የበረዶ መንሸራተት የጥንቱን የሮማውያኖችን ጋር በአንበሳና በነብር እያስጎተቱ ራሳቸው ጋሪውን በመንዳት ሄዱ።

በቼኮዝሎቫኪያ ውስጥ ፕራ በተባለ ቦታ የኮከብ ቅርጽ ያለው ሆኖ የተሠራው የጥንት ቤተ መንግሥት አለ፤ ያን ቤተ መንግሥት ያሠሩት የቦሄሚያ ገዥ የነበሩት ፌርዲናንድ ናቸው፤ ፌርዲናንድ ሚስታቸውን «ትንሿ ኮከብ» እያሉ ይጠሩዋቸው ስለነበረ ለሚስታቸው መታሰቢያ ብለው ያን ሕንፃ አሠሩት።

በማዳጋስካር ውስጥ የታማታቬ ጎሳ የሆኑት አቶ ሙሳ በወንዝ ዳር ሲሄዱ እግራቸውን አዞ ያዘቻቸው አቶ ሙሳ እግራቸው በአዞዋ ጥርስ ተነክሶባቸው ሳለ የአዞዋን እግር ይዘው ትግል ገጠሙ፤ አንድ ሰዓት ያህል ከታገሉ በኋላ አዞዋን አሸንፈው እግራቸውን በነፃ ለማስለቀቅ ችለዋል።

በእንግሊዝ አገር ሒቺን ውስጥ የሚኖሩ አቶ ጆን ማንሴል በአንጫቸው ጫፍና በአገጫቸው ጫፍ ዘንግ መያዝ ይችሉ ነበር።

በቻይና ውስጥ ሙሽሮች በሚያገቡበት ጊዜ አሥራ ሁለት ልብሶችን ደራርበው ይለብሳሉ።

በእንግሊዝ አገር በደን ፎርድ ባለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የብፁዕ አቡነ ጆን ጆዌል መጽሐፍ አለ፤ መጽሐፉ በሌባ እንዳይሰረቅ ብለው ቀዳማዊት ንግሥት ኤልሳቤጥ በሰንሰለት ታስሮ አትሮኑ ላይ እንዲቀመጥ አዘዙ፤ ታስሮ ከተቀመጠ 399 ዓመታት አለፉት።

አውስትራሊያዊው ብስክሌተኛ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ 1376 ኪሎ ሜትር ተኩል መንገድ በብስክሌቱ ተጉዟል፤ ይህ በ1933 ዓ.ም ያደረገው የብስክሌት ጉዞ በሰዓት የተጓዘው ሲታሰብ በአንድ ሰዓት 57 ኪሎ ሜትር ተኩል ነው።

በ1822 ዓ.ም ተወልደው በ1914 ዓ.ም በተራራ ወጪነታቸው የታወቁት ስዊሳዊው ዶክተር ጆሃን ኮዝ በዘጠና ሁለት ዓመት ዕድሜያቸው 10360 ጫማ ከፍታ ያለውን ንግላንቺያ የተባለውን ተራራ ወጥተዋል።

በኢጣሊያ በሩሲ አንድ 355 መስኮቶች ያሉት ሕንፃ አለ። መሐንዲሱ የቤቱን ኮንትራት የተቀበለው በአንድ ዓመት ጊዜ ለመጨረስ ስለ ነበረ ለሥራው ለመታሰቢያ ብሎ ነው።

እንግሊዛዊው የኢንደን ነዋሪ የነበረው አቶ ዊሊ ዊሌት በ1752 ዓ.ም አሥራ ሁለት ቀንና ለሊት ሳያርፍ 288 ሰዓት ጨፍሯል።

በ1624 ዓ.ም ተወልዶ በ1679 ዓ.ም የሞተው ዝነኛው ፈረንሳዊ ስዕል ላይ ኒኮላስ ፒር ሎይር ዛሬ የሚደነቅበትን 12 ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ስዕሎ ቹን የሳለው በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ነው።

በ971 ዓ.ም ተወልደው በ1039 ዓ.ም የሞቱት አቡሪይሃን ለአርባ ዓመታት ጊዜ በሕድን አገር የታወቁ የከዋክብት ምርመራ ሊቅ ነበሩ፤ የተሰማሩት ዓይናቸው ለሊት በጨለማ እንጂ ቀን በብርሃን ስለማያይላቸው ነው።

በግብጽና በኡጋንዳ ወሰን ላይ የሚኖሩ ኒሜሌ የተባሉት ሰዎች እስከ ዛሬ ድረስ አሳ የሚያጠምዱ ከአምስት ሺ ዓመታት በፊት ይሠራበት እንደነበረው በውሃ ውስጥ የሚወራጨውን አሳ በቀለት በመውጋት ነው።

በጃፓን አገር መንገድ ላይ የሚደረገው የቆሻሻ ወረቀት መጣያ ዕቃ የሚሠራ የፍየል ራስ ነው፤ ቆሻሻውን ወረቀት የሚጥሉ ሰዎች የፍየሏን ምስል የብረት ራሱን እንካ አድርገው በፍየሏ አፍ ውስጥ ወረቀቱን ይጨምራሉ፤ ፍየል ወረቀት ስለምትወድ ነው።

በ1795 ዓ.ም ተወልደው በ1879 ዓ.ም የሞቱት እንግሊዛዊው የቤርሚንግሃም ነዋሪ የነበሩት ሰር ሮውላንድ ሂል በ12 ዓመት ዕድሜያቸው የሂሳብ አስተማሪ ነበሩ እኚህ ሰው የፖስታ ቴምብር የፈለሰፉ ናቸው።

ከማዶ የሚያዩት ኬክ በሰላ ቢላዋ በጥሩ ተቆርጦለት ወጥቷል፤ ቁራጩ ኬክ የት እንዳለ ለማወቅ ገልብጠው ይዩት በሂማላያ ያሉ የቡታን ሰዎች የላማ ሃይማኖት መሪዎች ለጸሎት ሥርዓት የሚነፉት ጥሩንባ ከሰው ቅልጥም የሚሠራ ነው። በኒዎርክ በሰሜን ታሪታውን ውስጥ አንድ ቤተ ክርስቲያን አለ፤ ቤተ ክርስቲያኑ ከተሠራበት ቦታ አንድ የውሃ ግድብ ተሠርቶ ሲያልቅ ማዕበል እየተነሳ ግድቡን ሦስት ጊዜ አፈረሰው፤ አንድ ቀን ግድቡን ከሚሠሩት ኩሊዎች አንዱ «ግድቡ የሚፈርሰው በአጠገቡ ቤተ ክርስቲያን ባለመኖሩ ነው» ብሎ ብሎ በሕልሙ ያየውን ተናገረና ቤተ ክርስቲያኑ ተሠራ ከ1685 ዓ.ም ጀምሮ ግድቡ በደህና ኖረ።

# ነፍስ ትመጣለች?

የሉራንሲ ቬኑምን ታሪክ ከማንበብዎ በፊት የነገሩን አመጣጥ ከሥሩ ልጀምርልዎ። ሜሪ ሩፍ የተባለች ልጅ በአሜሪካ አገር በኢንዲያና ውስጥ ዋረን በተባለው ቀበሌ ጥቅምት 8 ቀን 1846 ዓ.ም ተወለደች። 13 ዓመት ዕድሜ ሲኖራት ወላጆችዋ ይዘዋት በኢሊኖይስ ውስጥ ዋቴስካ ወደ ተባለ አገር ሔደው መኖር ጀመሩ።

በዋቴስካ የሜሪ ጤንነት እየተበላሸ ሔደ። በተለይም የሚጥል በሽታ ስለያዛት በቀን ሁለት ጊዜ ያህል ይጥላት ጀመር። ሜሪ ከዚህ ኑሮ ለመገላገል ብላ ከእጅ ቁርጭምጭሚቷ አጠገብ ያለውን ትልቁን የደም ሥር (አርተሪ) በምላጭ ቆረጠችው። ብዙ ደም ከፈሰሳት በኋላ ወላጆችዋ ደርሰው ሐኪም ቤት ወሰዱዋት።

ከሐኪም ቤት እያለች ያወራጫት ነበርና ሐኪሞቹ ምንም ነገር እንዳታይ፤ ብለው ዓይኗን በወፍራም ፕላስተር ሸፈኑት። አንድ ቀን የወላጆችዋ ውዳጆች ቄስ ሪያ እና የዳንቪል ታይምስ ጋዜጣ አዘጋጅ አቶ ስሚዝ ከልጅቷ አልጋ አጠገብ ቆመው ሲወያዩ ሚሪ ዓይንዋ ላይ ያለውን መሸፈኛ እንዲያነሱላት ጠየቀች። እንደማይነሳላት ነገሩዋት። «ብዙ ነገር ካየሽ ያምሻል ተብሎ ነው አሉዋት።»

ሜሪም «አሁንም እኮ ማየት እችላለሁ» ብላ በአቶ ስሚዝ ኪስ ውስጥ ታጥፎ የተቀመጠውን ደብዳቤ ከዚያው እንዳለ አነበበችው። በክፍሉ ውስጥ ያለውንም ነገር እየተነተነች ተናገረች።

ሜሪ ድና ከሐኪም ቤቱ ወጣች። ሐኪሞቹን ግራ ያጋባቸው ተሸፍና የማየቷ ነገር ሊቃውንት እየተሰበሰቡ እንዲያጠኑት ተደረገ። ሐምሌ 4 ቀን 1865 ዓ.ም የሜሪ ወላጅጆች አንድ በዓል ለማክበር ፒኦሪያ ወደ ተባለች ከተማ ሜሪን ይዘው ሔዱ። ከዚያው አድረው በነጋታው ቁርስ ሲበሉ ሜሪ ራሴን አመመኝ ብላ ከገብታው ላይ ተነሥታ ሔደች። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወላጆችዋ ወደ ክፍልዋ ቢሔዱ ሜሪ አልጋዋ ላይ እንደተኛች ሞታ አገኙዋት።

ሜሪ ስትሞት ሉራንሲ ቬኑም ከተወለደች ዓመት ከ3 ወርዋ ነበር። ሉራንሲ ቬኑም የምትኖረው በኢዋ ባለ ባንድ የእርሻ ቦታ ነው፡ በ1871 ዓ.ም የሉራንሲ አባት አቶ ቶማስ ቬኑም ቤተሰባቸውን ይዘው ከዋቴስካ ሰባት ማይል ርቃ ካለች አምባ ሔደው እርሻቸውን ጀመሩ። ይህም ሜሪ ሩፍ ከሞተች ከስድስት ዓመት በኋላ መሆኑ ነው። ምንም ይሁን ምን ታሪኩን ላሳጥርሎትና ሜሪን ሉራንሲ ፈጽመው አይተዋወቁም።

ሉራንሲ ጤነኛ ልጅ ሆና አደገች። በ1877 ዓ.ም ሐምሌ 5 ቀን የሜሪ 12ኛ ሙት ዓመት ሲከበር ከሜሪ ወላጆች ዘንድ ተጠርተው ከወላጆችዋ ጋር የሙት ዓመቱን መታሰቢያ በዓል አከብራለች። ዕድሜዋ 13 ዓመት ሆንዋል።

የሜሪ 12ኛ የሙት ዓመት መታሰቢያ በተከበረ ማግስት ሉራንሲ ለወላጆቿ «ትናንት ለሊት ከተኛሁበት ክፍል ደጃፍ ላይ ብዙ ሰዎች ነበሩ። እነሱም ራንሲ ራንሲ እያሉ ይጠሩኝ ነበር። የትንፋሻቸውም ብዛት ፊቴን ለበለበኝ» ብላ ነገረችኝ። በቀጠለውም ማግስት «ትናንት ማታም እነዚያ ብዙ ሰዎች መጥጠው ሲጠሩኝ አደሩ» ብላ ነገረች። ከዚያ በኋላ እናትዮዋ አብራት ትተኛ ጀመር።

ለጥቂት ቀናት ያህል ከረመች። ልክ መጀመሪያ ጊዜ ሰዎቹን አየሁ ባለችበት ሳምንት ቀን ያው ችግርዋ ተቀሰቀሰ። እናትዋን በሥራ እየረዳች ምንጣች ስታነጣጥፍ «እማማ፤ ዛሬ አሞኛል፤ ደስም አላለኝ» አለች። ወዲያው ተኛች። ትንፋሽዋ አጠረ፤ የደም አመታትዋ (ፖልስ) ዝቅ አለ። ትኩሳትዋ ከትክክለኛው የትኩሳት ልክ አዘቀዘቀ ቀዘቀዘች።

ሐኪሞች መረመሩዋት ምን በሽታ እንደሆነ ግን መናገር አልቻሉም። ሕመሙ እየጸናባት ሔደ። ሐኪሞችም ሊያድኗት አልቻሉም። በየካቲት ወር 1878 ዓ.ም ሉራንሲ ከተኛችበት ብድግ ብላ «እኔ የብርሃን መልአክ ነኝ» አለች። ይህን ነገር በመደጋገምዋና በየቀኑም በመናገርዋ ወላጆችዋ በዌስትካ ሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ቄስ ለሆኑት ለቢ ኤም ቤከር አዩዋቸው። ቄሱም ልጅቱን አይተውና የምትናገረውን ሰምተው አብዳለች አሉ።

የሜሪ ሩፍ እናትና አባት ሉራንሲን ለመጠየቅ መጡና አእምሮ ሐኪም ዘንድ ቢወስዷት የሚሻል መሆኑን ለወላጆችዋ አማከሩ። በምክሩ

ተስማምተው በዊስኮንሲ በጃኔንሲቫል የሚኖሩትን ዶክተር ኢ ደብልዩ እስቲቨንስን ጠሩ። ዶክተሩ ጥር 31 ቀን 1878 ዓ.ም ሉራንሲ ካለችበት ቤት ደረሱ።

ዶክተሩ ሲደርሱ ሉራንሲ ተወዛወዥ ወንበር ላይ ተቀምጣ አቀርቅራ መሬት መሬቱን ታያለች። ዶክተሩ ሲገቡ ወንበርዋን አሽከክራ ፊቷን አዞረችና ሐኪሙ እንዳይጠጓት አስጠነቀቀች። ዶክተሩም ራቅ ብለው ተቀምጠው ከሉራንሲ ወላጆችና ከሜሪ አባት ካቶ ሩፍ ጋር ይነጋገሩ ጀመር። እኩል ሰዓት ያህል ልጅቷን በማይመለከት ጉዳይ ሲጨዋወቱ ቆዩና ዶክተሩ ድንገት ወደ ሉራንሲ ዞር ብለው «ይቺን እመቤት አይቻትም አላውቅ፤ ለመሆኑ ስምሽ ማን ይባላል?» አሏት።

«ካትሪና ሆጋን ነኝ» ብላ ሉራንሲ መለሰች። ዶክተሩ እየጠየቋትና እየመለሰች ብዙ ተጫወቱ። በድንገት ሳይታሰብ ሉራንሲ ከተቀመጠችበት ተወዛዋዥ ወንበር ላይ ከመሬት ወደቀች። ዶክተሩ አነሱና አስቀመጡዋት። ከንፈርዋ ይነቃነቃል መናገር ግን አትችልም። በዚህ ሁኔታ አሥር ደቂቃ ያህል ከቆየች በኋላ «ካትሪና ሆጋን ውጪ እናንተም ሌሎቹ ውጡ፤» አለች። ይህ አነጋገር ለዶክተሩም ሆነ ለወላጆችዋ እንቆቅልሽ ነበር።

ዶክተሩ «የሚያነጋግሩሽ ሰዎች አሉን?» አሏት። ሉራንሲም «አዎን አሉ፤ እዚህ ለመምጣት የሚፈጉም ብዙ መናፍስት አሉ።» አለችና ዝም አለች። ጥቂት ቆይታም «ከእነሱም አንደኛዋ የምታስቸግረኝ ሜሪ ሩፍ ናት» ስትል አቶ ሩፍ ከመቀምጫቸው ተነስተው «ሜሪ! ሜሪ የኔ ልጅ ነች፤ ከዓመታት በፊት የሞተችው ልጄ ነች...... አዎ እሷ ነች። እስቲ ትምጣ ብትመጣ በጣም እንደሰታለን» አሉ።

ሉራንሲ ተጣራች፤ «ሜሪ ትፈልጊያልሽና ነይ» አለች።

ሟችቷ ሜሪ፤ ኔርቪ ትላት የነበረችው እህቷ ሚኔርቫ ከእናትዋ ጋር ከዚያው ተቀምጣ ነበረችና ሉራንሲ «ኣንቲና እህቴ ኔርቪ እኚሁና» አለችና ከመቀመጫዋ ተነስታ አንገታቸውን አንገታቸውን አቅፋ እየተንሰቀሰቀች ታለቅስ ጀመር። የሜሪ እናት ወይዘሮ ሩፍ እና ልጃቸው ሚኔርቫም ያለቅሱ ጀመር። ተቀምጠው ወሬ ጀመሩ የአባትዋን የአቶ ሩፍን ጓደኞች የእናትዋን

ባልንጀሮች ሁሉ ደኅንነት ጠይቃ «.......የዛሬ 13 ዓመት የሞትሁ ጊዜ ግብዛ ጠርተውን እቤታቸው የሞትኩባቸው ፒአራ ያሉት ወዳጆቻችሁ ደህና ናቸው?? ያቺስ ሣጥኔ አለች?? ያቺ ከመሞቴ በፊት ጓደኞቼ የሚጽፉልኝን ደብዳቤዎች አስቀምጥባት የነበረችውን ሣጥኔን ነው የምላችሁ.......» አለች።

ወይዘሮ ሩፍም «አለች በጥንቃቄ አስቀምጫታለሁ» አሉ። በርሉራንሲ ላይ የመጣው የሜሪ መንፈስ ከደብዳቤዎቹ የአንዳንዶቹን ጽሑፍ ተናገረች። በኋላ ሣጥኑን ከፍተው ሲያነቡትም ትክክል ሆነ።

«እማዬ?? ናፍቃችሁኛልና እንድጠግባችሁ ጥቂት ቀን እቤታችሁ ውሰዱኝ» ብላ ሉራንሲ ብድግ አለች። ዶክተር እስቲቨንስም እንደምትላችሁ አድርጌ አሉ። ሉራንሲ ቤትና ወላጆችዋን ትታ በሜሪ መንፈስ ተሞልታ ከሜሪ ወላጆች ቤት ሔደች። በዚያም እስከ ግንቦት ወር ድረስ ቆየች። ወሬው ተባዛ፤ የቺካጎ ጋዜጦች በየቀኑ ታሪኩን ያወሩ ጀመር። ዶክተር እስቲቨንስም ከዚያው ሳይለዩ ነገሩን አንድ ባንድ ይከታተሉ ጀመር። በመጨረሻም ዝርዝር ታሪኩን በመጽሐፍ ጽፈው አወጡት። መጽሐፉን ለማንበብ ከፈልጉ «ዘ ዋቴስካ ወንደር» ይባላል።

ጋዜጠኞች ተሰብስበው «አንቺ ሜሪ ሩፍ ነኝ ትያለሽ፤ አቶ ሩፍንና ወይዝሮ ሩፍንም ወላጆቼ ናቸው ትያለሽ፤ መሞትሽንም ትናገሪያለሽ፤ ያልሞተችው ባለ ሥጋዋ ሉራንሲ ወዴት ነው ያለችው??» ብለው ጠየቋት። «ሉራንሲ አሟት ትታከማለች አሁን ተሽሏት ከኔ ጓደኞቼ ጋር ትጫወታለች፤ እኔ መልአኮች የወሰኑልኝ ጊዜ ሲደርስ እሔዳለሁ እኔ ስሔድ ሉራንሲ ትመጣና ቦታዋን ትይዛለች» ብላ መለሰች።

ጋዜጠኞቹም «እውነት አንቺ የሞተችዋን ሜሪን እንደሆንሽ ከሜሪ ታሪክ አንድ ነገር ንገሪን» አሏት።

«እማዬ! (ማማ)» ብላ ተጣራችና «ትንሿን ሣጥኔን አምጪልኝ ያቺን ጌጤን ላሳያቸው» አለች። አመጡላት ከሣጥኑ ውስጥ በርብራ አንድ ራስ ላይ ሚደረግ ጌት (ቲያራ) አነሳችና «ይሔ እወደው የነበረው ጌጤ ነው፤ የማደርገውም በማንኛውም ቀን ሳይሆን ግብዣ ስጠራና በበዓል ቀን ብቻ

ነበር። እናቴም ያስቀመጠችው እወደው እንደ ነበር ስለምታውቅ ነው» አለች። የሟችቷ የሜሪ እናትም ወይዘሮ ሩፍ «ያለቻችሁ ሁሉ እውነት ነው» ብለው ለጋዜጠኞቹ ነገሩ።

የማችቷ የሜሪ አባት አቶ ሩፍ «ታስታውሺ እንደሆነ ቴክሳስ ስንሔድ እንዴት ነበር?» ብለው ጠየቋት። «አስታውሳለሁ ቀዩ ወንዝ አጠገብ ስንደርስ ሕንዶችን አገኘን፤ ከኛ ጋራ ይሄዱ ከነበሩት ከወይዘሮ ሪደር ልጆች ጋርም ተነጋገሩ። ከዚያ ስናልፍ አንድ ሰውዬ አገኙንና ካንተ ጋር ስታወሩ የድሮ ጓደኛህ መሞቱን ነገሩህ፤......እናቴ አንድ ቀይ ቆብ ገዛችልኝ ቆብዋ ጠባብ ሆና ራሴ ውስጥ አልገባ ብትል ጠጉሬን ቆረጣችሁት አሁንም አልገባ ብትል ባርኔጣዋን ቀደህ አላገባህልኝም?? ይሄን ተወውና የቀብሬንም ልንገርህ ስቀበር የተገኘው ሰው ጥቂት ነበር፤ ላገሩ እንግዳ ነበራችሁና ነው። በዚህ እንኳ ስትበሳጭ ቀብሩ ላይ የነበሩ አንድ ሽማግሌ ቀረብ ብለው አይዞህ ምንም አይደል ሰው ቢበዛም ልጅህን ከሞት አያድኑም አላሉህም?» አለች።

የሟችቷ አባት አቶ ፍሩ ‹፣እይማያት ሉራንሲ ነች፤ የምትናገርዋ ግን ትክክለኛ ልጇ ነች የምትለው ሁሉ እውነት ነው» አሉ። በሉራንሲ የተወኻደው የሜሪ መንፈስ ብዙ ሲያወራ ከረመ። ዶክተር እስቲቨንስ ታሪኩን ቀንና ለሊት ይከታተሉ ነበርና አንድ ቀን ሲጨዋአወቱ «ዶክተር? ስለ ልጅዎ ስለኢማ እንድትነግሮት ይፈልጋሉ?? አለች። ዶክተሩም «አዎን መጥታ ብታነጋግረኝ ደስ ይለኛል» አሉ «ኢማ ኢንጂሊያ እስቲቨንስ አሁን ከዚህ ከቅርብ የለችም፤ ግን ብዙ ጊዜ ስለ እናንተ ናፍቆት ታወራ ነእብር። አንድ ጊዜ ኦፕራሲዮን ሲያደርጓት ግንባርዋ ላይ የሰፉት ስፌት የኤክስ ምልክት ሆኖ መልኳን አበላሽቶባት እንደ ነበር ነግራናለች፤ ኢማ አሁን የምትኖረው በብዙ ደስታ ነው» አለቻቸው። የዶክተር እስቲቨንስ ልጅ ኢማ ኢንጂልያ የሞተችው ከሃያ ዘጠኝ ዓመት በፊት በ1849 ዓ.ም በመጋቢት ወር ነበር።

ግንቦት 7 ቀን 1878 ዓ.ም በሉራንሲ ላይ ሆና ትናገር የነበረችው ሜሪ እናትዋን ወይዝሮ ሩፉን ጠራችና «እንግዲህ ልለይሽ ነውና ነይ ሳሚኝ» አለች ወዲያው እናትዋን አቅፋ ለጥቂት ደቂቃዎች እየተላቀሱ ቆዩ። ሉራንሲ ወይዝሮ ሩፍን ለቃ ወደ ፊቷ ወደቀች። አንስተው ሲያስቀምጧትም «የት ነው

ያለሁት» አለች። ወዲያው «ለብዙ ጊዜ እንቅልፍ ወስዶኝ እንደ ነበርስ አውቃለሁ፤ ግን እዚህ ቤት እንዴት መጣሁ?» አለች። ሐኪሞች ብዙ ምርመራ አደረጉላት። ጋዜጠኞችም ብዙ ጥያቄ ጠየቋት። የሉራንሲ ጉዳይ አለቀ።

አሳጥሬ የጻፍኩት የሉራንሲን ታሪክ ከመዝጋቴ በፊት ጥቂት ልጨምር። ጆርጅ ቢንግን የተባለ ሰው አግብታ በካንሳስ ውስጥ ሮሊንስ በተባለ ቀበሌ ይኖሩ ነበር። ከዚሁ ባላቸውም 11 ልጆች ወልደዋል። በ1940 ዓ.ም በካሊፎርኒያ የወጣ ጋዜጣ «.......ሳይንቲስቶች የ76 ዓመቷን አሮጊት ወይዘሮ ሉራንሲን የልጅነታቸው ጊዜ መንፈስ እንዳለ መረመሩ፤ ግን ምንም አላገኙም......» በማለት አንድ ዜና አውጥተው ነበር። ከዚያ ያለውን ታሪክ እኔ አላየሁም።

***

ታላቁ የአሜሪካ ፕሬዚደንት አብርሃም ንከን በዘራቸው በሰው እጅ ሲገደሉ ሁለተኛው ሰው ናቸው፤ አያታቸው በሰው እጅ ተገደሉ፤ የሁለቱም ስም አብርሃም ነው፤ የሁለቱም ሚስቶች ስም ሜሪ ነው፤ ሁለቱም ደግሞ ቶማስ የሚባሉ ልጆች ነበሩዋቸው።

ከ1680 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1740 ዓ.ም ድረስ በጀርመን አገር የታወቁ ቁማርተኞች ሁሉ ቁማር አዋቂነታቸውን ለመግለጽ የመጫወቻ ካርታ፤ አዲስ እና ልዩ ልዩ የቁማር መጫወቻ መሣሪያዎቻቸውን አንግተው በአደባባይ ይዞሩ ነበር።

አሜሪካዊው ኸንሪ ቻርልተን አንድ ሚኒስትር ተሳደበና በራሱ ኪሳራ አንድ የማሰሪያ ግንድ እንዲሠራ ታዘዘና ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ በዚያ በሠራው ማሰሪያ ሦስት ሳምንት እንዲታሰር ተፈረደበት።

በፊሊፒንስ ውስጥ ያሉ ሱሉ የሚባለው ጎሳ ሰዎች በሚጋቡበት ጊዜ ሙሽራዎቹ ከቤት የሚወጡት እያንዳንዳቸው በሁለት እንግዶች ትከሻ ላይ እየተቀመጡ ነው።

በእንግሊዝ አገር አልድ ሳሩም በሚባል ቀበሌ የቅዱስ አስመንድ ካቴድራል ሰላሳ ዓመት ሙሉ ሲሠራ ኖሮ ሊያልቅ ጥቂት ሰዓት ሲቀረው ሙብረቅ ብትንትኑን አውጥቶ አፈራረሰው።

በ1752 ዓ.ም ተወልዶ በ1833 ዓ.ም የሞተው ፊሊሞን ሐውኪንስ በ16 ዓመት ዕድሜው የግንቬሌ ከተማ ዳኛ ሆኖ ነበር።

በእንግሊዝ አገር ስቶክኔቪንግተን ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ወይዝሮ አን ሃርቶፐ፤ በዘጠና ዓመት ዕድሜያቸው ሲሞቱ ዕድሜያቸውን ሙሉ ይለብሱት የነበረው ልብስ ጥቁር የኀዘን ልብስ ነበር። ከመወለዳቸው በፊት አንዲት እህታቸው ተወልዳ ስለሞተች እና ስማቸውም በሟችቷ ስም ስለተሰየመ ለእሷ ኀዘን ብለው ነው።

የጥንት ግብፃውያን አምላክ የነበረው በማምለኪያው ምስል ላይ ጆሮ አለ፤ ጸሎት በትክክል ለመስማቱ ማስተማመኛ ነው።

በደቡብ ካሎሪና ያሉ ካታውባ የሚባለው የሕንድ ጎሳ ሰዎች ከሰል በእሳት ተያይዞ ፍም ከተንረከከ በኋላ በባዶ እግራቸው በፍሙ ላይ በመጨፈር አንድ ሰዓት ያህል ይቆያሉ።

የጥንት የሐዋይ ንግሥቶች በበዓላቸው ጊዜ በአንገታቸው የሚያጠልቁት በአበባ ፈንታ ፍሬ ነው።

በናይጄሪያ የሚኖሩ የኢቦ ጎሳ አፍሪካውያን የተለየ የቀን አቆጣጠር አላቸው፤ አንድ ሳምንት የሚሆነው አራት ቀን ነው፤ ሰባቱ ሳምንት ደግሞ አንድ ወር ይሆናል።

በአፍሪካ ውስጥ ሙኩሌሄ የሚባሉት ዓይኑን አፍጥቶ የሚጮህ የሚጠመው ከብቶች ቤቱን ሲሰርቁ ለማስፈራራት ነው የሚባሉት ሰዎች ቤታቸው ላይ የሚመስል ስዕል ይሠራሉ ስዕሉ እንዳይጠጉትና ሌቦች እንዲያይ ይላሉ።

በኢየሩሳሌም ውስጥ ኢየሱስ የመጨረሻውን ጸሎት በጸለየበት ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበታል፤ በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጌታ ያስተማረው ጸሎት «አባታችን ሆይ» ወይም በግዕዙ አቡነ ዘበሰማያት በሰላሳ ቋንቋዎች ተቀርጸው ተቀምጠዋል፤ ከነዚህም አንዱ የተቀረጸው በግዕዝ ነው።

በ15ኛውና በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ኢጣሊያውያን የማይዙት ከባርኔጣቸው ጋር በተቆራኘ ከረጢት ነበር።

በኮሎምቢያ ውስጥ ጌይራ ፎሬስት በሚባለው ሥራፍ የሚኖሩ ሰዎች ሚስታቸውን ለመፍታት በሚፈልጉበት ጊዜ ጥቁር ማክስ (የፊት መሸፈኛ) ያደርጋሉ፤ ይህንንም ማስክ የሚያደርጉት ለአንድ ዓመት ጊዜ እንው፤ ከአንድ ዓመት በኋላ ከጋብቻው ነፃ ስለሚሆኑ ማስኩን ያወልቃሉ።

በ1870 ዓ.ም የነበሩ የአሜሪካ ወታደሮች ለሊት በሚዘዋወሩበት ጊዜ መንገዳቸውን እያዩ የሚሔዱበት በጋዝ የምትሠራ ኩራዝ በባርኔጣቸው ላይ ያደርጉ ነበር።

በምዕራብ አፍሪካ ውስጥ የሚገኙት ኪሲ የተባለው ጎሳ ሰዎች በሚቀበሩበት ጊዜ መቃብራቸው ዙርያውን በግንዲላ ይከበባል ግንዲላው መጥፎ መናፍስት ያርቃል ይላሉ።

በሰሜን ሮዴሺያ የሚኖሩ የዋሺ ጎሳ ሴቶች በሚያገቡበት ጊዜ የሙሽርነታቸው ምልክት ሣር ነው የሰንበሌጡ ሣር ለዚሁ ተብሎ በሚዘጋጀው በሙሽራይቱ ላይኛና ታችኛዋ ከንፈሮች ላይ ባሉት ቀዳዳአዎች ይሰካል።

በምዕራብ ጀርመን ውስጥ በእስቱትጋርት አንድ የቴሌቪዥን ማስተላለፊያ የአንቴና ሕንፃ አለ፤ የዚህ አንቴና ርዝመት 230 ሜትር ነው። 163 ሜትር ከፍታው ላይ ሕዝብ የሚገባበት ሆቴል ቤት አለ።

በናይጄርያ ውስጥ የአዴ ጎሳ ሰዎች በመከር ወራት ባላቸው በዓል ምላሳቸው ውስጥ ረጅም ብረት ጦር በመሰካት ሲጨፍሩና ሲዘዋወሩ ይውሉና በዓሉ ሲያልቅ ጦሩን ይነቅሉታል፤ በምላሳቸው ላይ አንዲትም ቁስል መገኘት ይቅርና ደም እንኳ አይወጣውም።

በአፍሪካ ውስጥ የሚታካም ጎሳ ሴኦች ባል አግብተው የሙሽርና ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በራሳቸው ላይ የደረቀ ግማሽ ዱባ እንደባርኔታ አድርገው ነው።

በኒውዚላንድ የምትገኘው ኪዊ የሚሏት ወፍ ክንፍም ጭራም የላትም። ቀን ዓይንዋ አያይም፤ አፍንጭዋ ያለው ኩንቢዋ ላይ እንው፤ የምትበላው ደግሞ ትላትል ነው።

በዓለም ላይ እስካሁን ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ትልቅ ስዕል ፓኖራማ አፍ ሚሲሲፒ የሚባለው ስዕል ነው፤ ይህ ስዕል የተሳለው በ1846 ዓ.ም ጆን ባንቫርድ በተባለ ሰው ነው የዚህ ስዕል ስፋት 3 ሜትር ከ66 ሳንቲ ሜትር ወይም 12 ጫማ ሲሆን ርዝመቱ ግን አምስት ሺ ጫማ ወይም 1525 ሜትር ነው፤ ይህ ስዕል በዚህ ርዝመቱ 1920 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያእልውን ምድር ውበት አጠቃሎ ያሳያል።

ሰዐሊው ጆን ባንቫርድ ኅዳር 15 ቀን 1815 ዓ.ም ኒውዮርክ ከተማ ተወለደ፤ ወላጆቹ ድሆች በመሆናቸው በ15 ዓመት ዕድሜው ትምህርቱን ትቶ ምግቡን ፍለጋ ከተማ ውስጥ የሚዞር ወረበላ ሆነ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንድ መድኃኒት ቤት ተቀጠረ፤ በዚያም በየወረቅቱ ላይ ከመሞጫጨር በስተቀር ለገበያተኞች ቁብ የሌለው ስለሆነ ጥቂት ቀናት እንደሠራ አባረሩት።

ዕድሜው 25 ዓመት እስኪሆነው ድረስ ከሥራ ወደ ሥራ ሲዘዋወር ቆየና በመጨረሻው የሚሲሲፒን ወንዝ ከመነሻው ጀምሮ እስከ ኒውኦርሊየስ ከተማ ድረስ ያለውን ትርኢት ለመሳል ቆርጦ ተነሳ፤ አራት መቶ ቀንና ለሊት በእንዙ አጠገብ እየተዘዋወረ ኖረ፤ ምግቡንም የሚበላው አንዳንድ አውሬዎችን እያደነ መያዝ ነበር፤ በሺ የሚቆጠሩ ንድፎችንም ሠርቶ ጨረሰ።

የባንቫርድ ወዳጅ የነበረ ሴሉም ውድዎርዝ ከጻፈው ጥቂቱን ላስነብብዎት «......ባንቫርድ የንድፉን ሥራ እንደ ጨረሰ ከቤት ሆኖ የተለያዩ ንድፎቹን አንድ ጨርቅ ላይ መሳል (መገልበጥ) ጀመረ፤......ጨርቁ በአንድ በኩል እንዲያው የተቆለለ ሲሆን ስዕሉን የሚሠራው ያን ቁልል ጨርቅ እየሳበ ግድግዳ ላይ በማስያዝ ነው፤ የሳለውና የጨረሰው ደግሞ በአንድ በኩል በትልቅ ግንዲላ ላይ እየተጠቀለለ ይቀመጣል፤...... በዚህ ሁኔታ ስዕሉን በሙሉ ሠርቶ ጨረሱ......» ይላል።

የባንቫርድ ስዕል ለመጀመሪያ ጊዜ በኤግዚቢሽን ለሕዝብ የታየው በሉስቬል ነው፤ ለሕዝብ በታየበት ጊዜ ስዕሉ በትልቅ መጠቅለያ ሆኖ ቀርቦ

እየተተረተረ ካንድ በኩል ካለው ባዶ መጠቅለያ ላይ እየተጠቀለለ ነበር ይህም የመተርተርና የመጠቅለል ሥራ ማለት አንዱን ወጥ ስዕል አንድ ጊዜ ለሕዝብ ለማሳየት የሁለት ሰዓት ጊዜ ይፈጅ ነበር።

ይህ ስዕል በኒውዮርክ ከተማ በአንድ መጋዘን ውስጥ እንደ ተቀመጠ እሳት ተነስቶ ሰዐሊው ባንቫርድ ከመሞቱ በፊት ግንቦት 16 ቀን 1891 ዓ.ም ተቃጠለ ጆን ባንቫርድም በዚያው ዘመን ሞተ።

የስፔይኑ በሮንካሎ ይኖሩ የነበሩት ጁአን ፓታጎርዳ በአበላል ከአህያ እቀድማለሁ ብለው ተወራርደው ከአህያ ጋር እኩል የተሰጣቸውን ምግብ ከአህያዋ ቀድመው ጨረሱ።

በእስያ ውስጥ የሚገኙ የካዛክ ጋላቢዎች ፈረሳቸውን ሽምጥ እየጋለቡ ከመሬት ላይ በኩባያ ተሞልቶ የተቀመጠ ወተት አንስተው ወተቱ ጠብ ሳይል ይጠጣሉ።

በደቡብ አፍሪካ የባቡር ሐዲድ ሠሪ የነበሩት አቶ ጆርጅ ፓውሊንግ በቀን ሦስት መቶ ዶሮዎች ያህል ሥጋ ይበሉና በላዩ ላይ ሦስት ጠርሙስ ሻምፓኝና አንድ መቶ ጠርሙስ ቢራ በየቀኑ ይጠጡ እንደ ነበር ታሪካቸው ተጽፎ ይነበብላቸዋል።

አዞ ከእንቁላልዋ ውስጥ ተፈልፍላ ስትወጣ ወይም ስትወለድ ከውስጡ ከወጣችበት እንቁላል ሦት ብልጫ አላት፤ በሌላ አነጋገር በትልቅነት ከወጣችበት እንቁላል ሦስት እጅ ትበልጣለች።

በእንግሊዝ አገር በበርንሃም ውስጥ በ1530 ዓ.ም የነበረው ኤድዋርድ ቦቪንግተን ሦስት ምላሶች ነበሩት።

አቶ ፍራንክ ዙበር በኒውዮርክ አውራጃ በኖርዊች ከተማ ለአሥራ ስድስት ዓመታት በከንቲባነት አገልግለዋል፤ በዚህ የአገግሎት ዘመናቸው ውስጥ አንዲትም ቤሳ ለአገግሎታቸው አልተቀበሉም ነበር፤ በጠቅላላው በነፃ ነው ያገለገሉት።

በቻይና ውስጥ ኩዋንግተንግ በተባለ ቦታ ተራራ ላይ አንድ ከድንጋይ የተሠራ ምስል የሆነ ሐውልት አለ፤ ሐውልቱን የሠራው ገበሬ ወደ ሥራው

ሔዶ እስኪመለስ ድረስ ወይም በሚመለስበት ጊዜ ሚስቱ ከተራራው ላይ ቆማ ትጠብቀው ስለ ነበር ለእሷ መታሰቢያ ብሎ ነው።

በ1234 ዓ.ም ፈረንሳዊ ፖኵረን በተደጋገመ ሌብነቱ ስላስቸገረ የዘመኑ የፈረንሳይ ፍርድ ቤት በስቅላት እንዲገደል ፈረደበትና «ሆኖም አመሉን የምታስተው፤ ድሃ ሴት አገባለሁና፤ ባሌም አድርጌ በደህና አኖረዋለሁ የምትል ሴት ከተገኘች ስቅላቱ እንዲቀርለትና ለሴትዮዋ እንዲሰጥ» ሲል በተጨማሪ ፈረደ፤ ይህን ጥያቄ የምታቀርብለት ወይም ባል አደርገዋለሁና ለኔ ስጡኝ የምትል ሴት ጠፍታ ሊሰቀል ተወሰደ፤ ከመሰቀያው ቦታ ደርሶ ሊሰቀል ገመዱ አንገቱ ውስጥ ሲገባ አንዲት አሮጊት መጥታ «አትስቀሉት፤ እኔ ባሌ አድርጌ አኖረዋለሁና ለኔ ስጡኝ» ብላ በፍርዱ መሠረት ሰውየውን ለማዳን ጠየቀች፤ የመስቀያው ገመድ አንገቱ ገብቶበት የቆመው ፖኵረና ሴትዮዋን አቆልቁሎ አየና ወዲያውን ወደ ሰቃዩ ሰውዬ ዘውር ብሎ «ወንድም ለምን ሥራ ትፈታለህ? ይቺን አስቀያሚ አሮጊት ከማገባት አንገቴ ላይ ያለውን የመሰቀያዬን ገመድ ባገባ ይሻለኛልና ሰቅለኸኝ ወደምትሄድበት ሂድ» ብሎት ተሰቅሎ ሞተ።

የእስረኛና የወንጀለኛ ጉዳይ ከተነሳ አንድ ልጨምርሎት። አሁንም በፈረንሳይ አገር ፊስሜስ በተባለው ቀበሌ ይኖር የነበረው ታንቶን ካርቱቼ እሥር የሚይዘው ሰው አልነበረም። ከ1690 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1707 ዓ.ም ድረስ ባሉት 17 ዘምናት ውስጥ እንዲታሰርና እየተፈረደበት ሃያ ስድስት ጊዜ ከወህኒ ቤት አምልጥዋል። በመጨረሻው ያገሪቱ ዳኞች ወህኒ ቤት የማይዘው ሰው ስለሆነ ከሥራው ወንጀል ሁሉ ነፃ ነው ብለው ነፃነቱን ሰጥተው አሰናበቱት።

የሕንድ ቢሒል ሰዎች ልጆቻቸው ሲታመሙ በሚባለው ዛፍ ቀዳዳ ውስጥ ልጁን ሰባት ጊዜ ሲያሾልኩት ከሕመሙ ይድናል።

በአፍሪካ ውስጥ የቡባንጂዳ ሡልጣን የነበሩት ሬይ ቡባ ስምንት መቶ ሚስቶች ነበሩዋቸው፤ እነዚህ ሚስቶቻቸውም የሚኖሩት እያንዳንዳቸው በየራሳቸው ቤት ለየብቻቸው ነው።

በ1797 ዓ.ም ተወልደው በ1875 ዓ.ም የሞቱት የአስለለው ሰው አቶ ናፒር ባሎሜ ሀብታም ሰው ነበሩ፤ ሌቦች ያስቸግሩዋቸው ስለ ነበር ኪሳቸውን ከሌቦች ለመከላከል እያሉ በኪሳቸው አጠገብ ትንሽ ጦጣ እየያዙ ይዞሩ ነበር።

በቤልጅግ ውስጥ በሮዴ ባለው የቅዱስ ጄኔስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ጊዜ የተጋገረው ዳቦ ሁለት መቶ ኪሎ ያህል ክብደት ነበረ።

በምሥራቅ ጃቫ የሚኖሩ ሰዎች ሚስት ለማግባት በሚፈልጉበት ጊዜ ሴትዮዋን አይለምኑም ወይም አማላጅ አይልኩም። ለወደፊቱ መኖሪያችን ጣሪያ ይሆናል ብለው የሠሩትን ጣሪያ ወስደው ሊያገቡዋት ከሚፈልጓት ሴት ደጅ ያደርጉትና ይሄዳሉ ከሃያ አራት ሰዓት በኋላ ተመልሰው ሲመጡ ጣሪያ ተብሎ በተቀመጠው ላይ ሁለት ቀዳዳ ካገኙ ልጅቷ ፈቅዳለች ማለት ነው፤ ካጡበት ግን እምቢ ማለቷ ስለሆነ ይሄዳሉ።

በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ የማሳይ ጎሳ ሰዎች የሰጎን ላባ በራሳቸው ላይ የሚያስሩት ከአንበሳ ጋር በእጃቸው ብቻ ታግለው አንበሳው ሲገድሉት ነው።

በሕድን ያሉት ካኒስ የሚባሉት ሰዎች እንደደጋን በሚሠሩት መሣሪያ ጠጠር እያስፈነጠሩ በራሪ ወፍ መግደል ይችላሉ።

በእስኮትላድ ውስጥ ኪርኪነር በተባለ ቦታ አንድ እይጋብቻ ድንጋይ እየተባለ የሚጠራ አምስት ቀዳዳዎች ያሉበት ድንጋይ አለ። አዲስ የሚጋቡ ሰዎች ድንጋዩ ዘንድ ይሄዱና እጃቸውን በቀዳዳው ውስጥ አስገብተው ያወጣሉ፤ ምክንያቱም ጋብቻውን እንደ ድንጋይ ያጠነክረዋል፤ ብለው ስለሚያስቡ ነው።

በጀርመን አገር ኤከረ ንፋርድ በሚባል ቦታ ባለ የቅዱስ ኒኮላስ ቤተ ክርስቲያን በራፍ ላይ አንድ ትልቅ መልሕቅ አለ፤ መልሕቁ በዚያ ቦታ የተደረገው ከ125 ዓመታት በፊት በባሕር ላይ ተደርጎ ለነበረው ጦርነት መታሰቢያ ነው።

በሕንድ አገር በኒው ደልሒ ከተማ የቢርላ መቅደስ ለማንኛውም ሃይማኖት ማምለኪያ የሚሆን ነው፤ የማንኛውም ሃይማኖት ተከታይ በዚያ መቅደስ መጸለይ ይችላል።

የክርስቶስን ልደት በአል ፈረንጆች በሚያከብሩበት ጊዜ ሳንታክላውስ የሚሉት ሰው ለልጆች ስጦታ ያደርጋል፤ ሳንታክላውስ ሳቂታ፤ በነጭ ጥለት የተከበበ ቀይ ልብስ የሚለብስ ወፍራም ሰው አድርጎ የሠራው ቶማስ ናስት የሚባል ካርቶን ሰዓሊ ነው፤ ስዕሉን የሳለው ከ110 ዓመታት በፊት ነው።

በሰሜን አፍሪካ ዴርር በተባለ ሥፍራ ያለው መስጊድ በጣሪያው ላይ ወደ 42 ጉብታዎች አሉበት፤ ይህም መስጊዱን የሠራው ሰው ዕድመኢው 42 ዓመት ነበርና ነው።

በአሜሪካ አገር በቺካጎ ውስጥ በኢሊኖይስ አዎድ ሕንፃ አለ፤ ሕንፃው አሥር ፎቆች አሉት፤ ይህ ሕንፃ በ1884 ዓ.ም የተሠራ ነው፤ ይህ ሕንፃ በዓለም ላይ ከተሠሩት ረጃጅም ሕንፃዎች የመጀመሪያው ነው፤ በመጀመሪያ አጽሙ ተሠርቶ በኋላ ግድግዳው ከሚሠራላቸው ዘመናዊ ሕንፃዎች የመጀመሪያው ነው።

በጃቫ ውስጥ አንድ ሰው ከተቀበረ በኋላ በመቃብሩ ላይ ከፀሐይ መከላከያ የሚሆን ዣንጥላ፤ የሚወደው የቤት ዕቃ ሁሉ በመቃብሩ ላይ ይደረጋል፤ ይህም ነፍሱ በዚያ አካባቢ ስትመላለስ ትወደው የነበረውን ዕቃ እንዳታጣ እያሉ ነው።

በጃፓን ውስጥ ሴቶች በኀዘን ጊዜ ለኃዘን መታወቂያ የሚያደርጉት ትልቅ ባርኔጣ ነበር።

በጋና ውስጥ ድሆች የሚሠሩትን የመኖሪያ ውስጥ የመኪና ቼርኪዮ (እግር) በማድረግ የማይከፈት መስኮት ወይም ፉካ ያደርጉታል።

በምዕራባዊ ሕንድ የሚገኙ ፖሊሶች በዓለም ተመሳሳይ የሌላቸው ናቸው። ስድስት ወር ያህል ስርቆት ይፈቀድላቸዋና ከዚያ በኋላ ታማኝ ዘበኞች ይሆናሉ።

በ1562 ዓ.ም ተወልደው በ1633 ዓ.ም የሞቱት እንግሊዝ መንግሥት ምክትል ቻንስለር የሞቱት ጆርጅ አቦት በ1621 ዓ.ም ሐምሌ 24 ቀን አውሬ ለማደን ወጥጠው በስህተት ጓደኛቸውን ስለገደሉ ያቺን ማክሰኞ ቀን ዕድሜ ልካቸው ድረስ ምግብ ሳይቀምሱባት ይውሉ ነበር።

# ቀን ይጨልማል?

የቀን ብርሃን እንደ ሻማ ወይም እንደ ኩራዝ ድርግም ብሎ ጠፍቶ ቀኑ ጨለማ የሚሆንበት ጊዜ አለ፤ በአገራችንም ቢሆን ታሪክ ጸሐፊዎች ነገሩን አያቅዩት ወይም ታሪክ ጸሐፊዎች ጽፈውት የአሁን ጸሐፊዎች ተረት መስሎአቸው ትተውት እንደሆነ እንጃ እንጂ የቀን ጨለማ የሆነበት ጊዜ አይጠፋም፤ ከፈረንጅ አገር ግን ከየቦታው ያነበኩትን ላጫውትዎ።

በ1780 ዓ.ም ግቦት 19 ቀን በደቡብ ምዕራብ አሜሪካ ባለች አንዲት ከተማ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ገደማ ጨለማ ወረራት፤ ጨለማ ወረራት ጨ፤እ፣ አው እየተዛመተም እስከካናዳ ወሰን ድረስ ደረሰ፤ ጨለማው በዚያ አልነበረም፤ ከኒውዮርክ ከተማ ምሥራቁ ክፍል ሜይን ኒው ሀምፕሻየር የሮዴ ደሴት ማሳቹሴትስ፤ ኮኔክትኬት ሁሉ ቀኑ ወደ ጨለማነት ተለወጠ።

ከቀኑ ሰባት ሰዓት ሲሆን ፍፁም ድቅድቅ ጨለማ ሆነ፤ ነጭ ወረቀት ዐይን አጠገብ አስጠግቶ ካልሆነ በስተቀር ከማይታይበት ደረጃ ደረሰ፤ ተማሪ ቤቶች ተማሪዎችን አሰናበቱ፤ በየቤቱ መብራት በራ፤ በኒውሀምፕሻየር ላይ ስለነበረው ጨለማ የተፃፈውን ታሪክ «……ዶሮዎች በየቆጣቸው ሠፈሩ፤ ወፎች በየጎጆአቸው ገቡ፤ ልክ በግብፃውያን ላይ ደርሶ እንደ ነበረው ጨለማ ያለ ነበር……» ይላል።

ብዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ይጸልዩ ጀመር፤ የፍርድ ቀን (የምፅአት) የሆነም መስሎአቸው ነበር፤ በሰዐት ቁጥጥር ቀኑ እንደጨለመ ውሎ ደንበኛው ምሽት መምጣጡ ታወቀ፤ ትታይ የነበረችው ሙሉ ጨረቃ ደም በመምሰልዋ እንደተለመደው ብርሃን ለመስጠት አልቻለም፤ የሚታዩት ከዋከብትም የደበዘዙ ነበሩ፤ እውነተኛው ለሊት ሲያልቅ በነጋታው ደንበኛው ንጋት ነጋ።

በ1884 ዓ.ም ሚያዝያ 26 ቀን ደግሞ በእንግሊዝ አገር በፕሬስተን ከቀኑ 6 ሰዓት ሲሆን ፍፁም ጨለማ ሆኖ ነበር፤ ጨለማ የምለው ወይም ታሪኩ የሚያወራው የኤክሊፕስ (የጨረቃ ግርዶሽ) አጨላለም አይደለም፤ ከተፈጥሮ ሕግጋት ውጪ የሆነ ጨለማ ነው።

በፕሬስተን የደረሰውን ጨለማ የዘመኑ ጋዜጦች ሲያወሩት «.......ሰማዩ ወደ ጥቁርነት ተለወጠ፤ ከዳር እስከ ዳር ጥቁር መጋረጃ ያለበሰው መሰለ፤ ሕዝቡ በየመንገዱ ላይ ቆሞ ይጨነቃል፤ እንስሳት ወደየቤታቸው ለመተኛት ይጓዛሉ፤ ሌሎች ሰዎች ደግሞ ለጸሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን አመሩ፤ እውነተኛው ጨለማ፤ እምጥቶ እስኪመሻሽ ድረስ አዲሱ ጨለማ እንዳለ ቆይቶ ሲመሻሽሽ ፈገገ.......» ብለዋል።

በ1889 ዓ.ም ሚያዝያ 2 ቀን በሜኒሶታ ውስጥ በአይትኬን ቀኑ ወደ ጨለማነት ተለውጦ ነበር፤ በ1763 ዓ.ም ነሐሴ 19 ቀን ጧት ወደ ረፋዱ ገደማ ለንደን ከተማ በሙሉ በጨለማ ተወርሶ ነበር፤ ለጥቂት ጊዜ የለንደን ከተማ ሕዝብ በመብራት ከቆየ በኋላ ተመልሶ ብርሃን ሆንዋል፤ በዚያን ቀን ኤክሊፕስ እንዳልነበረ የለንደን ሊቃውንት መግለጫ አውጥተዋል።

በ1886 ዓ.ም መጋቢት 19 ቀን በዊስኮንሲ ውስጥ ኦሽኮሽ ከተማ በጨለማ ተውጣ ነበር፤ ከቀኑ በዘጠኝ ሰዓት ጨልሞ ሕዝቡ መብራት ካበራ በኋላ የቀኑ ብርሃን ተመልሷል፤ ይህ አጨላለም ለአሥር ደቂቃ ያህል የቆየ ቢሆንም የአገሩ ሊቃውንት ባወጡት መግለጫ «.......ከባድ የሆነ ደመና ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ይጓዝ ስለነአብረ በከተማዋ ላይ ባለፈበት ጊዜ ከተማዋን ሊያጨልማት ቻሉ......» ብለዋል።

በ1904 ዓ.ም ታኅሣሥ 2 ቀን በቴኔሲ ውስጥ ሜምፊስ በተባለው ከተማ ከጧቱ በአራት ሰዓት ጨለማ ደርሶ ነበር፤ ለ15 ደቂቃዎች በጨለመው በዚህ የጨለማ ጊዜ ሴቶችና ሕፃናት በመጯጯህ ከተማዋን ረብሸዋት እንደ ነበረ የዘመኑ ጋዜጦች አውርተዋል።

በ1950 ዓ.ም በመስከረም ወር በአሜሪካ አገር የፀሐይዋ መልክ ወደ ሰማያዊ አረንጓዴ ተለውጦ ያበራ እንደነበረ ሰሞኑን በጋዜጦች ሲወራ ከርሟል፤ ይህም ብርሃን ለስምንት ቀን ያህል ቆይቶ መስከረም 24 ቀን ደንበኛው ብርሃን ተመልስዋል።

በዚያው ዘመን መስከረም 26 ቀን በእስኮትላንድ በእንግሊዝ አገር ፀሐይ ሰማያዊ አረንጓዴ መስላ ትታያለች፤ በዚያው ቀን የደንማርክ ጋዜጦች እንደ ጻፉት ፀሐይዋ ሰማያዊ መልክ ነበራት፤ የምፅዐት ጊዜ መሆኑንም ጋዜጦች

ጽፈው ነበር። ይህ ጨለማ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚለው ጥያቄ የሊቃውንትም ጥያቄ ነው፤ መልሱ ከተመራማሪ ሊቃውንት ገና በመጠበቅ ነው።

ጀርመን ውስጥ በሽለስዊግ የሚኖሩ ሴቶች ለጋብቻ መድረሳቸውን የሚያስመሰክሩት በረጅም ዘንግ ወንዝ በመዝለል ነው።

በሕንድ አገር በኩርግ ነዋሪ የነበረችው ወይዝሮ ዴዋ አማጂ ባልዋ ቢሞቱባት ባልዋን ለመከተል ብላ ጌጥዋ የነበረውን አልማዝ ፈጭታ በመዋጥ ሞተች።

በ1854 ዓ.ም የሐዋይ ንጉሥ የነበሩት ሳልሳዊ ካሜሃሜ ሊሞቱ በአልጋቸው ላይ ሆነው ሲያጣጥሩ ዙፋናቸውን የሚወርሰው ሰው እንዲመርጡ ተጠየቁ። ንጉሡም ከታላላቅ ቤተሰብ የምትወለደዋን በርኒስ ፓውሂ ዙፋኔን ትውረስ ብለው ተናዘዙ፤ በርኒስ ግን «ንግሥት መሆን ፈጽሜ አልፈልግም» ብላ ውርሱን አልቀበልም አለች።

በአውስትሪያ ውስጥ ካፕፌንገር በተባለው ከተማ ውስጥ ያሉ ሕንፃዎች በሙሉ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በቦምብ ተደብድበው ሲጠፉ በከተማዋ ያለ አንድ ቤተ መቅደስ ብቻ ምንም ጉዳት ሳያገኘው ተርፏል።

በአፍሪካ ውስጥ በኡጋንዳ ይኖሩ የነበሩት ካፒቴን ሳማኪ ሳልሞን በሰላሳ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ አራት ሺህ ዝሆን ገድለዋል።

የኮሪያ ሙሽሮች በሙሽርነታቸው ቀን ዕውር እና ዲዳ መለው ይታያሉ በ1400 ዓ.ም ከአምስት እምቶ ዓመት በፊት ንጉሥ ሄታይ ጆንግ ዲዳና ዕውር ስለወለደ ሴቶች ልጆች ሁሉ በደስታቸው ቀን በሠርጋቸው ዕለት ዕውርና ዲዳ መስለው እንዲታዩ ስላዘዘ ነው።

በአፍሪካ ውስጥ የማየሃ ጎሳ ሰዎች የሚገበያዩት በድንጋይ ነበር፤ ድንጋዩ ጉጡ ብዛት ዋጋው ከፍ ይላል።

በ1815 ዓ.ም ተወልዶ በ1871 ዓ.ም ሞተው ሔንሪ ሐርት በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ሲኖር በሰላሳ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሺ ሁለት መቶ ዝሆን ገድሏል።

በእንግሊዝ አገር በሎንግንር ይኖሩ የነበሩት ዊልያም ቢሊንግ የተወለዱት እርሻ ውስጥ ነበር። 112 ዓመት ኖረው ሞተው የተገኙት እርሻ ውስጥ ነው።

በሕንድ የሚኖሩ የዙቱሂሊ ሰዎች የጋብቻ ፍጥምጥም ሲያደርጉ ወንዱ በማሰሮ የተሞላ ውሃ በሴቲቱ ራስ ላይ በመስብር ነው።

በአፍሪካ ውስጥ የንጋታ ጎሳ ሰዎች የሚቀበሩት ከእንጨት ተጠርቦ ቀጥ ብሎ በሚቆም ሳጥን ውስጥ ነው።

በአሜሪካ አገር በቺካጎ ይኖሩ የነበሩት ወይዘሮ ኤሊኖር አርም ስባይ በአራት ዓመት 11 ልጆች ወልደዋል ሁለት ጊዜ መንታ አንድ ጊዜ 3 አንድ ጊዜ ደግሞ አራት ልጆች በመውለድ ነው።

በዩጎዝላቪያ ውስጥ ስዋቢያን በሚባለው ቀበሌ የሚኖሩ ልጃገረዶች እሑድ እሑድ ከሰዓት በኋላ የጋብቻ ወንበር በሚባለው አግዳሚ ወንበር ላይ መደዳውን ይቀመጣሉ። የመንደሩ ጎረምሳ ይመጣና ከተደረደሩት ውስጥ መርጦ የምትስማማውን ለሚስትነት ያጫል። ካጣም ለሌላ እሑድ ይመለሳል።

ፔድሮ ካን ዲዮቲ የተባለ ዋናተኛ መጋቢት 11 ቀን 1931 ዓ.ም ፓራና በሚባለው ወንዝ ለመዋኘት ገብቶ ከሳንታፌ እስከ ቦነስ አይረስ ድረስ ያለውን 336 ኪሎ ሜትር ርቀት ያለውን በዋና ሄደዋል። ይህን ርቀት የተጓዘው በ71 ሰዓት ከ55 ደቂቃ ነው።

አምሳ እግር የምንለው ትል ሁለት ሺ ጡንቻዎች አሉት በጡንቻዎች ብዛት ከሰው 4 ጊዜ ያህል ይበልጣል፤ ሰው 510 ጡንቻዎች አሉት።

በሕንድ አገር እይጎንድ ጎሳ ሰዎች እንዲበሉ የሚፈቀድላቸው በቀን አንድ ኪሎ ሩዝ ነው፤ የሚጠጡትም ሩዙ የተቀቀለበትን ውሃ ነው።

በአፍሪካ ውስጥ በሩዋንዳ ይነግሱ የነበሩ ንጉሦች በዙፋናቸው ላይ መቆየት የሚችሉት ወላጅ እናታቸው እስካለች ድረስ ነው። መልካም ምክር ትመክራለች ብለው የሚያስቧት የንጉሡ እናት ከሞተች ንጉሡ ከዙፋኑ ይወርድ ነበር።

በሕንድ አገር የላዳክ ሴቶች ጠጉራቸውን የሚሠሩት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። በመከር ወራት ሰብል ከተሰበሰበ በኋላ ይሠሩትና 12 ወር ሙሉ በማበጠሪያም አይነካም።

በ1832 ዓ.ም ተወልዶ 1914 ዓ.ም የሞተው የታወቀው ተራራ ወጪ ሰር ፍራንሲስ ጆጆሴፍ ካምፕ ቤል 15771 ጫማ ከፍታ ያለውን ሞንት ብላክን፣ 13900 ጫማ ከፍታ ያለውን ኢገርን፣ 13645 ጫማ ከፍታ ያለውን ጀንግራውን፣ እና 14692 ጫማ ከፍታ ያለውን ማተርን ሆርን የተባሉትን ተራራዎች ሁሉ በመውጣቱ ዝነኛ ነበር። ዝነኛ ያስደረገው ዋናው ምክንያት ከተወለደ አራት ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ምንም ያማያይ ፍጹም ዕውር ስለ ነበር ነው።

በአፍሪካ በሴራሊዮን ውስጥ ታላቅና የተከብረ እንግዳ ተሸከመው የሚሄዱት በራሳቸው ላይ አድርገው ነው፤ ተሸካሚዎቹ ኩሊዎች የሆኑ እንደሆነ ብዙ ገንዘብ የሚከፍላቸውን መቀምጫውን ራሳቸው ላይ አድርገው ያጉዙታል፤ አነስተኛ ገንዘብ ከከፈለ የመቀመጫውን አግዳሚ እንጨጥ የሚይዙት ትከሻቸው ላይ ነው። እይሰውየውን ምንነትም መንገደኛው ሁሉ በኩሊዎቹ አሸካከም ለይቶ ያውቃል።

በአፍሪካ ጋምቢያ ውስጥ አብማሩ የሚባሉት ዝናብ የሚያዝንቡ ሰዎች ከፊታቸው አነስተኛ ከረቦ ያደርጉና በዚያ በጉልበታቸው እየነኩ በመነሳት ዝናብ እስቲዘንብ ድረስ ይህንኑ ዝላይ ይቀጥላሉ ሊቃውንት እንደ አጠኑት በየ8 ሴኮንድ አንድ ጊዜ ይዘላሉ ጠቅላላ 18 ሰዓት ስለሚቆዩ አሥራ ሰባት ሺህ ጊዜ እንደሚዘሉ ታውቋል።

የሎምባርዲያው ንጉሥ ሚስት የነበሩት ንግሥት ሮሳሞንድ ባላቸውን ንጉሥ አልቢይንን መርዝ አጠጥተው በ573 ዓ.ም ገድለዋቸው፤ እንደ ገና ሌላ ባል አግብተው ከቆዩ በኋላ ይህንንም ሁለተኛውን ባላቸውን መርዝ አጠጥተው ለመግደል መርዙን ሲሰጧቸው ባልዮው ግማሹን ዋንጫ ሚስቲቱ እንዲጠጡ አስገድደው አጠጡዋቸው ጥቂት ቆይተው ሁለቱም እኩል አብረው ሞቱ።

በ1844 ዓ.ም ተወልዶ በ1914 ዓ.ም የሞተው ዝነኛው ፈረንሳዊ ስዕል ሳይና የስዕል ጥበብ መምህር የነበረው ረኔ ፕሪንችት ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ዲዳና ደንቆሮ ነበር።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ የጃፓን ወታደሮች ማሊያን ለመያዝ ሲገሰግሱ ወንዞችን የሚሻገሩት የወታደሩ የመሐንዲስ ክፍል በልዩ ያሠለጠናቸው ወታደሮች ግንዲላዎችን እየተሸከሙ ድልድይ እየሆኑላቸው ነበር።

በሜይን ይኖር የነበረው ነጋዴው አቶ ጆሹአ ሆል ሁለት ጀልባዎ ነበሩት ሜዳውን በፈረሱ ይሄድና ከወንዙ ሲደርስ ሁለት ጀልባዎች አቆራኝቶ ሁለቱን የፈረሱን እግሮች በአንደኛው ጀልባ ላይ በማድረግ ጀልባዎቹን እየቀዘፈ ይሻገራል።

በአፍሪካ የሙሁቱ ጎሳ ሴቶች ጀርባቸውን በመነቀስ ልዩ ጌጥ ያበጃሉ። ይህንንም የሚያደርጉት አንዲት የፈረንጅ ሴት እንደዚያ ለብሳ የተነሳቸውን ፎቶ ግራፍ አይተው ነው።

በአውስትራሊያ ውስጥ አቶ አውስቲን ዋንግኔላ ያሳደጉት ኮርማ በግ በኢትዮጵያ ብር ሂሳብ አምሳ ሁለት ሺ አስምት መቶ ብር ተሽጧል።

በአፍሪካ ውስጥ በማሳኪን ቲዋል የሚኖሩ ሰዎች ሚስት ለማግባት የሚችሉት ወይም የሚፈቀድላቸው አምስት ጎጇዎች ከሠሩ በኋላ ነው፤ እነዚህም ጎጆዎች አንዱ ለመኝታ፤ ሁለተኛው ለምግብ መሥሪያ፤ ሦስተኛው ለእህል ማስቀመጫ አራተኛው ለጠላ መጥመቂያ ሦስተኛው ተዘግቶ ለመጠባበቂያ የሚሆኑ ናቸው።

በሰሃራ በረሃ ውስጥ ባለው ጋት በተባለው ከተማ የማሠሩትም ሆኑ የተሠሩት ቤቶች ያለ ጣሪያ ነው፤ ባጭሩ ቤቱ የመከደኛ ጣሪያ የለውም።

ስዋንስ በትምባለው ደሴት ላይ የሚኖሩ ገበሬዎች ጋሪያቸውን የሚያስቡት በሬና ፈረስ እያቀናጁ ነው።

አውስትራዊው ጆሃን ላንገር ለስልሳ ዓመታት ጊዜ ያህል በየቀኑ አሥራ ሦስት ሊትር ተኩል ቪኖ ይጠጡ ነበር፤ እኚህ ሰው በጠቅላላው የጠጡት

የወይን ጠጅ ብዛት 79300 ጋሎን ነው፤ ለሃያ ዓመት ያህል ታመው አልጋ ላይ ሲውሉ ከአልጋቸው አጠገብ ባለመዘውር መቅጃ ያለው በርሚል ተደርጎላቸው ሲያልቅ ወይን ጠጅ እየተሞላ ከዚያ እራሳቸው እየቀዱ ይጠጡ ነበር።

በ1957 ዓ.ም በእንግሊዝ አገር ከኳሮን እስከ ውድሐውስ ድረስ መስከረም 9 ቀን አንድ ፈረስ የስድስት ሺሊንግ ቴምብር ተለጥፎበት በፖስታ ቤት ተልኳል።

የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት አብርሃም ሊንከን ከመሞታቸው ሁለት ሳምንት በፊት መሞታቸውን በሕልማቸው አይተው ነበር፤ «ከፊት ለፊቴ ሬሳ ተጋድሟል፤ በዋይት ሐውስ ውስጥ የሞተው ማነው ብዬ ስጠይቅ ፕሬዝዳንቱ ነው፤ እሱም የሞተው በሰው እጅ ተገድሎ ነው ብለው እንደመለሱልኝ ደንግጬ ከንቅልፌ ነቃሁ» ብለው በሕልማቸው ያዩትን ለሰዎች አጫውተው ነበር።

በእንግሊዝ አገር በአስክሪግ ይኖሩ የነበሩት ልብስ ሰፊው አቶ ዴኒሳ አስሌ ወደ ሥራቸው ሲሄዱ በየቀኑ በሚስታቸው ላይ የቤታቸውን በር እየቆለፉባቸው ነበር። አንድም ቀን ሳያቋርጡ በዚህ ዓይነት ኑሮ ከሚስታቸው ጋር 52 ዓመት ሙሉ አብረው ኖረዋል።

በእግሊዝ አገር ግሪንስቴድ በተባለ ቦታ አንድ 970 ዓመት ዕድሜ ያለው ቤት አለ ቤቱ የተሠራው የቅዱስ አንድሪውስ ሬሳ ወደ ለንደን ከተማ ለመቀበር ሲጓዝ ለሬሳው ለአንዲት ቀን ማሳረፊያ ተብሎ ነው፤ ሬሳው አርፎበት ከተወሰደ በኋላ የቅዱስ አንድሪውስ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ እስካሁን ይሠራበታል።

# ሜሲ እና ክርስቲና

በ3ኛው አስደናቂ ታሪኮች መጽሐፍ እንዳነበቡት (አንብበውት ከሆነ) እንደ ቻንግና ኢንግ ሁሉ ሚሊ እና ክርስቲና ተጣብቀው የተወለዱ ናቸው። እነዚህ ልጆች በአሜሪካ አገር በኮሎምቦስ ውስጥ በሰሜን ካሮሊና ሐምሌ 11 ቀን 1851 ዓ.ም ተወለዱ። የእነዚህ ልጆች ወላጆች የአቶ ማክ ኮይ ባርያ ነበሩ፤ እናታቸው ወይዘሮ ሞኒሚያ ልጆቹን የወለደችው በ32 ዓመት ዕድሜዋ ነው።

እነዚህ ልጆች ተጣብቀው የተወለዱት በታችኛው ደንደሳቸው ክፍል ነው፤ በዚህ ምክንያት የሁለቱ ቂጥ በአንድነት የተያያዘ ነው፤ በቂጣቸው መጣበቅ ምክንያትም የጋራ የሆነ የሰገራ መውጫ እና የሽንት መሽኚያ ብልቶች አሉዋቸው፤ የተጣበቁት በትክክለኛይቱ ውደ ኋልዮች ሳይሆን አንደኛይቱ ወደ ግራዊ ትንሽ ዞር ያለች ስትሆን ሌላዋ ደግሞ ወደ ቀኝዋ ዞር ያለች ነች፤ ልቦቻቸው ለየብቻ ቢሆኑም ከተጣበቁበት ቦታ ላይ የደም መዘዋወሪያ ሥሮቻቸውና ነርቮቻቸው በአንድነት ይገናኛሉ፤ ይህ ባይሆን ኖሮ ሐኪሞች እንደ ተናገሩት ልጆቹን በሁለት እግሮችና በሁለት እጆች መለያየቱ ቀላል ነበር፤ በፎቶ ግራፉ ላይ እንደሚያዩዋቸው በስተግራም በኩል ያለችው ሚሊ ነች።

ሚሊና ክርስቲና እንደ ተወለዱ ከወላጆቻቸው ጋር አብረው ተሸጡ፤ የገዛው፤ እያተረፈ ሲሸጣቸው እንደ ገና የገዛቸው ደግሞ እያተረፈ ሲሸጣቸው በመጨረሻው ከወላጆቻቸው ተለይተው ለብቻቸው ተሸጡ፤ በዚህ ልጅ ሽያጭ መሠረት ሲገላበጡ በመቆየታቸው የትርፍ ትርፍ ጄ ፒ ስሚዝ የገዛቸው በዛሬው የኛ ብር ሂሳብ 60000 ብር ነበር፤ (ይህን ብር በድሮው የገንዘብ ውድነት ያስሉት) አቶ ስሚዝ ሩኅሩኅ ሰው ነበርና እነዚህን ሕፃናት ለብቻቸው ከገዛ በኋላ ወላጆቻቸውንም ከተሸጡበት ቦታ ገዝቶ ወላጆችና ልጆችን ባንድነት ማኖር ጀመረ። ጥቂት ከፍ እንዳሉም አቶ ስሚዝ እነዚህን ልጆች በኤግዚቢሽን መልክ ለሕዝብ እያሳየ ገንዘብ መሰብሰብ ጀመረ።

ተሰርቀው እንደ ገና መሸጣቸውን ባርያዎች ስለሆኑ ባርያ ባልሆኑ ሰዎች አካባቢ እየተዘዋወሩ እንዳይታዩ አሜሪካኖች ያደረጉትን ተቃውሞና ክስ፤

ከዚያም ወደ እንግሊዝ አገር የመሰደዳቸው ዝርዝር ታሪክ የሚጥምዎ ስላልመሰለኝ ወይም የሚያደክምዎ ስለመሰለኝ ትቼዋለሁ።

በእንግሊዝ አገር በ1855 ዓ.ም በተባበሩት አፍሪካውያን መንትዮች የሚል መጠሪያ ወጥቶላቸው በለንደን ከተማ ውስጥ ባለው በግብጻውያን አዳራሽ ለሕዝብ ይታዩ ጀመር።

በዚያው በእንግሊዝ አገር ዶክተር ኤች ኤፍ ራምስቦታም ልጆቹን መርምረው አንድ መግለጫ አወጡ፤ «......ልጆቹ በትክክል ጀርባ ለጀርባ ተጋጥመው አይቆሙም፤ ትንሽ ወደየጎናቸው ዘንበል ይላሉ፤ በዚህም ምክንያት አንደኛዋ እጆችዋን በአንደኛዋ አንገት ዙርያ ማድረግ ትችላለች፤ መሳሳምም ይችላሉ፤ ግን ጎን ለጎን መሄድ አይችሉም ሲተኙም አንደኛዋ በጀርባዋ ተንጋላ ስትተኛ አንደኛዋ በጐንዋ ትተኛለች፤ በአሻንጉሊቶቻቸው በአንድነት ይጫወታሉ፤ ብዙ ጊዜም ጭቅጭቅ አይታይባቸውም......» ብለዋል።

በእንግሊዝ አገር በቆዩበት ጊዜ ከንግሥት ቪክቶሪያ ጋር ተገናኝተው ተሸልመዋል፤ በዚያው በእንግሊዝ አገርም ማንበብና መጻፍ ተማሩ፤ መጻፍና ማንበብ ብቻ ሳይሆን ዜማ ማዜምና መጨፈርም ተማሩ፤ ይህም ለሕዝብ ለሚያሳዩት ዝግጅት ሙሉ አደረጋቸው።

በአሜሪካ አገር የተነሳው የርስ በርስ ጦርነት ተፈፀመ፤ ባርያዎች ነፃ ወጡ፤ ሚሊና ክርስቲናም በነፃነት በየትም ቦታ ለመኖር ነፃ ሆኑ፤ የሳምንት ገቢያቸውም ከፍ አለ፤ እስከ ሺ ሁለት መቶ ብር በየሳምንቱ ገቢ ያገኙ ጀመር። በሚያደርጉት ከቦታ ቦታ ጉዞም ያስደስታቸው ጀመር፤ ለሕዝብ የሚያሳዩትንም ትርኢት እያሻሻሉ በመሔዳቸው እንደ ተጣበቁ የገመድ ዝላይ (ጢብጢብ) ያሳዩ ጀመሩ በሚዘሩበት ወይም በሚዘፍኑበት ጊዜ የድምፃቸው ጥሩነት ተመልካችን ይስብ ጀመር። እንዲያውም «ሁለት ራስ ያላቸው የሌሊት ወፎች» የሚል ቅጥል ስም ተሰጥቷቸው ነበር።

እነዚህ ልጆች ዘፈን የሚዘፍኑት በጊታር እየታጀቡ ነው፤ የሚገጥሙትም ግጥም ተወዳጅ ነበር፤ አሁን ድምፃቸውን መስማት ባይቻልም የሚዘፍኑበትን ግጥም ላስነብብዎ፤ ግጥሙን በአማርኛም እንዲገጥም አድርጌው ነበር፤ ግን አልፎ አልፎ ቤት ለማስመታት ሌላ ቃላት ስለገቡበት ደስ አልልህ አለኝና

ግጥሙን ትቼ በእንግሊዝኛ የሚገጥመውን ግጥም በአማርኛ ጥሬ ትርጉሙን አቀረብኩት፤ ቤት አይምታ እንጂ ትክክለኛ አባባሉ ይሔ ነው።

በግል ለብቻ መናገር አይጠቅምም፤
በነፃነት መናገር ያስፈልጋል፤
ሁሉን ነገር በነፃነት እናገራለሁ፤
ለሚገረሙ (ለሚደነቁ) ሰዎች።
2 ራስ፤ 4 እጆች 4 እግሮች፤
ሁሉም በአንድ ትክክለኛ አካል ተገናኝተዋል፤
አስገራሚ ፍጡር ነኝ፤
የሳይንስ አዋቂዎች ሁሉ ብለውታል፤
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እንደኔ የለም፤
ወደ ፊትም አይኖርም ይሆናል፤
አስገራሚ ፍጡር ነኝ፤
እያለፉ ለሚያዩኝ ሁሉ።
በጣም ደስተኛ ነኝ፤ ምክንያቱም ጤነኛ ነኝ፤
መድኃኔ ዓለምንና እግዚአብሔርን እወዳለሁ፤
እግዚአብሔር የፈጠረውን ነገር ሁሉ እወዳለሁ፤
ምንም እንኳ 1 ወይም 2 ሆኜ ብፈጠርም።

እነዚህ ልጆች የአሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ ሲኖራቸው በ1866 ዓ.ም አንድ ተመልካች ስለ ልጆቹ ሲጽፍ «......በመልካም ጤንነት ላይ ናቸው፤ ክብደታቸው 159 ፓውንድ ተኩል ነው፤...... ጨዋና ተጨዋቾች ናቸው፤ ማንበብ ይወዳሉ፤..... በሚሄዱበት ወይም በሚሮጡበት ጊዜ የመሐል እግሮቻቸውን እኩል ያነሳሉ፤ አንዷ የግራዋን ሲሆን ሌላዋ የቀኝዋን እግር

ማለት ነው፤……. የመሐል እግሮቻቸው ከዳርኛዎቹ እግሮቻቸው አጠር ይላሉ ለምሳሌ በወለል ላይ ቀጥ ብለው በሚቆሙበት ጊዜ የእያንዳንዳቸው የመሐል እግሮቻቸው ወለሉን ለቀው ተንጠልጥለው ይታያሉ፤….. ከሚሊ ይልቅ ክሪስቲና ጠንካራና ትልቅ ናት፤ ክርስቲና ቆማ ሚሊን ማንሳት ትችላለች፤ አንስታ መሄድና መሮትም ትችላለች፤ ሚሊ ግን እንዲህ ማድረግ አትችልም…….» ብለዋል።

በአውሮፓ በአሜሪካ ትርኢት ሲያሳዩ ኖሩ፤ በ1900 ዓ.ም ሚሊና ክርስቲና ከአሥራ አራት እህትና ወንድሞቻቸው ጋር በአሜሪካ አገር በኮሎምቦስ መኖርን ጀመሩ፤ ሚሊ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የሳምባ በሽታ ይዟት ስለ ነበር በዚሁ ጠንቅ ጥቅምት 9 ቀን 1912 ዓ.ም ዓመቷ ሞተች፤ ክርስቲናም ከእህቷ ሞት በኋላ እንደምትሞት አወቀችው፤ ከ17 ሰዓታት በኋላም ሞተች።

ተጣብቀው የተወለዱ ብዙ ሰዎች አሉ፤ ግማሾቹ በሐኪሞች ጥበብ መለያየት ሲችሉ አንዳንዶቹም ለመለያየት ፈፅመው የማይችሉ ናቸው፤ በቆዳ ወይም በለስላሳ አጥንት (ካርትሌጅ፤ ጆሮና አፍንጫ የሚፈጠሩበት ዓይነት) ወይም በሥጋ ብቻ ወይም በራስ አጥንት ብቻ ወይም በደረት አጥንት ብቻ ወይም በእግር ወይም በእጅ ወይም በጭን ተጣብቀው የተወለዱ ልጆች ሲያጋጥሙ በኦፐሬሽን መለያየቱ ለሐኪሞች ቀላል ነው ግን በደም መዘዋወር በአንጎልና በሆድ ዕቃ ግንኙነት ያላቸውን ተጣባቂዎች ለማለያየት ያስቸግራል።

የተጣበቁ ልጆች በዓለም ላይ በብዛት ይወለዳሉ፤ ከጥቂት ዓመታት በፊት በቦስተን የጤና ምክትል ኮሚሽነር የሆኑት ዶክተር ፍሬድሪክ ጀ ባሌይ ባወጡት መግለጫ ላይ በአሜሪካ አገር ብቻ በ250000 አወላለድ ውስጥ አንድ የተጣበቀ አወላለድ እንደሚገኝ ገልጸው ነበር። የጥንት የግሪክ የሕክምና ሊቃውንትም የተጣበቁ ሰዎች ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምሮ ይወለዱ እንደ ነበር ጽፈዋል።

በ1530 ዓ.ም የተወለዱት ፈረንሳዊው ኤድሞንድ አውገር በፈረንሳዮች የርስ በርስ ጦርነት ጊዜ እንዲሰቀሉ ተፈረደባቸው። ከመሰቀያው ቦታ ደርሰው የመጨረሻው ቃላቸውን እንዲናገሩ ተጠይቀው ሲናገሩ፤ የመስቀያው እንጨት

ካለበት ሰገእንት ላይ ለመውጫቸው በተዘጋጀው መሰላል ላይ እየተራመዱ በመውጣት ስለተናገሩ የያዙዋቸው ሰዎች አድንቀው ምሕረት አደረጉላቸውና በሰላም ስልሳ አንድ ዓመት ኖረው በ1591 ዓ.ም በሕመም ሞቱ።

«ጎን ዊዝ ዘ ዊንድ» የተባለው መጽሐፍ ለውራኖች ተብሎ በብሬል ቢጻፍ ሰላሳ ቮሊውም (መጽሐፍ) ወጣው። የዚህ መጽሐፍ ታሪክ በፊልም ተቀርጾ በአዲስ አበባ ከተማ ባሉ ሲኒማ ቤቶች እየተደጋገመ ታይቷል። ይህ መጽሐፍ በዓለም ላይ በብዛት የተሸጠ በመሆኑ ታሪከኛ መጽሐፍ ነው።

በፈረንሳይ አገር የኢስሌ ወይዛዝርቶች ተቀምጠው የሚሄዱባቸው አህያዎች ሱሪ የሚታጠቁ ነበሩ።

ክብሪት እንደተፈለሰፈ ጊዜ የክብሪት ማስቀመጫ ሳጥን በጫማ ፎርም ሆኖ ከእንጨት የሚሠራ ነበር።

በስፔይን ውስጥ በአንዳንድ ቦታዎች ሰዎች የዘመዶቻቸውን የመቃብር ግብር አልከፍል ሲሉ አጽሙ ይወጣና ቅልጥሞቹን ማገር ጭንቅላቶቹን ጌጥ እያደረጉ እንደ አጥር ይሰሩታል።

በሜክሲኮ ውስጥ ያሉ ሕንዶች እስከ አሁን ድረስ በየዓመቱ በሰኔ ወር ከተራራውላይ ወጥተው ዘብ በመቆም የንጉሥ ዳግማዊ ሜንቴዙማይ የጥንቱ የሜክሲኮ ንጉሥ ይመጣሉ እያሉ ይጠብቃሉ ንጉሡ ከሞቱ 448 ዓመት አልፏል።

በኒጄሪያ የሚገኙ የፉላኒ ጎሳ ሰዎች አንድ ሰው ሚስት በሚያገባበት ጊዜ ተሞሽሮ ሳለ ከሰው ደረጃ መድረሱን ለማረጋገጥ በጨፈቃ ይደበደብና ከዚያ በኋላ ጋብቻው ይፈቀድለታል።

በቱርክ ውስጥ ኡቺሳ በምትባል መንደር የሚኖሩ ልጃገረዶች በግንባራቸው ላይ ከብርና ከወርቅ የሚሠሩ ቤሳዎችን ያደርጋሉ፤ የጌጡ ብዛትና ዓይነትም የወላጆቻቸውን ሀብት የሚመሰክር ነው።

በ1754 ዓ.ም ተወልደው በ1801 ዓ.ም የሞቱት የሩሲያው ንጉሥ ቀዳማዊ ጳውሎስ በአፍንጫቸው ደፍጣጣነትና በራሳቸው መላጣነት ያፍሩበትና ይቆጩበት ነበር። በዚህ ምክንያት ማንም ሰው ማንንም አንተ

አፍንጫ ደፍጣጣ ወይም አንተ መላጣ ብሎ ቢሳደብ በሞት እንዲቀጣ የሚል ሕግ አውጥተው ነበር፤ እሳቸው ግን መላጣቸው እንዳይታይ ሰው ሠራሽ ጠጉር ያደርጉበት ነበር።

በ1823 ዓ.ም ተወልደው በ1912 ዓ.ም የሞቱት ፈረንሳዊው ፍራንኮስ ሩሲሌ በየቀኑ ያለማቋረጥ አንድ ሊትር ተኩል ኮኛክ ይጠጡ ነበር፤ 69 ዓመት ሙሉ ያለማቋረጥ የጠጡት ኮኛክ 12500 ጋሎን ነው ይህ ሆኖ እኚህ ሰው ዕድሜ ጠግበው በተወለዱ 89 ዓመታቸው ሞቱ።

እስከ 1785 ዓ.ም ድረስ ይሰፉ የነበሩት ጫማዎች ሁሉ የግራና የቀኙ እግር ተለይቶ አይሰፉም ነበር።

በአርጀንቲና ውስጥ የፓምፓስ ገበሬዎች ያላቸው ጋሪ እግሩ ብቻ አሥር ጫማ ርዝመት ያለው ነው።

በገመድ ላይ ተጓዥ የነበሩት ፈረንሳዊው ብሎንዲን በ1859 ዓ.ም ነሐሴ 17 ቀን ሔንሪ ኮልኮርድ የተባለው አዝለው የኒያግራን ወንዝ በነጠላ ገመድ ላይ እየተራመዱ ተሻግረዋል ገመዱ በወንዙ ማዶና ማዶ ታስሮ ነው።

በ1766 ዓ.ም በአልጄሪያ፤ ውስጥ የንጉሥ ምርጫ ሲደረግ መሐመድ ቤን ኡስማን እንዲነግሱ ተብለው ተመረጡ፤ መልእክተኞች መሐመድ ቤን ኡስማን እንዲያመጡ እና እያዲያነግሱ ተላኩ። መልእክተኞቹ ተሳስተው በስመ ሞክሼ ሌላውን መሐመድ ቤን ኡስማን አምጥው አነገሡ፤ እኚህ ንጉሥ ሃያ አምስት ዓመት ሙሉ ነግሠው በ1791 ዓ.ም ሞቱ፤ በአልጄሪያ ታሪክ ውስጥ ከእኚህ ሰው እኩል ረጅም ዘመን የነገሠ የለም።

በ935 ዓ.ም የሞቱት የቦሄሚያ ንጉሥ ዌንቼስላውስ ከሞቱ ሺ ዓመታት በኋላ የቼኮዝሎቫኪያ ሰዎች ዘውድ ጭነው ጭነውላቸዋል።

በ1506ን ዓ.ም ተወልደው በ1599 የሞቱት የታወቁት ታላቁ የሂሳብ ሊቅ ኒኮሎ ፋንታና ገና የስድስት ዓመት ልጅ ሆነው የሂሳብ ሥራቸውን ይሠሩ የነበሩት በየመቃብሩ ቦታ እየተዘዋወሩ በመቃብር ሕንፃዎች ላይ በመጻፍ ነበር።

በናይጄሪያ ውስጥ ሙሪ የሚኖሩት የኩዌይላ ጎሳ የሆኑት አቶ ሶድኮ በአንድ እግራቸው ብቻ በመቆም ስምንት ሰዓት ሙሉ ደንሰዋል፤ በዚህ የስምንት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ወደ ላይ ያነሱት እግራቸው ለአንዲት ሴኮንድ ጊዜ እንኳ ወደ መሬት ተመልሶ እረፍት አላደረጉም።

በአፍሪካ ውስጥ በጋምቢያ ያሉ የማንዲንጎ ጎሳ ሰዎች አውሬ የሚያድኑት ወይም ጎሽ ከነሕይወቱ የሚይዙት መሣሪያ ይዘው ሳይሆን የሚሄዱት ዋሽንት ብቻ ነው፤ አዳኞቹ ከዛፍ ጥግ ይሆኑና አውሬው የሚጠላውን የሙዚቃ ዓይነት ሲያሰሙ ጎሹ ይመጣና ሙዚቀኛውን ለመውጋት በማለት ዛፉን እየደጋገመ ሲወጋው ይደክመውና ይወድቃል፤ ከዚያ በኋላ አዳኙ ጎሹን ከነሕይወቱ ይይዘዋል።

የአይረሹ ነጋዴ አቶ ሺ ለንግድ ሥራ ስፔይን ውስጥ ወዳለው ወደ ካዲዝ ሔደ፤ በዚያ ሜሪ ስቶፐስን የምትባለዋን ሴት አይቶ በቁንጅናዋ ተደነቀ፤ በፍቅርዋም ስለተያዘ እንድታገባው ጠየቃት ሜሪም «ጊዜ ስጠኝና ላስብበት» አለችው። አቶ ሺ ውሳኔዋን ሳይጠብቅ አሳፎኖ በመርከብ ጭኖ ወዳገሩ ያጉዛት ጀመር ሜሪም ራስዋን የገኘችው በባህር ላይ በሚንሳፈፍ መርከብ ላይ ሆኖ ነው። በመርከቡ ጉዞውን ቀጥሎ ከመሐል መንገድ እንደደረሰ የመርከብ ዘራፊ ሌቦች በሌላ መርከብ ደርሰው እነሜሪ ያሉበት መርከብ ተዘረፈ። ዘራፊዎቹ በመርከቡ ላይ ካሉት ሰዎች በሕይወት የተረፉትን ማርከው ከሞሮኮ ወስደው በባርነት ሸጡዋቸው። ከእነኚህ ከተሸጡት ሰዎች መሐል ሜሪም አለችበት። በሞሮኮ የሜሪ ቁንጅና ሲወራ ወሬው ከሡልጣን ሲዲ መሐመድ ዘንድ ደረሰ፤ ሡልጣኑ ከቤተ መንግሥታቸው ከሜክኔስ ውስጥ ሜሪን አስጠርተው ሲመለከቱ በቁንጅናዋ ተደንቀው ሚስት አደረጉዋት፤ ያቺ ባርያ ሆና የተሸጠች ሴት የሞሮኮ ንግሥት ተብላ ከ1760 ዓ.ም እስከ 1790 ድረስ 30 ዓመት ሙሉ በንግሥትነት ኖረች።

በ1754 ዓ.ም ተወልደው በ1826 ዓ.ም የሞቱት ካፒቴን ጆን ዱግቲ በ1784 ዓ.ም የአሜሪካ የጦር ኃይል አዛዥ ብዛት ሰማንያ ሰዎች ብቻ ያሉት ነበር።

በጊንያ የሚገኝ ኩራስ የሚሉት አሣ ለሊቱን የሚያሳልፈው በደረቅ መሬት ላይ በመተኛት ነው።

ፕሬዝደንት አብርሃም ሊንከን በእንግሊዝኛ አጻጻፍ አንድ ታሪክ አላቸው

T home የአባታቸው ስም

N ancy የእናታቸው ስም

E Lizabeth የእህታቸው ስም

D ennis የጓደኛቸው ስም

I LLinois የአገራቸው ስም

S aqah የእንጀራ እናታቸው ስም

E mancipastor ቅጥል ስማቸው

R obert ትልቁ ልጃቸው

P ostmaster የመጀመሪያ ሥራቸው

በዚህ በዳር በኩል ያሉት ፊደላት ሽቅብ ሲነበቡ ፕሬዝደንት ይሆናሉ።

በ950 ዓ.ም ተወልደው በ999 ዓ.ም የሞቱት በቱኒዝያ ውስጥ የካይርዋን ሡልጣን የነበሩት አቤል ቃሲም ማንሱር አንድ ሌባ ወይም ዘራፊ በሚያዝበት ጊዜ እንዲገደልና ሥጋውን ቤተሰቦቹ እንዲበሉት የሚል ደንብ አውጥተው ነበር።

በእንግሊዝ አገር ለኤግዚቢሽን ቀርቦ የነበረ አንድ ሸሚዝ ከውጭ ከቤት ግድግዳ ላይ ተሰቅሎ ለሕዝብ ሲታይ ሁለት ፎቅ ቤቶችን አልብሶ ነበር።

በ1787 ዓ.ም ተወልደው በ1867 ዓ.ም የሞቱት ማድሚዜል ጆርጅ በየምሽቱ ጠጉራቸውን የሚጠቀልሉት አንድ መቶ ፍራንክ በሆነ የገንዘብ ወረቀት ነው፤ በነጋታው የጠቀለሉበትን የወረቀት ገንዘብ ይጥሉትና ማንም ይወስደዋል፤ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር በወጣትነት ዕድሜያቸው ሲሠሩበት ቆይተው በመቸረሻው ቤሳ ቤቲን አጥተው አሥራ ስምንት አመት ሙሉ በድኅነት ማቀው ሞቱ።

ክሪቴ በምትባለው ደሴት ላይ የሚኖሩ ልጃገረዶች ከ3 ሺህ ዓመት በፊት ጀምረው አንድ የሚሠሩት ስፖርት አለ ኮርማ በሬ እየሮጠ ሲመጣ ፊት ለፊት ተጋጥመው ቀንዱን ይይዙትና ኮርማው ተናዶ ወደ ጀርባው እንዲጥላቸው ያደርጋሉ፤ ከዚያም በኮርማው ጀርባ ላይ ተንከባለው ምንም ሳይጎዱ ከመሬት ያርፋሉ።

የልጃገረድ ጉዳይ ከተነሳ በመሐከለኛው አፍሪካ ውስጥ የሚኖሩ የግራይ ጎሳ ሰዎች ሚስት ሲያገቡ ለሴቲቱ የጋብቻ ቀለበት የሚያስሩት የተጠመለለ ረጅም ሽቦ በክንድዋ ላይ ነው።

በአውስትራሊያ ውስጥ ባሳልዝበርግ ያለው ተንተሉስ የሚሉት ዋሻ በውስጡ ከልዩ ልዩ ድንጋዮች በተፈጥሮ የተሠሩ ምስሎች ስላሉ የዋሻው ግድግዳ በሙሉ በአበባ ወረቀት ያጌጠ ይመስላል።

በ1546 ዓ.ም ተወልደው 1612 ዓ.ም የሞቱት በጀርመን አገር የተቢንገን ዩኒቨርሲቲ ዲን የነበሩት እስቴፋን ገርላች አንድ ጊዜ ያነበቡትን ነገር ምንጊዜም ቢሆን አስታውሰው በትክክል መናገር ይችላሉ፤ ስማቸውን ሲጠይቋቸው ግን ስማቸው ይጠፋባቸዋል።

የፓፑንስ ሰዎች ሀብታነታቸውን ለመግለጽ የበሉዋቸው አሳማዎች ብዛት እንዲገልጽ የአሳማዎቹን ጭንቅላት በግቢያቸው ውስጥ ይሰቅላሉ።

በአውስትራሊያ ይኖሩ የነበሩት የአቶ ዊልተን ፈረስ በአንዲት ግንዲላ ቁራጭ ሚዛኑን ጠብቆ መቆም ይችል ነበር።

የሩሲያው ንጉሥ ትልቁ ጴጥሮስ ስዊድንን ሊወጉ ዘመቱ በዚያን ጊዜ የስዊድኑ ንጉሥ ቻርለስ ፲፪ኛ ታመው ስለ ነበር በአልጋ ላይ ሆነው በሃያ አራት ምርጥ ወታደሮቻቸው ታጅበው ወደ ጦርነቱ ቦታ ጉዞ ጀመሩ፤ ሐምሌ 8 ቀን 1709 ዓ.ም ሩሲውያን የተኮሡት መድፍ የስዊድኑ ንጉሥ በአልጋ ከሚጓዙበት ላይ ወድቆ 21 ወታደሮችን ሲገልድ ንጉሡ ግን ትንሽም ቡጥጫ ሳይነካቸው ማምለጥ ቻሉ።

በጀርመን አገር በሃሌ ዩኒቨርስቲ የቀዶ ጥገና ፕሮፌሰር የነበሩት ዶክተር ፍሬደሪክ ቴዎዶር ሜኬል በ1803 ዓ.ም ሲሞቱ ሬሳቸውን ለትምህርት ቤቱ

መማሪያ ስለሰጡ አጽማቸው ለመታሰቢያነት ተብሎ እስካሁን ድረስ ባለበት ሥፍራ እንደ ነበር ቆሞ አለ።

በሕንድ አገር ፓርዳን የሚባለው ጎሳ ሰዎች ሚስታቸው ጥፋት ስታጠፋ ወይም ሰነፍ ስትሆን ከበሬ ጋር ጠምደው እንድታርስ በማድረግ ይቀጡዋታል።

የንጉሥ አርዘር ሰይፍ ከሰማይ የወረደ ነው እየተባለ የተከበረ ነበር፤ ሰይፉ በትክክል ከሰማይ የወረደ ሳይሆን ከሰማይ ከወረደ ብረት የተሠራ ነው። ከሰማይ ስለሚወርደው ድንጋይና ብረት በ፪ኛው መጽሐፌ አንብበዋል?

# አሣነባሪ

በዓለም ላይ ካሉ ፍጥረትታ ሁሉ እንደ አሣ ነባሪ ትልቅ ፍጡር የለም፤ አሣ ነባሪን ትልቅነት በአንድ ምሳሌ ልንገርዎት፤ በአንድ ትልቅ ሰውና በአንዲት የድመት ግልገል መሐል እንዳለው ልዩነት ነው፤ ሰው እንደ አሣነባሪው ቢሆን የድመቱ ግልገል እንደ ሰው ይመስላል ማለት ነው፤ እንዲያውም እከዚህ ቀጥሎ ከግርጌ ያለው ስዕል ለአሣነባሪ ትልቅነት ደህና ማስረጃ ሊሆንዎት ይችላል አሣ ነባሪው ተጋድሞ ሳለ በአጠገቡ አውቶሞቢሏና ሰውየው ምን እንደሚያህሉ ያነፃፅሩት አንድ ጊዜ በመጋቢት ወር 1926 ዓ.ም እስኮትላድ ውስጥ በደቡብ ሽትላንድ የተጠመደው አሣ ነባሪ የቁመቱ ርዝመት 109 ጫማ ከአራት ኢንች ተሩብ ሆንዋል፤ ይህም ማለት 33 ሜትር ተሩብ ያህል ነው፤ የአንድ አሣ ነባሪ ክብደት 195 ቶን ወይም 195000 ኪሎ ይደርሳል አሣ ነባሪዋ እርጉዝ ከሆነች ክብደቷ 200000 ኪሎ እንደሚበልጥ ሊቃውንት ይናገራሉ።

ፈረንጆች ዌልቦን የሚሉት አሣ ነባሪ ዘር የሚጠመደውና የሚያዘው በውስጡ ያለውን ዘይት ለማውጣት ነው፤ ከውስጡ በሚገኘው ዘይትም ብዙ

ነገሮች መድኃኒት ጭምር ይቀመምበታል፤ ከዚያም ከአንዱ አሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ 30000 ኪሎ የሚመዝን ዘይት ይገኝበታል።

የዚህ የባለ ዘይቱ አሣ ነባሪ ዘር ከሌሎች አሣ ነባሪዎች የተለዩ ጥርሶች አሉት፤ በተለይ በታችኛው መንጋጋው ላይ ያሉት ጥርሶች ከምንም ፍጡር ጥርሶች ጋር የማይወዳደሩ ወይም የማይመሳሰሉ ናቸው፤ በአጭሩ ጥርሶቹ ምን እንደሚመስሉና ምንስ እንደሚያካክሉ ከግርጌ ያለውን ፎቶ ግራፍ ይመልከቱ፤ ሰው በአጠገቡ ቆሞ ጭቅጭቅ ያለ አግር የሚመስለው የአሣ ነባሪው ጥርስ ነው፤ በጠቅላላው የታችኛው መንጋጋው ነው።

አሣ ነባሪ ትልቅነቱ በክብደቱ ችምር እንጂ በቁመቱ ርዝማኔ ከሆነ ፈረጅች ጄሊ ፊሽ የሚሉት አሣ ይበልጠዋል፤ የዚህ አሣ ቁመት 120 ጫማ ይደርሳል፤ አሁን ወደ አሣ ነባሪያችን እንመለስ።

የአሣ ነባሪ ልጅ በጣም ታዳጊ ነው፤ በተወለደ ባመቱ አሥር ሺ ኪሎ ያህል ይመዝናል፤ በኛ አጠራር የሁሉም ስም አሣ ነባሪ በመሆኑ ተማሪን ወይም አንባቢን ሊያሳስት ይችላል። ታላላቆቹ እውቆች ሁለት ዓይነት ናቸው፤ አንዱ ዌል whale ሲባል ሌላው ደግሞ ሻርክ shark ይባላል እስካሁን ያወራሁት የዌልን ነው፤ በጠቅላላው ግን የአሣ ነባሪ ዘር 150 ዓይነት ነው፤

ዌል ጥጃ ሲወልድ ሻርክ ግን እንቁላል ነው የሚጥለው። እንቁላል ከሚጥሉ ፍጡሮች ሁሉ የሻርክን እንቁላል በትልቅነት የሚወዳደረው የለም። እንግዲህ የማወራልዎት ስለ ሻርክ ሳይሆን በዚህ ቦታ አሣ ነባሪ የምለው ዌሉን ነው

አንድ አሣ ነባሪ በአንድ ሰዓት 36 ኪሎ ሜትር እየዋኘ መሮጥ ይችላል። ሊቃውንት እንደሚሉት የ520 ፈረስ ጉልበት አለው።

አሣ ነአብሪ እንደ አሣ በውሃ ውስጥ የመተንፈሻ አካል የለውም፤ ከውሃ ውጭ ወጥቶ አየር ስቦ ከውሃው ውስጥ ይመለሳል፤ የአሣ ነባሪ አፍንጫ ከራሱ ላይ በመሆኑ አሣ ነባሪው ራሱን ብቻ ከውሃው ውስጥ ብቅ አድርጎ በቀላሉ አየር መሳብና ያመቀውን መጥፎ አየር ማስወጣት ይችላል፤ አሣ ነባሪው ከውሃ ውስጥ ሲገባ የአፍንጫው ቀዳዳ ይዘጋል፤

አንድ አሣ ነባሪ ከውሃ ወጪ ለአምስትና አሥር ደቂቃ ያህል አየር ሲስብ ይቆይና ይጠልቃል፤ ከውሃ ውስጥም እስከ አርባ ደቂቃ ያለ አዲስ የውጭ አየር መቆየት ይችላል፤ አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚሉት አንዴ ስቦ ይዞት በገባው አየር እስከ ሁለት ሰዓት ውስጥ መቆየት ይችላል። በእንዲህ ያለ ሁኔታ ቆይቶ ከውሃ ውስጥ ሲወጣ አምቆ ያቆየውን የተቃጠለ አየር በኃይል ተንፍሶ ሲያስወጣው እያፏጨ የሚውዘገዘገው አየር ውሃውን ስለሚበትን ሽቅብ የሚወጣው ውሃ የፏፏቴ ወይም ከጠባብ ቧንቧ ውስጥ ታፍኖ የሚለቀቀውን ውሃ ይመስላል። ይህም አድራጎት እየተመላለሰ ቀንና ለሊት የሚያደርገው ነው።

አሣ ነባሪ እንደሌላው ተራ አሣ ነባሪ በተራ ሁኔታ የሚጠመድ ወይም የሚያዝ አይደለም፤ ስለ አሣ ነባሪ አጠማመድ ጥቂት ፎቶ ግራፍ ላሳይዎት። ለዚሁ ለአሣ ነባሪ ማጥመጃ ወይም ማደኛ ተብሎ የሚሠራ ልዩ ጥይትና መተኮሻው አለ፤ አሣ ነባሪው ብቅ ሲል በመርከብ ላይ የተጠመደው ጥይት ይተኮስበታል፤ አሣ ነባሪው በጥይቱ ከተመታ ጥይቱ አሣ ነባሪው ውስጥ ጠልቆ ይገባል፤ ጥይቱ ብቻውን ተወርዋሪ ሳይሆን ከኋላው በኩል በጠንካራ ገመድ የታሠረ ነው፤ ጥይቱ አሣ ነባሪው ውስጥ ከገባ በኋላ በማጥመጃው መርከብ ላይ ባለው ልዩ መሣሪያ የጥይቱ ገመድ እየተጠቀለለ አሣ ነባሪው ይጎተታል፤ ከዚያም በታላላቅ መርከቦች እየተጫነ ወደ ወደብ ይወሰዳል፤ ዕንዚህ ሁለት ፎቶ ግራፎች የጥይቱን አተኳኮስ እንዴት አድርጎ እንደሚወጋው ያሳያሉ፤ ሌላው ደግሞ መጠነኛ ክብደት ያላቸው አሣ ነባሪዎች በዚህ አተኳኮስ ሁኔታ ከተያዙ በኋላ በታናናሽ መርከቦች እየተጎተቱ ወደ ታላቁ መርከብ ይወሰዳሉ፤ ከታላቁ መርከብ ዘንድ ሲደርሱም የታላቁ መርከብ ታችኛ በር ይከፈትና የሚያሙለጨልጨው ብረት ላይ በመርከቡ ልዩ መሣሪያ እየተጎተቱ ይጫናሉ፤ ከዚያ በኋላ ወደ ሚቆራረጥባቸው ኢንዱስትሪ ይወሰዳሉ።

~~~~~

በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በበገና ደርዳሪነቱ የታወቀው እንግሊዛዊው ጆን ፓሪ በቼከርስ ተጨዋችነቱ ዝነኛ ነበር በብዙ አገሮች እየተዘዋወረም ተጫውቷል፤ ግን ሲወለድ ጀምሮ ፍፁም እውር ነበር።
~~~~~

በኖርዌይ አንድ ርዝመቱ 55 ጫማ የሆነ ሐውልት አለ፤ ሐውልቱ ከአንድ ወጥ ድንጋይ የተሠራ ሲሆን በላዩ ላይ ከዚያው አንድ ድንጋይ የ121 ሰዎች ምስል ተቀርጾበታል።

የሱዳን ሴቶች የጋብቻ ቀለበታቸውን የሚያደርጉት አፍንጫቸው ላይ ነው።

በ1599 ዓ.ም በቤልጂግ ውስጥ ሲሞን እስቲቨን የተባለ ሰው በነፋስ ኃይል የምትሄድ አንዲት አውቶሞቢል ሠርቶ ነበር፤ ይቺ አውቶሞቢል ለሙከራ በወጣችበት ጊዜ ሃያ ስምንት መንገደኞችን ይዛ በሁለት ሰዓት ውስጥ 67 ኪሎ ሜትር ተኑብ ተጉዛለች፤ ይህን ሁሉ ጉዞ የተጓዘችው በነፋስ እየተገፋች ነው።

በፈረንሳይ አገር የታላቁ ሬቮሊሽናቸው ጊዜ ፎሬዝ በተባለ ሥፍራ የነበሩ ሰዎች ሬቮሊሽኑን ይቃወሙ ነበር። ተቃዋሚነታቸውን የሚገልጹት ጠጉራቸውን ተላጭተው ከፊት ለፊታቸው በሁለት በኩል ዘለላ ጠጉር በመተውና ዘለላዎቹን በጆሮግንዳቸው በኩል ቁልቁል በመልቀቅ ነበር።

ከ1574 ዓ.ም እስከ 1589 ዓ.ም ድረስ ፈረንሳይን ይገዙ የነበቱ ንግሥት ሉዊስ ልብሳቸውን ማንም ሰው እንዲያለብሳቸው ማንም ሰው ጠጉራቸውን እንዲያበጥርላቸው አይፈቅዱም ነበር። የሚያለብሷቸውም ሆኑ፤ ጠጉራቸውን የሚያበጥሩላቸው ባላቸው ንጉሥ ሔንሪይ ሣልሳዊ ነበሩ።

በፖላንድ ውስጥ ፒትሽን በተባለ ከተማ በ13ኛው ክፍለ ዘመን የተሠራ የከተማው ሕዝብ አዳራሽ ስምንት ጊዜ በእሳት ቃጠሎ ወድሞ ተመልሶ በነበረበት ፎርም ተሠርቷል። አገሪቱን የሚወሩ ጠላቶች አሥራ ኍልት ጊዜ ደምስሰው አጥፍተውት እንደገና እየተመለሰ አሥራ ሁለት ጊዜ ተሠርቷል።

በሴይሎን ውስጥ የፖሎናሩዋ መቅደስ የሚባል አለ፤ ቤቱ የተሠራው ከአፈር፤ ከሸክላ፤ ከተቃጠለ ሣር፤ ከህል ዘይትና ማር ባንድነት ተደበላልቆ ከተሠራ ጡብ ነው፤ መቅደሱ ከተሠራ ስድስት መቶ ዓመት ሆኖታል። የጡብ ሽታ እስከዛሬ ድረስ ያን የጥንት መአዛውን ያውዳል።

ቄስ አሮን ሌንባች በአሜሪካ አገር በኦሌይ ቫሌይ ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ቄስ ነበሩ። እኚህ ቄስ በአርባ ሰባት ዓመት የቅስና

አገልግሎታቸው ዘመን ውስጥ 7729 ሰዎች አጥምቀዋል፤ 2829 የጋብቻ ሥነ ሥርዓት አስፈጽመዋል፤ 4289 የቀብር ስነ ሥርዓት ላይ ተገኝተው ፍትሐት ፈትተዋል። ከአምስት ሺ በላይ በሚሆን በልዩ ልዩ የቅስና ተግባር ላይ ተካፋይ ሆነዋል።

በጀርመን አገር ግሌስተን በሚባለው ዩኒቨርስቲ ውስጥ አቶ ክሪስቲያን ቡሽ የተባሉ ሰው ይማሩ ነበር። እኒህ በ1871 ዓ.ም ገብተው በ1904 ዓ.ም ከዚያ ዩኒቨርስቲው ውስጥ 33 ዓመት ተምረዋል ማለት ነው። 33 ዓመት በዩኒቨርስቲው ተምረው ሲወጡ ትምህርታቸውን ጨርሰው ሳይመረቁ ነበር ለሰነፍ ተማሪ ጥሩ ማበረታቻ ነው።

ከ2600 ዓመታት በፊት የተቀበረ ነው ተብሎ የተገመተ አንድ ማሰሮ በኢጣልያ አገር ፔስተም በተባለ ቦታ ባለ ሰብተራን በሚባል ገዳም በቁፋሮ ተገኝቶ ነበር። ማሰሮው የተገኘው ብቻውን አልነበረም። ግማሽ ወገቡ ድረስ ማር ይዞ ነበር። በቻልስ ውስጥ ለስ ኢውክስ በተባለ ቀበሌ ያለው ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚቀደሰው።

በስዊዘርላንድ ቱን በተባለው ሐይቅ አጠገብ ገንተን የተባለች መንደር አለች። የመንደርዋ ነዋሪዎች ለከብቶቻቸው ውሃ የሚያጠጡትና ለእነሱም የሚቀዱት ከአንድ ዛፍ ወገብ ውጽጥ ከሚወጣ ውሃ ነው። የአገሬው ሰው ውሃው ከየት እንደሚመጣና እንዴትስ እንደሚወጣ አያውቁም። ታሪኩ ግን በዚያች አገር ከስልሳ ዓመት በፊት የቧንቧ ውሃ ሲገባ አንዱ ቧንቧ ከአንድ ዛፍ ጋር ታበተ። ዛፉ እየወፈረና እያደገ በሄደ ጊዜ ቧንቧውን ስለዋጠው ዛሬ የሚታየው የውሃው መውጫና ውሃው ብቻ ነው።

ከ2450 ዓመታት በፊት የፔርሺያ ንጉሥ ቀዳማዊ ኬሴርኬስ የግሪክን አገር ወርረው ነበር። ከድሉ በኋላ ንጉሡና ሠራዊታቸው ፈንጠዝያ ሲያደርጉ ድል የተመታው የግሪክ ሠራዊት እንዴት አድርጎ ንጉሡን ለመቋቋም እንደሚችል ሲያውጠነጥን ይህን የሰማች አንዲት ሲያና የተባለች የግሪክ ልጃገረድ በባሕር ውስጥ ለውስጥ ሂዳ የንጉሡ መርከብ መልሕቅ የተንጠለጠለበትን ገመድ በቢላዋ ገዝግዛ በጠሰች። ንጉሡ መሸሺያ እንዲያጡ ለማድረግ ብላ ነው።

በፓፓኦ ውስጥ ዋሮፕን የተባለ ጎሳ ሰዎች የቀን መቁጠሪያቸው ለሳምንት ብቻ የሚያገለግል ነው። በአንድ እንጨት ላይ ሰባት ቀዳዳ ይበጅበትና በላዩ ላይ አንድ ረዘም ያለ ዘንግ በመጀመሪያው ቀዳዳ ላይ ይደረጋል። ሰኞ ነው ማለት ነው። ሲነጋ ከጎኑ ቀዳዳ ላይ ዘንጉ ይሻገራል። እንዲህ እያለ ሳምንቱ ያልቃል።

በቻይና ውስጥ ያናን ፉ በተባለ ቀበሌ ይኖር የነበረው ይህ ቼን ኩአን የተባለ ሰው የቤተ መቅደስ መብራት አብሪ ነበር። በአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜው ጀምሮ በተለይ ሥራዬ ብሎ የያዘው ከባድ የሆነ የብረት ምድጃ በግራ እጁ ካንድ ላይ አንጠልጥሎ እሳት እያንቦገቦገበት የቅዳሴው ሥርዓት እስቲያልቅ ድረስ መቆየት ነበር። የእሳቱ ምድጃ የተንጠለጠለበት ሽቦ በየህ ክንድ ውስጥ በመንጠቆ ዓይነት ብረት በሥጋው ውስጥ የሚነካ ነበር። የዚህ ዓይነቱን ሥራ በአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜው የጀመረ እስከ ሰላሳ ስድስት ዓመት ዕድሜው ድረስ ያለ ማቋረጥ ለቤተ መቅደሱ አገልግሏል።

ከ1856 ዓ.ም እስከ 1870 ዓ.ም ድረስ በሕንድ አገር የባሮዳ ገዥ የነበሩት ካንዴራሮ የተለየ ታሪክ ያላቸው ሰው ነበሩ ርግቦቻቸውን ማጋባት ይወዱ ነበርና ነው በዓመት ሦስት ጊዜ ድግስ እየደገሱ ለአንድ ጊዜ ሁለት ርግቦች ማለት ሴትና ወንድ ይመረጡና በይፋ እንዲጋቡ ይደረጋል። የጋብቻው ሥነ ሥርዓት የሚከናወነው፤ ሙሽራዎቹ ርግቦች በወርቅና በአልማዝ ባጌጠ ዝሆን ላይ ይደረጉና በታላቅ ጭፈራና አጀብ ታጅበው በከተማው ውስጥ ዞረው ግብዣው ከተዘጋጀበት ቦታ ይሄዳሉ። በዚያም ገዥውና ታላላቅ መኳንንት ባሉበት ታላቅ ግብዣ ይደረግና የበዓሉ ፍጻሜ ይሆናል። ለአንድ ጊዜ የርግቦች ሠርግ የሚደረገው ወጪ በዛሬው በኛ ብር ሂሳብ ዘጠና ሰባት ሺ ብር ነው። እኚህ ሰው አርባ አራት ጊዜ ርግቦችን ድረው ለሠርጉ አራት ሚሊዮን ብር አውጥተዋል።

በሕንድ አገር ማድራስ አጠገብ ቪኑኮንዳ በተባለ ቀበሌ አንድ ቤተ መቅደስ አለ። ከቤተ መቅደሱ ራስጌ ካለው ተራራ ላይ ከዛሬ 225 ዓመታት በፊት ማለት በ1750 ዓ.ም አንድ ታላቅ ቋጥኝ ወርዶ አረፈበት። ድንጋዩ ወርዶ ያረፈበት ድንጋዩ ወርዶ ያረፈው ቤተ መቅደሱን ሊነካ በሚሊሜትር ርቀት ሲቀረው ጭንቅላትና ግርጌው ከሌሎች ድንጋዮች ጋር ተነካክቶ ቆመ። በቤተ መቅደሱ ጣርያና በድንጋዩ መሐል ያለው መለያየት የሚታየው ፀሐይ

በውስጡ ስታልፍ በሚታየው ብርሃን ነው። ሊቃውንቱ እንደገመቱት የዚያ ድንጋይ ክብድት 600 ኩንታል ይሆናል ድንጋዩ በወረደ ጊዜ ሰዎች ተሰብስበው በቤተ መቅደሱ ውስጥ ይጸልዩ ነበር። አሁንም ቢሆን ሰዎች እየተሰበሰቡ ይጸልያሉ። ከጸሎቱ አንደኛው «ይህን ድንጋይ አንጠልጥለህ ያስቀረህ አምላክ አወራረዱንም አሣምረው» እያሉ ነው።

በሕንድ አገር ርግብ የሚያገቡ ሰዎች አሉ። እነዚህ ርግብዋን በሚስትነት የሚያገቡ ሰዎች የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ናቸው። ሁለት ጊዜ ሚስት አግብተው ከፈቱ በኋላ ለሦስተኛ ጊዜ ሚስት ለማግባት ከፈለጉ ሰው ከማግባታቸው በፊት የእርግብ ሚስት ያገባሉ። በእነሱ እምነት መሠረት 3 ቁጥር ገደቢስ ነው ብለው ስለሚያምኑ ያን ገደቢስ ቁጥር ነው ብለው ስለሚያምኑ ያን ገደቢስ ቁጥር ለማለፍ ከሴት ርግብ ጋር ይጋባሉ። ከርግብዋ ጋር ጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ ርግብዋን ፈተው ሰው ያገባሉ።

በ1825 ዓ.ም ተወልደው በ1909 ዓ.ም የሞቱት ጀርመናዊው ባሮን ሄርማን ቮን ሚትናች በእኩለ ለሊት የሚያምኑ ነበሩ። ሚትናች የሚለው ስማቸው እኩለ ለሊት ማለት ነው። የተወለዱት እኩለ ለሊት ላይ ስለነበረ ነው። ራታቸውን የሚበሉት በእኩለ ለሊት ነው ቀን ሲሰራ የዋለውን ሥራ ከሹሞቻቸው ጋር የሚፈርሙት በእኩለ ለሊት ነው። የውሻቸው ስም እኩለ ለሊት ነው። የሁለት አሽከሮቻቸው ስም እኩለ ለሊት ነው። 118 ልጆች ክርስትና አንስተው የሁሉንም ስም እኩለ ለሊት ብለዋቸዋል። የእረፍት ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በኖርዌይ ውስጥ ባለችው ሚድናይት ሰን (እኩለ ለሊት) በተባለችው ቦታ ነው።

የፖርቱጋሉ ታላቁ የግጥም ደራሲ ሉዊዝ ቫዝ ደ ካሞይስ በ1524 ዓ.ም ትወእልዶ በ1580 ዓ.ም ሞትዋል። ዛሬ በፖርቱጋል ውስጥ ፓርቲክል በተባለ ቦታ የዚያ ታላቅ ገጣሚ መቃብር አለ። በዚያ መቃብር ውስጥ ሬሳ ስለልገባበት አሁን አጽም የለበትም። ያ ታላቅ ገጣሚም በዚያ መቃብር ውስጥ አልተቀበረም። ደራሲው የት እንደ ሞተ እና እንደ ተቀበረ ስለማይታወቅ ለመታሰቢያው ብለው መቃብሩን ሠርተው ገጣሚው ከሄደበት አገር ሁሉ ጥርኝ ጥርኝ አፈር ሰብሰበው በዚያ መቃብር ውስጥ አኖሩ። እንደሚሉት

«ከዚያ ከተሰበሰበው አፈር ውስጥ አፈር የሆነው የገጣሚያችን ሥጋ ሳይገኝበት አይቀርም» ብለን ነው ይላሉ።

አሜሪካዊ አቶ ማክ ካርትኔይ ሚስታቸውንና ልጃቸውን ይዘው በአሜሪካ ግዛት ውስጥ በሺ የሚቆጠር ማይል ርቀት ተጉዘዋል። ይህን ሁሉ ጉዞ የተጓዙት በሁለት ሰረገሎች ሆነው ነው። ሠረገላዎቹ የሚጎተቱት በፍየሎች ነበር።

አሜሪካዊው ፍሬድ ባልዳሳር በእንግሊዝ ቻናል ውስጥ እየዋኘ በውሃው ውስጥ ለውስጥ 67 ኪሎ ሜትር ከ200 ሜትር ተጉዟል፤ ሐምሌ 10 ቀን ጉዞውን ጀምሮ በማግስቱ ሐምሌ 11 ቀን 1962 ዓ.ም ጨረሰ።

በአፍሪካ ውስጥ የዳን ጎሳ ባላባት የነበሩት አቶ ቶዌ ቀንና ለሊት ከራሳቸው ላይ የማይነሳ አንድ የሐር ባርኔጣ ነበራቸው፤ በዚሁ ሁኔታ ባርኔጣውን አርባ ዓመት ሙሉ አድርገውታል፤ አቶ ቶዌ አንድ እምነት ነበራቸው፤ እሱም የሐር ባርኔጣ ከጥይትም ሆነ ከማንኛውም የስለት ነገር የመከላከል ኃይል አለው እያሉ ያምኑ ስለ ነበር ነው።

ማርኩሳስ በሚባለው ደሴት ላይ የሚኖሩ ሰዎች፤ አንዲት፤ ሴት ባል አግብታ ተሞሽራ በምትወጣበት ጊዜ ብዙ መንገድ የምትጓዘው ሙሽራው አስከትሎ ባመጣቸው እድምተኞቹ ጀርባ ላይ እየተራመደች በመርገጥ ነው።

በ956 ዓ.ም ተወልደው በ1015 ዓ.ም የሞቱት የሩሲያው ቀዳማዊ ብላድሚር አራት ምሲቶችና አንድ ሺ ቁባቶች ነበሩዋቸው ንጉሡ በ988 ዓ.ም እነዚህን ሁሉ ሴቶች ባርረው መነኑ፤ ከሞቱም በኋላ የሩሲያ ቤተ ክስቲያን ቅዱስ ሆኑ።

የታወቀው ተራራ ወጪ ሉድዊግ ስቴነር በሃያ አምስት ዓመት ውስጥ ሦስት ሺ ተራራዎችን ወጥቷል፤ ከነዚህም ውስጥ 262ቱ ርዝማኔያቸው 13000 ጫማ ነው።

የታወቀው ታላቅ ፈላስፋ ፍራንክሊን ጥር 17 ቀን 1706 ዓ.ም ተወለዱ አወላለዳቸው ከ17 ልጆች አንዱ ናቸው በ17 ዓመት ዕድሜያቸው ሥራ ጀመሩ፤ በሚያዝያ 17 ቀን 1790 ዓ.ም ሞቱ።

በሰሜን ካሜሩን ውስጥ ማንዳራ በሚባእልው ጎሳ መጥረቢያ እንደገንዘብ ያገለግል ነበር፤ በሁለት መጥረቢያ አንድ በግ ይገዛ ነበር።

ጃፓኖች አንድ የዝሆን ጥርስ ሳያለያዩ በመጥረብ ሁለት የተያያዙ ፈረሶችን ይሠራሉ።

በሕንድ አገር የሜዋር ማሀራጃ ሳንግራም ሲን በጦርነት ላይ ሰማንያ ጊዜ ቆስለዋል። አንድ ዓይናቸው ጠፍቷል፤ አንድ እጃቸው ተቆርጧል፤ አንድ እግራቸውንም አጥተዋል፤ እንዲህ በመቆራረጥ የጀመራቸው ጦርነት በዚያው ጨረሳቸው በጦርነት ላይ ተገደሉ ፡

በ1763 ዓ.ም ተወልደው በ1805 ዓ.ም የሞቱት ዊልያም አጉስቶስ በሰዓሊነት፤ በዲፕሎማቲክነት፤ በተዋናይነት በመርከበኛነት፤ በወታደርነት በሙዚቀኛነት በዳቦ ጋጋሪነት፤ በቋንቋ አዋቂነት፤ በአዳኝነት፤ በሕግ አዋቂነት፤ በመድኃኒት ቀማሚነት፤ የታወቁ ሰው ነበሩ።

በአፍሪካ ውስጥ የቦንጎስ ሰዎች ሞተው በሚቀበሩበት ጊዜ በመቃብራቸው ላይ ከእንጨት የተሠራ ጌጥ ያለው ቋሚ ምሰሶ ይደረግና ለቀስተኛው ሁሉ አንዳንድ ቀስት ይወረውሩበታል፤ ቀስቱም አይነሳም፤ ምክንያቱም የቀስቱ ልክ በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ የነበረውን ሰው ብዛት ይገልፃል ብለው ስለሚያምኑ ነው።

## ውሻ

ውሻ ከተፈጠረ አርባ ሚሊዮን ዓመታት ያህል እንደሚሆነው ሊቃውንት ይናገራሉ፤ ውሻ አጫጭር እግሮችና ግዙፍ አካል የነበረው እንደነበርም የተገኙት የጥንት ማስረጃዎች ይገልጻሉ፤ ውሻ ከአውሬ ዘር ሁሉ ለሰው በጣም የቀረበ ነው፤ ተኩላና ቀበሮ የውሻ ዘሮች ሆነው ሳለ ውሻ ከሰው ጋር መኖርን ሲላመድ እነሱ አውሬዎች እንደሆኑ ቀሩ።

ውሻ ከክርስቶስ ልደት በፊት ስምንት ሺ ዓመታት ገደማ በሜሶፖታሚያ ውሻ እንደታየና ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ከሰው ጋር መኖርን እንደ ጀመረ ይነገርለታል በዚህ የረጅም ጊዜ ኑሮው ከዛሬዎቹ የቤት እንስሳት ሁሉ ከሰው ጋር ቀድሞ መኖርን የጀመረ ውሻ እንደ ሆነ ይታመናል።

የውሻ ዘር ዓይነቱ ከሁለት መቶ በላይ ነው፤ ይህ ሁሉ የውሻ ዘር ለሰው ልጅ የቅርብ ወዳጅ በመሆን በመላው ዓለም ላይ ውሻ የተወደደ እንስሳ ነው፤ ውሻ ከብዙ ዘመን ጀምሮ ከሰው ጋር በመኖሩ ከሰው ጋር የተያይዘ ብዙ ታሪክ አለው፤ የጥንት የደቡብ አሜሪካ ሰዎች በውሻ ያመልኩ ነበር የጥንት የሜክሲኮ ሰዎች አንድ ሰው ሲሞት ከጭቃ የሚሠሩ የውሻ ምስሎች ከሟቹ ዘመዳቸው ጋር አብረው ይቀብሩ ነበር።

ስለ ውሻ የሰው ወዳጅነት ለመጥቀስ ያህል ቢያስፈልግ ብዙ ታሪኮችን ማምጣት ይቻላል፤ ጥቂቶቹን እንመለከታቸዋለን፤ እንግሊዛዊው የኪልክ ሀምተን ነዋሪ የነበረው ጆን ግሪንቪል በተወለደ በአሥራ ስድስት ዓመቱ ኒውብሪ ላይ በተደረገው ጦርነት በጥይት ተመትቶ በዚያው በጦሩ ሜዳ ጓደኞቹ ቀበሩት፤ ከጌታው ጋር አብሮ ዘምቶ የጆን ውሻ የጌታውን መቃብር ያይ ነበርና ጭር ሲለልት ጌታውን ከመቃብር ቆፍሮ አውጥቶ እየጎተተ ከሠፈር አደረሰው፤ ጆን አልሞተም ነበርና ቁስሉን ድኖ ከመቃብር ከወጣ በኋላ 57 ዓመት ኖሮ በ73ኛው ዓመቱ እውነተኛውን ሞት ሞተ።

የኖርዌይ ንጉሥ የነበሩት ኤስቴን ውሾቻቸውን የገዢነት ማዕረግ ይሰጡዋቸው ነበር፤ በተባይ ሳዑር የተባለው ውሻቸው ሙሉ የገዢነት ሥልጣን ነበረው፤ እነኚህ የገዢነት ማዕረግ የነበራቸው ውሾች ሁሉ የሚቀበሩበት በቤተ መንግሥቱ ውጥ ነበር በንጉሡ ቤተ መንግሥት ውስጥም ዘጠኝ ውሾች ተቀብረዋል።

ውሻ ከቤተ ክርስቲያን ለምን አይገባም? ለምንስ እርኩስ ተብሎ ይባረራል? ታሪኩና ውግዘቱ የመጣው ከእንግሊዝ አገር ነው፤ እንግሊዞች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄዱ ውሾቻቸውን እየያዙ ይሔዱ ነበር፤ በ1638 ዓ.ም የጌታ ልደት ዕለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥርዐተ ቅዳሲወ ሲካሄድ አንዲት ውሻ ከመሰዊያው ላይ ለቁርባን የተቀመጠውን ኅብስት ይዛ በረረች፤ ከዚያ በኋላ ሊቀ ጳጳስ ላዑድ «ውሾች ከቤተ ክስቲያን ቅጥር ግቢ እንዳይገቡ» ስለከለከሉና ይሄው አዋጅ ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ስለተላለፈ እስከ ዛሬ ድረስ ውሾች ከቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ ክልከላው ጸና።

ከውሻ ዘር ሁሉ እስከ ዛሬ በሚዛኑ ከባድነት የታወቀው የዶክተር በርነር ውሻ ነው፤ ይህ አሜሪካ አገር በዊስኮንሲ ይኖር የነበረው ውሻ ጥቅምት

ስምንት ቀን 1964 ዓ.ም ተመዝኖ ክብደቱ 145 ኪሎ ሆኖ ነበር፤ ይህ ውሻ በ1969 ዓ.ም በነሐሴ ወር ሞተ። ከውሻ ዘር ሁሉ አሁን ዘርዋ እየቀነሰና በመጥፋት ላይ ያለችው ውድ ውሻ ሎቼን የሚሏት የውሻ ዘር በአገራችን አልፎ አልፎ በየሰው ቤት ይገኛሉ ግን፤ በእንክብካቤ እየተያዙ እንዲረቡ ስለማይደረግ በእኛም አገር ዘራቸው እንዳይጠፋ ያሰጋል፤ በተለይ በአገራችን ውሻ እያረቡ የመሸጥ ልምድ የለም እንጂ ቢኖር ኖሮ ውጭ አገር ድረስ በመሸጥ ጠቃሚ ገቢ ይገኝ ነበር።

የውሻ ዕድሜ ከአሥራ አምስት ዓመት አይበልጥም ሃያ ዓመት የሚሞሉ በጣም ጥቂቶች ናቸው፤ በዚሁ በውሻ ታሪክ ውስጥ በቦስተን ይኖር የነበረው አዡታን የሚባለው ውሻ 27 ዓመት ከሦስት ወር በመኖሩ እስከዛሬ ድረስ በዕድሜ ተወዳዳሪ አልተገኘለትም፤ የሊቃውንትን ጥናት በጥቂቱ ቢያፋልስም በመጨረሻው በተአምር የኖረው ውሻ ተብሏል። ይህ ውሻ በ1936 ዓ.ም ነሐሴ 14 ቀን ተወልዶ ኅዳር 20 ቀን 1963 ዓ.ም ሞተ።

በ1970 ዓ.ም ጥቅምት 10 ቀን የውሾች የጉልበት ውድድር በኒውፋውንድላንድ ተደርጎ ኒውፊልድ ኔልሰን የሚባለው ውሻ 1630 ኪሎ ክብደት ያለውን ዕቃ አሥራ አምስት ጫማ ርዝማኔ በዘጠና ሴኮንድ ጊዜ ውስጥ እየሳበ በመውሰዱ ዛሬ በክብደት መሳብ ተወዳዳሪ የሌለው ውሻ ሆንዋል።

በቁመት ደግሞ ከዓለም ውሾች እስከ ዛሬ ድረስ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት በእንግሊዝ አገር በኬንት ከተማ የነበረው በ1962 ዓ.ም የተወለደው የወይዘሮ ሜሪ ቤይኖን ውሻ አንድ ሜትር ከሃያ ሳንቲም ርዝማኔ ነበረው። በትንሽነት ተወዳዳሪ የሌላት ቺኋኋ የሚሏት ውሻ ናት፤ የዚች ውሻ ክብደት ግማሽ ኪሎ ያህል ብቻ ነው። በሩጫ ፍጥነት ደግሞ ሳሉኪ የሚሉት ውሻ ፈጣን ነው፤ የዚህ ውሻ ዘር በአንድ ሰዓት ውስጥ ስልሳ ስምንት ኪሎ ሜትር ያህል ለመሮጥ ይችላል። በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጃፓን አገር ውሾች እንዲመለኩ ያለዚያም በክብር እንዲያዙ የሚያስገድድ አዋጅ ወጥቶ ነበር፤ አዋጁን ያወጁት የጃፓኑ ንጉሠ ነገሥት ካታኮቴ በቤተ መንግስታቸው ውስጥ 50 በክብር የተያዙና የሚመለከባቸው ውሾች ነበሩዋቸው።

በቻይና፣ ንግሥት ፂ ሲ አንድ መቶ ውሾች ነበሩዋቸው፣ አንድ ጊዜ ንግሥቲቱ የነበራቸውን አንድ ውሻ አስከትለው ሲንሸራሸሩ በድንገት ነብር መጥቶ ንግሥቲቱን ሊበላቸው ሲል ውሻቸው አስቀድሞ ነብሩን ነክሰው ንግሥቲቱ አምልጠው እስኪሄዱ ድረስም ውሻው ነብሩን እየታገለው አቆይቶ ንግሥቲቱ ማምለጣጨውንና መዳናቸውን ሲያውቅ ውሻው ነብሩን እንዲሄድ አደረገው፣ በዚህ ምክንያት ንግሥቲቱ ውሻ የተሻለ ወዳጅ መሆኑን አውቀው በቤተ መንግሥታቸው ውስጥ አንድ መስሎ ስለ ነበር በዚያው ሰበብ ሲሞት በቤተ መንግሥቱ ግቢ አስቀብረው ለመታሰቢያውም ሐውልት አሠሩለት።

ውሻ የሰው ልጅ ወዳጅነቱ በዛሬው ጊዜ የበለጠ እየሆነ ሄድዋል፣ ለምሳሌ ዕውራንን በመምራት በኩል የሚሰጠው አገልግሎት በመላው ዓለም ላይ እየተስፋፋ ሄድዋል። አንድ ውሻ የሚመራውን ዕውር ሰው ይዞ በሚሄድበት ጊዜ አንድ አደጋ ነገር ወይም የሚሮጥ መኪና ከፊቱ ካለ ጌታው ዕውሩ ሰውየ ሂድ እያለ በዚያውም አይሄድም፣ ያ አደጋ ነገር ካለፈ በኋላ ግን ውሻ ጌታውን እየሳበ ይሄዳል፣ ለዚህ ዓይነቱ ተግባር የሚያገለግሉት በተለይ ሸፐኸርድ የሚሏቸው የጀርመን ውሾች ናቸው።

ውሻ ወዳጅነቱ ብቻ ሳይሆን የሚያመጣው መዘዝ ብዙ ነው፤ የውሻ በሽታ ወይም ያበዳ ውሻ በሽታ በሰው ልጅ ላይ ስለሚጋባ በዚህ በሽታ ያለቀው የሰው ልጅ እጅግ በጣም ብዙ ነው።

አንድ ያበደ ውሻ ሰውን ከነከሰ የተነከሰው ሕክምና ካላገኘ ሕመሙ ከጀመረው በኋላ በሞት እንጂ መዳኛ የለውም፣ አንድ ያበደ ውሻ አንድ መቶ ሰዎችን ቢነክስ በሽታው የሚተላለፍባቸው ሰዎች ምናልባት አራትና አምስት ሰዎች ያህል ቢሆኑ ነው፤ በሽታው የተላለፈው የትኛዎቹ ሰዎች ላይ እንደሆነ በጤንነት ጊዜ መርምሮ ማወቅ ስለ ማይቻል በእብዱ ውሻ የተነከሱት ሰዎች በሙሉ መከተብ ወይም መታከም አለባቸው፤ ምክንያቱም በሽታው ሥር ሰድዶ በሰውየው እስጥ ከተሠራጨ በኋላ ከሞት በስተቀር የማዳኛ መድኃኒት የለውም ከዚህ ሁሉ ጣጣ ውሻ የሚያሳድጉ ሰዎች ውሾቻቸውን በየተወሰነው ጊዜ ቢያስከትቡ ውሾቻቸው ታማኝና ጥሩ ወዳጆች ይሆኑዋቸዋል።

የእብድ ውሻ ጉዳይ ከተነሳ ክትባቱን ያገኘውን ሉዊስ ፓስተርን ሳያነሱ ማለፍ ታላቅ ወንጀል ነው፤ ከዘመናቸው አልፈው ለዛሬው ዘመን የሰው ልጅ

ጭምር ታላቅ ውለታ ከዋሉት ታላላቅ የዓለም ሊቃውንት መሐል አንዱ ሉዊስ ፓስተር ነውና ነው።

ፓስተር የእብድ ውሻን መድኃኒት ለማግኘት የለፋው በልጅነቱ ወራት ከሚያድግበት ሠፈር ስምንት ሰዎች በአበደ ተኩላ ተነክሰው መሞታቸውን አይቶ ነበርና ያን አሰቃቂ በሽታ ለማጥፋት ብሎ ነው።

ፓስተር መድኃኒቱን ለማግኘት ሺ ጊዜ ሙከራ አድርጓል፤ አንዳንዴም የሚያገኘው መድኃኒት እጅግ አደገኛ ያሉትን ተቸግሯል፤ በመጨረሻ ጊዜ ግን መድኃኒቱን አገኘው፤ በውሻው ውስጥ ያሉትን ጀርሞች ማዳከም የተሻለ ጥሩ ውጤት አስገኘለት፤ የዚህን በሽታ ጀርም ቫይረስ የሚባለውን ለጤነኛ ውሻ በመርፌ በመውጋት ያደረገው ሙከራ መልካም ውጤት አስገኘለት ከአሥራ አራት መርፌ መወጋት በኋላም ውሻው በበሽታው ቢለከፍም ለመቋቋም ይችል ጀመር፤ መርፌዎቹን የተወጉት ውሾች በማንኛውም እብድ ውሻ ቢነከሱ ፈጽመው የማያብዱ ሆኑ።

ይህ ሉዊስ ፓስተር ያስገኘው መድኃኒት እስከዛሬ ድረስ በመላው ዓለም ላይ የሚሠራበት በመሆኑና የሰውን ልጅ ከከፍተኛ አሰቃቂ በሽታ በማዳኑ በየአገሩ ለሉዊስ ፓስተር የመታሰቢያ ቤቶች ወይም ሐውልቶች ተቋቁመዋል፤ በኢትዮጵያም በአዲስ አበባ ከተማ ያእልው ዋናው መድኃኒት ቤት (ላቦራቶሪ) የሚጠራው በፓስተር ስም በመሆኑ ለዚያ ታላቅ ሊቅ የተደረገ መታሰቢያ ነው።

ሉዊስ ፓስተር በ1822 ዓ.ም ከፈረንሳዊው ከናፖሊዮን ወታደሮች መሐል ከአንዱ ተወለደ፤ ሉዊስ ፓስተር በተማሪ ቤት ሆኖ ትምህርቱን የማይከታተልና የማይገባውም ልጅ ልጅ ነበር። ሁልጊዜም «ባንድ ነገር ላይ መጠበብ ካለ ሁሉም አለ» ይል ነበር፤ በጉርምስና ዘመኑም ሲጽፍ «በመፍትሄ ቃላት መዝገብ ውስጥ ካሉት ቃሎች ሁሉ ውናዎቹ ፈቃደኛነት መሥራትና ውጤት የሚሉት ብቻ ናቸው» ብሏል።

ከኮሌጅ ትምህርቱን እንደ ጨረሰ ወደ መድኃኒት መቀመሚያ ክፍል ዞረ፤ በዚያም መልካም ውጤት ስላሳየ በ1849 ዓ.ም የፈረንሳይ የትምህርት

ሚኒስቴር በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፊዚክስ እንዲያስተምር አደረገው በትርፍ ጊዜው ባያሎጂ አጥንቶ ተመረቀ።

አንድ ጊዜ የወይን ገበሬዎች ወደ ፓስተር መጥተው «የምንጠምቀው ወይን አንዳንድ ጊዜ ባንድ ዓመት ውስጥ ይኮመጥጣልና ምን እንደሚበጀን ንገረን» አሉት፤ ፓስተር የኮመጠጠውን ወይን ጠጅ በመደጋገም መርምሮ ይህን የኮመጠጥ ጠባይ የሚያመጡት ባክቴሪያ የሚባሉት ጀርሞች መሆናቸውን አወቀ እነኚህንም ባክቴሪያዎች ከወይን ጠጁ ውስጥ ለማጥፋት ጠጁን ማፍላት መሆኑን ተገነዘበ፤ በዚህ ሳቢያ የወተትም ጥበቃ ጉዳይ እንደዚሁ መሆኑን አውቆ አሳወቀ።

በዚያው በፈረንሳይ አገር የዶሮ ኮሌራ ተነስቶ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዶሮዎችን ፈጀ፤ ዶሮ፤ አርቢዎችም ወደ ፓስተር ሂደው እንዲረዳቸው ለመኑት፤ የታመመችዋን ዶሮ ደም ሲመረምር ባክቴሪያዎችን ስላገኘ የእነዚህን ጀርሞች አቅም ለማዳከም በሽተኛ ዶሮዎችን ደም እየቀዳ ጤነኞቹን በመውጋት በሽታውን እንዲላመዱት እያደረገ በሽታውን አጠፋ፤ ፓስተር ዘዴ ቢጠቀምም የክትባትን ዘዴ ያገኘው ፓስተር ሳይሆን ፓስተር ከመወለዱ ሰላሳ ዓመት በፊት ያገኘው እንግሊዛዊው ሳይንቲስት ኤድዋርድ ጄነር ነው።

በጎችና ላሞችን ይፈጁ ለነበረው አንትራክስ ለሚባለው በሽታ እንደሌላው ሁሉ ተመሳሳይ የክትባት ዘዴ ያገኘውም ፓስተር ነው። ፓስተር ታሞ በአልጋው ላይ እንደተኛ በ1859 ዓ.ም በ73 ዓመት ዕድሜው እንቅልፍ እንደ ወሰደው በዚያው ሞቶ ቀረ።

ወደ ውሾቹ ታሪክ ልመልስዎትና ጥቂት ላውራልዎት በ1956 ዓ.ም በጥር ወር እንግሊዛዊቷ ወይዘሮ ሜሪ የሦስት ዓመት ተኩል ዕድሜ ውሻቸውን ሸጠው ነበር፤ ያ ውሻ የተሸጠበት ዋጋ በዘመኑ የኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር 73500 ብር ነው።

በውሻ ዘር ታሪክ ውስጥ በአሜሪካ አገር የኮማንደር አሊይ ውሻ የካቲት 11 ቀን 1945 ዓ.ም 23 ቡችላዎችን ስለወለደች በአወላለድ ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ ተወዳዳሪ ያልተገኘላት ነች።

የቻይና ገበሬዎች አሳማ ለመሸጥ ወደ ገበያ ሲወስዱ አሳማው በጉዞ ምክንያት ክብደቱ እንዳይቀነስ በጫንቃቸው ላይ ተሸክመው ይወስዱት ነበር።

በኒው ሄይብራድስ ውስጥ በሜኩላ የሚኖሩ ናምባስ የተባለው ጎሳ ሴቶች በአሥራ ሁለት ዓመት ዕድሜያቸው ባል ሲያገቡ አንድ ከጠጉር የሚሠራ ባርኔጣ ይደረግላቸዋል፤ ይህ ባርኔጣ እስኪሞቱ ድረስ ቀንም ሆነ ለሊት ከራሳቸው ላይ አይወልቅም።

በ1805 ዓ.ም ተወልደው በ1865 ዓ.ም የሞቱት ሰር ዌልያም ሮዋን ሐሚልተን በ12 ዓመት ዕድሜያቸው 12 ቋንቋዎች መናገር ይችሉ ነበር፤ በዚሁ ዕድሜያቸው በአስተሮኖሚ የፕሮፌሰርነት ማዕርግ አግኝተዋል።

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ከተጻፉት ታሪክ ካላቸው ሕንፃዎች ሁሉ ዛሬ በኢየሩሳሌም የሚገኘው ሔሮድስ ያሠራው ሕንፃ ብቻ ነው ይህ ሕንፃ የሁለት ሺ ዓመታት ዕድሜ አለው።

በአፍሪካ ውስጥ የጎቡስ ጎሳ ሴቶች በከንፈሮቻቸው ላይ ቀለበቶች ያደርጋሉ ከባሎቻቸው ጋር ጭቅጭቅ ወይም ንትርክ ሲጀምሩ ባሎቻቸው ሁለቱን ቀለበቶች በማገናኘት ዝም ያሰኙዋቸዋል።

በቦርኒዮ የሚኖሩ የካኒያህ ጎሳ ሰዎች ጀልባቸውን የሚሠሩት አዞ አስመስለው ነው፤ ከፊት ለፊት ያለው የጀልባው መከላከያ ወይም የአዞዋ ራስ ከንጹህ ብረት የሚሠራ የሾሉ ጥርሶች ያሉበት ነው።

በ1785 ዓ.ም ተወልደው በ1849 ዓ.ም የሞቱት ፈረንሳው ኢውገን ኮኩበርት በ5 ዓመት ዕድሜያቸው በአደጋ ምክንያት ጆሮአቸው ሲደነቁር፤ አፋቸው ደግሞ ዲዳ ሆነ። እኒህ መናገርና መስማት የማይችሉ ሰው በፈረንሳይ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ ተቀጥረው በተርጓሚነት ይሠሩ ነበር፤ ራሳቸው ራሳቸውን በማስተማር ጽሕፈትና ንባብ ይችሉ ነበር፤ በዚያም ላይ 21 የተለያዩ ቋንቋዎች ይችሉ ነበር።

በካንሳስ ውስጥ በሞንቴዙማ ይኖሩ የነበሩት አቶ አልክላርክ መቶ ያርድ ርቀት ከፈረስ ጋር ተሽቀዳድመው ቀድመዋል።

በዚህ በአፍሪካ በቻድ ውስጥ ሐዤራይ የሚሉት ጎሣ አለ። የዚህ ጎሣ ሰዎች በጋያ ትንባኖ እንዲያጨሱ የሚፈቀድላቸው ሴቶች ብቻ ናቸው። ለወንዱ የሚፈቀደው ትንባሆ መጉረስ ነው።

የሰጎን እንቁላል አንድ መቶ ኪሎ ያህል ክንደት ሳይሰበር መሸከም ይችላል።

በሕንድ አገር ከፍሬ ዘይት የሚያወጡ ሰዎች ፍሬውን በጨርቅ ውስጥ ሞልተው ከግንድ ላይ ያስሩና በዚያ በታሠረ ጨርቅ ውስጥ አንድ እግራቸውን ከትተው ፍሬውን በመርገጥ ዘይቱን ይጨምቃሉ። በአንድ እግራቸው ቆመው በአንድ እግራቸው ዘይቱን እየጨመቁ ሲውሉ የአካላቸውን ሚዛን ስተው ትንሽ እንኳን ወልገድ አይሉም።

በቦርኒዮ ባልና ሚስት በሚጋቡበት ጊዜ በሙሽራዎቹ ፊት የሰው ራስ አጽም ይቀመጣል። ምሳሌው «የፍቅር መጨረሻው ሞት ነው» ለማለት ነው።

በሩሲያ የኡዝቤክስ ሰዎች በገበያ ላይ የሚገበያዩት ሻጩም ገዥውም በፈረስ ላይ ተቀምጠው ነው።

የሂሳብ ፒራሚድ ይሥሩ።

1x9+ 2=11

12x9+3=111

123x9+4=1111

1234x9+=11111

12345x9+=111111

123456x9+=1111111

1234567x9+=11111111

12345678x9+=111111111

በደቡብ አሜሪካ በጉዋና ውስጥ ዋሮው የሚባሉት ሰዎች ቤታቸውን የሚሠሩት በውሃ ውስጥ ነው። በዚያም በውሃ ውስጥ ቤታቸው የሚኖሩት ዓመቱን በሙሉ ሳይሆን ከዓመት ውስጥ ዘጠኝ ወር ነው። በኑሮአቸው ጊዜ ዓሣ የሚያጠምዱት ከቤታቸው ይርቁና በቤታቸው ውስጥ እንዳሉ ነው።

በደቡብ አሜሪካ ውስጥ እስፒደር መንኪ የሚሉዋቸው ዝንጀሮዎች አሉ። እነዚህ ዝንጅሮዎች ካንዱ ወንዳንዱ በሚሸጋገሩበት ጊዜ እርስ በራሳቸው ተቆላልፈው ድልድይ ይሠራሉ።

ፈረንጆች ሲልቨሪ ጉል የሚሏት ወፍ ቀንድ አውጣ የሚባለውን አውሬ መብላት ትወዳለች። ቀንድ አውጣው ከቀፎው ውስጥ ስለማይወጣላት ቀንድ አውጣውን ይዛ ወደ አየር ትወጣና ከድንጋይ ላይ እንዲያርፍ ቀንድ አውጣውን ትጥለዋለች። በአንድ ጊዜ ውርወራ ቀንድ አውጣው ከቀፎው ተላቆ አይወጣላትም። ተስፋ ባለመቁረጥ እየደጋገመች 59 ጊዜ ድንጋይ ላይ በመወርወር ፈንክታ ትበላዋለች።

በኦስትሪያ ሐሊስታ በሚባለው የቀበር ሥፍራ የሚቀበሩ ሬሳዎች ከአሥር ዓመት በኋላ አጽሞቹ እወጡ ታሪካቸው እየተጻፈ መጋዘን ይቀመጣሉ።

በፓኪስታን የሚኖሩ ሴቶች ኮብራ የሚባለውን አደገኛና መርዘኛ እባብ በሰፈናቸው አፍዝዘው ያቆሙታል።

በቻድ ውስጥ ያሉ ቆነጃጅት በአፍንጫቸው ቀዳዳ ጠጉር በመከተት ጢም እያስመሰሉ ያጌጡበታል።

በሰሜናዊ ካሜሮን ሡልጣን አሊ በበዓል ቀን የሚቀመጡበት ፈረስ ሐረር ሱሪ የሚታጠቅ ነው።

በአሜሪካ አገር በፍሎሪዳ ውስጥ በሳን ፔተርስበርግ በሚባለው ቦታ ያለው የአቶ ኦዌን አልበርት ቤት አጥሩ የተሠራው ዛጎሎች አቶ ኦዌን ለቅመው የሠሩዋቸው ከሚክሲኮ ገልፍ እየለቀሙ በማጠራቀም ነው።

ዶክተር ኦሴንሶ በኮንጎ ውስጥ የሜዳ አህያ አስለጥነው ኮርቻ በመጫን ተቀምጠውባት ይዞሩባት ነበር።

የፈረንሳይና የስፓኝ ወሰን ላይ ያሉ ሰዎች በያመቱ ላይ ባለው ድንጋይ ላይ እጃቻቸውን ደርበው በመማማል 596 ዓመት አድርገዋል።

በ1518 ዓ.ም ተወልደው በ1610 የሞቱት ፈረንሳዊቷ ወይዘሮ ፓውል ቪዙር በቁንጅናቸው የሚደነቁ ወይዘሮ ነበሩ በመንገድ ላይም ሰው አላስኬድ ስለሚላቸው ከቤት ላይወጡ ወስነው ነበር። ሕዝቡ በአቤቱታ ስለጠየቀ በቀን ሁለት ጊዜ ከፎቅ በረንዳ እንዲወጡ ሰልተበየነ 92 ዓመት ታይተዋል።

በአላስካ የሚኖሩ እስኪሞ እየተባሉ የሚጠሩት ሰዎች በአሣ ማጥመጃ መንጠቆዋቸው ላይ የባህላቸውን የጣዖት ምስል ያደርጉበታል። ምክንያቱም ጣዖቱ አሣ ያስይዛል ብለው ሰለሚያምኑ ነው።

የጥንት የባቢሎን ሰዎች ለባቢሎን ከተማ የወይን ጠጅ ለማደል ከባላገር ወደ ከተማ ሲሄዱ የሚጓዙት በኤፍራጥስ ወንዝ ላይ ድብልብል በሆነ ጀልባ እየተጓዙ ነው፤ በሚጓዙበት ጊዜ በጀልባቸው ላይ አህያ ጭነው ይጓዛሉ፤ የወይን ጠጃቸውን ሸጠው ሲጨርሱ ጀልባቸውንም ከዚያው ይሸጡና ወደ ቤታቸው ሲመለሱ በአህያቸው ተቀምጠው ነው።

በኢጣሊያ አገር በጄናዛኖ ባለ መቅደስ ውስጥ ወደ መሠዊያው የመውጫው ደረጃ ከአንድ ዕብነ በረድ ድንጋይ ብቻ ተፈልፍሎ የተሠራ ነው፤ የዚያ ደረጃ ወይም ዕብነ በረድ ክብደት አንድ መቶ ሰባ ኩንታል ይመዝናል።

በፈረንሳይ አገር ቢሮስ በሚባለው ሸለቆ የሚኖሩ ገበሬዎች ከጫፉ ሸቅብ የሾለው ጫማ ያደርጋሉ፤ ይህም የሚያደርጉት ጫማ ከብዙ ዘመን ጀምሮ ነው፤ የእንግሊዙ ንጉሥ ዳዊት ሪቻርድ የፈረንሳዩን ንጉሥ የቻርልስ 6ኛ ልጅ የሆነችውን ኢሳቤላን ሲያገቡ አድርገውት የነበረው ጫማ ከአፍንጫው ቆላፋ ሆኖ ሸቅብ የቆመ ስለ ነበረ ገበሬዎቹ የዚያን ጊዜ ያዩትን ማድረግ ጀምረው እስከ ዛሬ ያደርጉታል፤ ይህም ዛሬ 1400 ዓመት ያህል መሆኑ ነው።

በብራዚል የእንቁራሪት አሣ የሚሉት የአሣ አለ፤ ይህ አሣ ከውሃ ውስጥ ወጥቶ ክንፎቹን እንደ እግር በማድረግ ይጓዛል፤ ከውሃ ውጪም ሦስት ቀን ያህል በደረቅ አፈር ላይ መቆየት ይችላል።

1818 ዓ.ም በፈረንሳይ አገር አንድ በእንፋሎት ኃይል የሚሄድ ባብር ተሠርቶ ነበር። ባቡሩ በሚሄድበት ጊዜ እሳቱን የሚቆሰቁሱ ሁለት ሰዎች ይከተላሉ።

በ1819 ዓ.ም ተወልደው በ1878 ዓ.ም የሞቱት የጀርመኑ ንጉሠ ነገሥት ጆርጅ ፭ኛ በየቀኑ በፈረስ ላይ እየሆኑ የጦር ሠራዊታቸውን ይጎበኙ ነበር። እኚህ ንጉሥ ሠራዊታቸውን ይጎበኙ እንጂ ፍጹም ዕውር ነበሩ።

በቤልጂግ አገር በሞንት ግኒ ውስጥ የቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን አለ። ቤተ ክርስቲያኑን የሚሳለሙ ሰዎች አንድ እምነት አላቸው። ልጆቻችንን ከጨለማ መፍራት ያድናቸዋል ብለው ያምናሉ።

በ938 ዓ.ም ተወልደው 995 ዓ.ም የሞቱት ሳሂብ የሚሏቸው የፔርሺያ ሰው ነበሩ። እኚህ ሰው 117000 መጻሕፍት ነበሩዋቸው። ሳሂብ መጻሕፍቶቻቸውን የሚያስቀምጡት በቤት ውስጥ አልነበረም። መጻሕፍቶቻቸውን በአራት መቶ ግመሎች ጭነው ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ይዟዟሩ ነበር። መጽሐፍቱን የተጫኑት ግመሎች በመጽሐፍቱ ፊደል ተራ መሠረት ስለሚጓዙ አንድ አንባቢ አንድ መጽሐፍ ሲጠይቅ ያለ ምንም ችግር ግመል ሳቢዎቹ አውጥተው መስጠት ይችላሉ። እኚህ ሰው በዚህ መልካም ተግባራቸው ሳሂብ (ወዳጅ) ተባሉ እንጂ ስማቸው አቢል ቃሲም እስማኤል ነው።

ከ12 ዓ.ም እስከ 41 ዓ.ም ድረስ የሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት ካሊጉላ ማንኛውም መኳንንታቸው ያላደረጉትን ክብር ለፈረሳቸው ያደርጉ ነበር። ለፈረሳቸው ያደርጉ ነበር። የፈረሱ ጋጣ ከብር የተሠራ ነበር። ፈረሱ የሚጠጣው ንጉሡ የሚጠጡትን ወይም ጠጅ ሲሆን የሚጠጣበት ገንዳ ደግሞ ከንጹህ ወርቅ የተሠራ ነበር።

በጀርመን አገር ባቫሪያ ውስጥ ቫልድሳሰን በሚባል ከተማ አንድ በሥላሴ ስም የተሰየመ ቤተ ክርስቲያን አለ። በሦስቱ ሥላሴ የተሰየመው ቤተ ክርስቲያን 3 ሰገነት 3 ትልልቅ መስቀሎች፤ 3 ትንንሽ መስቀሎች፤ 3 ጣርያዎች፤ 3 በራፎች3 ታላላቅ መስኮቶች፤ 3 መሠዊያዎች፤ 3 የመቁረቢያ ቦታዎች፤ 3 መዝጊያዎች፤ 3 መብራቶች፤ 3 ታላላቅ ምሰሶዎች፤ 3 የማርያም

ሐውልቶች፤ በእያንዳንዱ ሰገነት ላይ 3 መስኮቶች አሉበት። ቤተ ክርስቲያኑን የሠራው መሐንዲስ በቤተሰቡ 3ኛው መሐንዲስ ነው። ቤተ ክርስቲያኑ ተሠርቶ ያለቀው በ33 ወር ከ33 ሳምንት በ33 ቀኖች ነው። የፈጀው ገንዘብ 33333 ፍሎሪንስ ከ33 ክሬውዘር ነው።

ቲበታውያን አዳኝ አምላክ የሚሉት አንድ አያት አላቸው በጣዖቱ አፍ ውስጥ መድኃኒት ይጨመርና አንድ የታመመ ሰው ያንን መድኃኒት ከጣዖቱ አፍ ውስጥ አጎንብሶ ሲጠጣ ይድናል ብለው ያምናሉ።

ካንጋሮ የምትባለዋ አወሬ ስመዋ እንዴት እንደወጣላት ሰምተዋል? አንድ እንግዳ ሰው አንዱን ያገር ተወላጅ ይጠራና «ይቺ አውሬ ስምዋ ማን ይባላል?» ብሎ ቢጠይቀው ያገሬው ሰው ሲመልስ «ካንጋሮ» አለ። ያም እንግዳ ሰው የአውሬዋን ስም ካንጋሮ እያለ በመጻፍ ስምዋ ካንጋሮ ሆኖ ቀረ። በአገሬው ቋንቋ ካንጋሮ ማለት «እኔ አላውቅም» ማለት ነው።

በምሥራቅ አፍሪካ ናንዲ የሚባል ጎሳ አለ። የዚያ ጎሣ ወንዶች ሚስት ለማግባት በሚፈልጉበት ጊዜ ሰፊ ባርኔጣ ይሠራሉ አምሳ ያህል ወፎች ይይዙና በዚያ ባርኔጣ ያስሩዋቸዋል። ከዚያ በኋላ ባርኔጣውን ራሳቸው ላይ አድርገው ሲሄዱ ወፎቹ ደንብረው ለመብረር ሲነሱ ይበራሉ። ወፎቹ ከሰውዬው ራስ ላይ አንስተው ይበራሉ። ወፎቹ በርረው ከሚያርፉበት አካባቢ ወይም ቤት ያለች ሴት ልጅ ለሰውየው በሚስትነት ትሰጠዋለች። ጋብቻ ከሰማይ መምጣት አለበት ብለው ስለሚያምኑ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኦሪት ዘኁልቁ ምዕራፍ 21 ቁጥር 9 ላይ ቢያነቡ ሙሴ የነሐስ እባብ ሠርቶ በምድረ በዳ ላይ መስቀሉን ያነባሉ። ያ የዚያን ጊዜ ተሰቅሎ የነበረው የነሐስ እባብ በኢጣልያ አገር፤ በሚላን ውስጥ ቅዱስ አምብሮጊዮ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን ምስል እሱ ነው ብለው ይናገራሉ።

የቀዳማዊ ናፖሊዮን ወንድሞች ፒሬ በናፓርትና ሉዊስ ቦናፖርት ለሁለት አንዲት ሴት ወደዱ። ሁለቱም ወንድማማቾች የወደዷትን ማሪያ ቼቺን ለማግባት ፈለጉ። በዚች ሴት ምክንያት ሁለት ወንድማማቾች እንዳይጣሉ አስበው በካርታ ጨዋታ ያሸነፈ እንዲያገባት ተስማምተው ተጫወቱ። ፒር

ተሸነፈ። የወደዳትንም ልጅ ሰላጣ አገሩን ፈረንሳይን ትቶ ወደ አሜሪካ አገር ሄደ። በአሜሪካ አገርም በኒውጀርሲ ባለው ቦርደን ታውን በተባለው ከተማ ኑሮውን መሥርቶ ኖረ።

በኢንዶኔዝያ ባታክ የሚሉት ጎሳ አለ። የዚያ ጎሳ መድኃኒት አዋቂ የሆኑ ሰዎች ባላቸው የሰው ምስል ባርኔጣ ላይ ላባዎችን ሸጠው በየገበያው ይዞራሉ። በባርኔጣው ላይ ብዙ ላባዎች ካሉ ሕክምናቸውን የሚፈልግ ይበዛል። ምክንያቱም እያንዳንዱ ላባ ያዳኑት ያንዳንድ ሰው ምስክር በመሆኑ ነው።

በአላሥካ ያሉ ሕንዳውያን የበግ ቀንዶችን በመጥረብ ይህን የመሰለ ጎድጓዳ ሰሃን ይሠራሉ።

በቲቤት ከይላሥ የሚሉት ተራራ እንደ ቅዱስ ሥፍራ ይታሰባል። ምዕመናን ተራራውን ዙርያ ክቡን በመዞር ያከብሩታል ዙርያውን እየዞሩ የሚያከብሩት በእግራቸው በመሄድ ሳይሆን በደረታቸው እየተሳቡ በመጓዝ ነው። የሚጓዙት መንገድ 7335 ሜትር ያህል ርዝመት አለው። ይህን ጉዞ ለመጨረስ ሦስት ሳምንት ይፈጅባቸዋል እየደጋገሙ የሚዞሩ ምዕመናን አሉ። ቀንና ሌት በመጓዝ ወይም በመዳህ ዘጠኝ ሳምንታት የሚቆዩም አሉ።

በሕንድ በቤንጋል አቅራቢያ ባለው ኒኮባር በሚባለው ደሴት የሚኖሩ ሰዎች የልደት በዓላቸውን የሚያከብሩበት ጊዜ የዘመዳቸውን አጽም ከመቃብር በማወጣት የአጽሙን ጭንቅላት ይዘው ነው ለምን እንዲያ እንደሚያደርጉ ሲናገሩ «ነገ አጽም መሆናችንን ለመንገር ነው» ይላሉ።

በኒውጊኒያ ያሉ የብዙ ጎሣ ሰዎች በዕድሜያቸው ጢማቸውን የሚላጩት አንድ ጊዜ ብቻ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ጢም ላጪው ሰውዬ የተላጨውን ጢሙ ሙጫ ይቀባዋል ከዚያ በኋላ እያንዳንዷን ጠጉር ከሥር ከመብቀያዋ እየነቀለ ለዳግመኛው እንዳይበቅል ያደርገዋል።

በዚሁ በአፍሪካ ውስጥ በናይጄሪያ ያሩባ የሚሉት ጎሳ አለ። በዚህ ጎሣ ውስጥ አንዲት ሴት መንታ ወልዳ አንደኛዋ መንትያ የሞተች እንደሆነ በሕይወት ያለችውን መንትያ ለማሳደግ አንድ የአሻንጉሊት መንትያ ይሠራል። የአቿንም አሻንጉሊት በሕይወት ያለችው ልጅ ልክ እንደ እህትዋ በማየት

አብራት ትኖራለች። አሻንጉሊቷ እንደ ሰው የምትለብስ ሲሆን እንደ ሰው ልጅ ደግሞ ምግብ ይሰጣታል።

በ1824 ዓ.ም ተወልደው በ1880 ዓ.ም የሞቱት ጆን ሽሚት የተለየ ባርኔጣ ነበራቸው ፕሮፌሰር ጆን ሽሚት በጀርመን አገር በፍሬይበርግ ዩኒቨርስቲ የቋንቋ መምህር ነበሩ ባርኔጣቸው ረጅም ይሆንና ከላይ በኩል የሚከፈትና የሚዘጋ ነው። ፕሮፌሰር ጆን የባርኔጣቸውን መዝጊያና መክፈቻ የሆነውን ሽቦ በኪሳቸው ይይዙና ፀሐዩ ገርሮ ራሳቸውን ሲያልባቸው የባርኔጣቸውን መከደኛ ከፈት ዘጋ በማድረግ አየር ወደ ውስጥ እንዲገባ ያደርጉ ነበር።

12x483=5796

42x138=5796

18x297=5346

27x198=5346

እነዚህ ስሌቶች በሙሉ በእያንዳንዱ መደዳ ያልተደጋገመ ሙሉ ቁጥሮች ማለት ከአንድ እስከ ዘጠኝ ድረስ ብቻ ያለባቸው ናቸው።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ጀርመኖች አንድ ጠመዝማዛ ጠመንጃ ሠርተው ነበር። ጠመንጃው የሚያገለግለው መዓዘን ቦታ ይዘው ለሚታኮሱ ወታደሮች የሚያገለግል ነበር።

አሌክሳንደር ዶማስ በዓለም የታወቀ ታላቅ ደራሲ ነው ዱማስ የተወለደው በ1842 ዓ.ም ሲሆን የሞተው በ1895 ዓ.ም ነው። አሌክሳንደር ዱማስ አንድ ለማዳ ነስር ነበረውና ሽርሽር ሲሄድ እንደ ውሻ በገመድ ይዞት ይዞር ነበር።

በአይርላድ ውስጥ ኩሊይ ባኬይ በተባለ መንደር ይኖሩ የነበሩት ወይዘሮ ማርጋሬት ስልሳ ዓመት ሙሉ ያለማቋረጥ ከሰንበት ትምህርት ቤት ውስጥ አስተምረዋል።

በቤልጂንግ ውስጥ በብሩጌስ አንድ ሕንፃ አለ። ሕንፃው ከመሐል ወገቡ አንድ ሜትር ከሩብ ወደ አንድ በኩል ዘሟል። በያመቱም እየዘመመ ይሄዳል።

በአሜሪካ አገር በአዞሪና ውስጥ ዊሊንግ በሚሉት ተራራ ወገብ ላይ አስምት ፎቅ ሆኖ ሃያ አምስት ክፍሎች ያሉት ሕንፃ አለ። ሕንፃው የተሠራው ኮሎምቦስ አሜሪካን ከማግኘቱ አንድ መቶ አምሳ ዓመታት በፊት ነው።

በአገራችን «አንቺ ምን ቸገረሽ የገዳይ ውሽማ፤ አንተርሶሽ ያድራ ዐጽ እንደ ብርኩማ» እየተባለ ለዝሆን ገዳይ ወዳጅ ይዘፈንላት ነበር፤ ዐጽ ማለት ከዝሆን ኮቴ የሚሰራ ትራስ ነው። በአገራችን የዝሆን ገዳይ ክብር ያለው ነበር፤ በእርግጥም ደግሞ ሊሆን የሚገባ ነው፤ ምክንያቱም አደገኛና በቀላሉ የማይገኝ አውሬ ነበርና ነው።

በሌሎች አገርሳ? ሳላበዛው በጥቂቱ ላጫውቶት፤

በአፍሪካ ያለ ዝሆን አውሬ ነው፤ በእስያ ያለ ዝሆን ግን ለማዳና እንድ አህያ ማንኛውም ሥራ የሚሠራ ታዛዥ ነው፤ ይህ ፎቶ ግራፉ ላይ የምትመለከቱት ዝሆን እርሻ ሲያርስ ነው፤ በሕንድ አገር ናይኒ ታል ቴራይ በሚባለው ሸለቋማ ሥፍራ የሚኖሩ ሰዎች እርሻቸውን የሚያርሱት ማረሻውን በዝሆን እያሳቡ ነው፤ በሕንድ አገር ዝሆን ብዙ ሥራ ይሠራል፤ ሁለት ፎቶ ግራፎች ላሳይዎ የአፍሪካ ዝሆን ግን ለማዳ ባለመሆኑ የኮንጎ አራት ጠባቂዎች ሁለት ዝሆኖች ለማዳ ስላደረጉ ይደነቃሉ።

በጥንታዊቷ እስፓርታ የታወቁ ሠካራሞች እየተመለመሉ ሰክረው በከተማዋ መሐል እየተወላገዱ እንዲዘዋወሩ ይደረግ ነበር። እነሱን እያየ ወጣቱ ትውልድ ከስካር እንዲሸሽ ለማድረግ ታስቦ ነው።

በኒውጊንያ የሚኖሩ ሰዎች ካሉ ሰዎች ሁሉ የተለየ ባርኔጣ ያደርጋሉ ባርኔጣቸው የሚሠራው ከሸረሪት ድር በመሆኑ ነው።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ37 ዓ.ዓ ሥልጣን የያዙት ፍራቴስ ፬ኛ ሥልጣን ይዘው ፓርቲያንስ ማስተዳደር ሲጀምሩ ሥልጣኔን ይቀናቀኑኛል ወይም ይነጥቁኛል ብለው የሚጠረጥሩዋቸውን ሁሉ ገድለዋል። ከተገደሉት ሰዎች መሐል አባታችው፤ ልጃቸውና ሰላሳ ወንድሞቻቸው ይገኙበታል።

አሜሪካዊው ጆንሌድፎርድ ምሳ በሚበሉበት ጊዜ ሙዚቃ መስማት አይወዱም፤ ነበር። በካንሳስ ቡክሆርን በሚባለው ሆቴል ምሳ ሲበሉ ሙዚቃውን አናጠፋም ቢሏቸው በሽጉጥ ጥይት መትተው ዝም አሰኙት።

በ1912 ዓ.ም አንዲት ሕንዳዊት ልጅ በዱር ተጥላ ነበር። ይቺ እናቷ ማሳደግ አቅቷት የተጣለችውን ሕፃን አንዲት ተኩላ አሳድጋታለች። ተኩላይቱ ልጅቷን በመመገብ ካሳደገቻት በኋላ ዕድሜዋ ስምንት ዓመት ሲሆን ልጅቱን ሰዎች አገኙዋት። ከዚያም በሚድናፑር ያለው እናት አባት የሞቱባቸው ልጆች ማሣደጊያ ድርጅት ተረከባት። ልጅቱ ሁኔታዋ እንደ አውሬ ስለ ነበረ የተረከባት ድርጅት በሁለት እግርዋ ብቻ እንድትሄድ፤ እንደ ሰው በእጅዋ እንድትበላና እንደሰው እንድትናገር አስተርምሯታል።

በቦምቤይ ነዋሪ የነበሩት ሕንዳዊው አቶ ካሬሽዋሪ ቀንና ለሊት በመቆም አሥራ ሦስት ዓመታት አሳልፈዋል። አንዳንዴ ብቻ ለጥቂት ጊዜ በግንድ ላይ ካሰሩት ተንጠልጣይ ገመድ ላይ አረፍ ይላሉ። በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የሚያርፉት አንድ ጊዜ ብቻ ነው። አሥራ ሦስቱን ዓመት በቁመና ሲጨርሱት ከማንም ጋር አይነጋገሩም ነበር። የሚመገቡትም አትክልትና ፍራፍሬ ነበር።

የፈረንሳዩ ንጉሥ ሄንሪ ፪ኛ ሜሪ ዲ ሜዲቺ የተባለውን ወይዝሮ ሲያገቡ የጣሉት ጥሎሽ በዛሬው የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር ነው።

ከ1319 ዓ.ም ጀምረው እስከ 1364 ዓ.ም ድረስ ፈረንሳይን ይገዙ የነበሩት ዳግማዊ ንጉሥ ጂን የናቫሬውን ንጉሥ ዳግማዊ ቻርልስን ይዘው ለማሰር ብለው በፈረሳቸው እየጋለቡ 246 ኪሎ ሜትር ተጉዘዋል። በዚሁ ጉዞ ፈረሳቸውን አለወጡም ለእረፍትም ብለው ጥቂትም አልቆሙም። ጉዞአቸውንም የጨረሱት ሃያ ሰዓት ጋልበው ነው።

በ1795 ዓ.ም ተወልደው በ1872 ዓ.ም የሞቱት ኤድዊን ኖሪስ በቋንቋ አዋቂነታቸው የተከበሩ እንግሊዛዊ ነበሩ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ፖርቱጋልኛ ወደ ማኦሪኛ ወደ እስፓንኛ ወደ ፔርሺያኛ፤ ወደ ፈረንሳዊኛ ወደ አረብኛ ወደ ጋናውኛ ወደ አኔቱምኛ፤ ወደ ኦቲጂኛ፤ ወደ ቡልጋሪያውኛና፤ ወደ ኢጣሊያኛው ተርጉመዋል።

በበርማ አንድ የመናፍስት ዛፍ አለ። ለእያንዳንዱ የዛፍ ቅርንጫፍ በየሥሩ አንዳንድ ጎጆ ነዋሪዎቹ ይሠራሉ የሚሠሩበት ምክንያት በየቅርንጫፉ አንዳንድ መናፍስት ስለሚኖር መናፍስቶቹ ሁሉ በየቤታቸው ተዝናንተው እንዲኖሩ እያሉ ነው።

በኢጣሊያ አገር ፓድዋ ይኖሩ የነበሩት ኢንሪኮ እስክሮቬኚ ገንዘብ በወለድ የሚያበድሩ ነበሩ። የወለዱ ገንዘብ እየበዛ በመሄዱና ኃጢአት መሆኑም ገብቷቸው ለኃጢአታቸው ማሥተሠሪያ ብለው እስከዛሬው ያለውን ቤተ መቅደስ በ1303 ዓ.ም አሠሩት።

በአውስትራሊያ ውስጥ አራንዳ የሚባለው ጎሳ ሰዎች በበዓላቸው ጊዜ አካላቸውን ፊታቸውንና ጠጉራቸውን በልዩ ልዩ የወፍ ላባ ይሸፍኑበታል የሚሸፍኑት ከክንዳቸው ላይ ደም እያወጡ በገዛ ደማቸው ላባዎቹን በገላቸው ላይ ማጣበቅ ነው።

በሶርያ ደማስቆ፤ አጠገብ አንድ መንደር አለ። መንደሩ ከአንድ ተራራ ጎን በሃ ድንጋዮች እየተፈለፈሉ የተሠራ ነው፤ በዚያ አምባ የሚኖሩ ሰዎች የሚነጋገሩበት ቋንቋ አራማይክ ነው። አራማይክ ክርስቶስ ያስተማረበት ቋንቋ ነው።

በጀርመን አገር በቦርኩም ለመርከበኞች የዳርቻ ብርሃን የሚያመለክት ቤት አለ። ቤቱ የታጠረው በአሣ ነባሪ የጎድን አጥንት ነው።

በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ ሴት አስተማሪ ወይዘሮ ጄን ዊንሺፕ ናት። ዊንሺፕ በ1645 ዓ.ም ተወልዳ በ1707 ዓ.ም የሞተች ናት።

በማዳጋስካር ብቻ የሚገኝ የውሃ ጢንዚዛ እያሉ የሚጠሩት አንድ የጢንዚዛ ዘር አለ። ሴቲቱ የዚህ የጢንዚዛ ዘር እንቁላልዋን የምትጥለው ብወንዱ ጢንዚዛ ጀርባ ላይ ነው። እንቁላሉ እስኪፈለፈል ድረስ ወንዱ ጢንዚዛ አይበርም።

በኒውጊንያ ያሉ የአገሬው ሐኪሞች አንድ የተለየ ቀስት አላቸው። በዚያ ቀስት ጫፍ ላይ መድኃኒት ይደረግና መድኃኒት አድራጊው ያን ቀስ አነጣጥሮ በመተኮስ በበሽተኛው ደም ሥር በመምታት መድኃኒቱን በበሽተኛው ውስጥ ይከታል።

በስዊዘርላንድ እስጥ በባሴል አንድ በፀሐይ ሰዓት የሚለካበት ቦታ አለ። የቦታው ስፋት አሥራ አንድ ዲያሜትር ይሆናል። ከመሐሉ በዓመቱ ወሮች ልክ የተሠመረ ቦታ አለ። ጊዜውን ለማወቅ የሚፈልግ ከወሩ መስመር ሲቆም ጥላው ይነግራል።

ሰባት ክንድ ያህል ርዝማኔ ያለው የፈረስ ጫማ ምስል በጀርመን አገር ባቫሪያ ውስጥ በቅዱስ ሊዎናርድ ቤተ መቅደስ መግቢያ ላይ አለ። በዚያ የፈረስ ጫማ ሥር የሚያልፉ ሰዎች ሁሉ ከፈረስ አደጋ ይድናሉ ተብሎ ይታመናል።

በስዊዘርላንድ ውስጥ ፒላቱስ የሚሉት ተራራ አለ። የዚህ ተራራ ከፍታ 6996 ጫማ ነው በተራራው አናት ላይ አጠር ያለ ትንሽ ደመና ከታየ የአየሩ ሁኔታ መልካም ነው ብለው ያስባሉ፤ በተራራው አናት ላይ በረጅሙ የሚዘረጋ ደምና ካዩ ግን አግሬዎቹ ታላቅ ነጎድጓዳማ ዝናብ እንደሚጥል ይናገራሉ እንደሚሉትም ልክ ይሆናል።

በፓኪስታን ውስጥ ሲንድ በተባለ ቦታ አራል የሚሉት ወንዝ አለ። ይህ ወንዝ በየዓመቱ የሚወርድበትን አቅጣጫ በመለዋጥ ይወርዳል ለስድስት ወር ከኢንዱስ ወንዝ ወደ ማንቻ ሐይቅ ይፈሳል። በተቀረው ስድስት ወራት ጊዜ ደግሞ ከሐይቁ ወደ ወንዙ ይፈሳል።

በአሳም ውስጥ ሎታናጋ የሚሉት ጎሣ አለ። የዚህ ጎሣ ሰዎች በአዳኝነት የታወቁ ናቸው። ከአደኖቻቸው ሁሉ ዝሆን ገዳይ በሚሞትበት ግዚኤ በመቃብሩ ላይ በሣርና በእንጨት የሚሠራ የዝሆን ምስል ይደረጋል። ይህ የዝሆን ምስል በመቃብሩ ላይ የሚቆይበት ጊዜ ሌላ ዝሆን ገዳይ እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ ነው። ሌላ ዝሆን ገዳይ ሞቶ በመቃብሩ ላይ ሌላ የዝሆን ምስል ከተሠራ በኋላ ቀዳሚው ሐውልት ይነሳል።

በአውስትራሊያ ውስጥ ራራትዝበርግ ያለው ቤተ መንግሥት የውስጥ ጣሪያው የተሠራው በሰባት ታላላቅ አናጢዎች ነው። ሰባቱን አናጢዎች ይረዱ የነበሩት ኩሊዎች ሰባት ናቸው። ዕቃዎች ይመላለሱባቸው ጋሪዎችም ሰባት ነበሩ። በነዚህ ሰዎች የሚሠራው ሥራ በሰባት ዓመት ከሰባት ወሩ አለቀ።

በቦርኒዮ ውስጥ የበንጅማርሲን ሴቶች ለመቶ ዓመታት ጊዜ ያደረጉት የነበረው ባርኔጣ ፊታቸውን በሙሉ የሚሸፍን ነበር፤ ይህንንም የሚያደርጉበት ምክንያት የቦርኒዮ ሡልጣን በመንገድ ላይ የሚያዩዋትን ማንኛውንም ቆንጆ ሴት እየወሰዱ ያገቡዋት ስለ ነበር ነው።

በፊሊፒን ደሴት የሚኖሩ የማንዴ ጎሣ ሴቶች ሲሆዱ ቦርሳቸውን በጠጉራቸው ላይ በሚዶ እያበቱ ነው።

በቻድ ውስጥ ሞግሩም በሚባለው መንደር የቤቶቹ በር ቁልፍ ቀዳዳ ይመስላል፤ እንዲያ አድርገው የሚሠሩት የማይፈለገንግዳ አያስገባም ብለው ስለሚያምኑ ነው።

በላቲቪያ ውስጥ በጋሪ ከተማ ያለው የቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ ካለቀ በኋላ በጊዜ ብዛት ከመሐል ወገቡ 61 ሳንቲ ሜትር ዘምሞ ቆሟል።

ከ1900 ዓመታት በፊት በፖምፔ ግዛት በሙሉ ውሾች ሲሞቱ ሐውልት እንዲሠራላቸው የሚያዝ ደንብ ነበር።

በጀርመን አገር በሀልበርስዳት ይኖሩ የነበሩት አቶ ዊሊ በየር ፀሐይ ዘቅዘቅ ስትል በሩኬን ከሚባለ ተራራ ላይ ይወጡና ጥላቸውን በደመና ላይ ማየት ይወዱ ነበር፤ የተራራው ርዝመት 3733 ጫማ ሲሆን አቶ ዊሊ በአየር ጥላቸውን ለማየት እያሉ ተራራውን 650 ጊዜ ወጥተውታል።

በ1874 ዓ.ም ለወታደሮች ተሠርቶ የነበረው ጦር ሲፈልጉ በጨበጣ ይዋጉበታል ካልተመቻቸው ጦሩ ማስፈንጠሪያ ስላለው አስፈንጥረው ብረቱን ጦር ከጠላት ላይ የልቁታል።

በ1776 ዓ.ም የፓሪስ ሴቶች ለኤሌትሪክ ፈልሳፊው ለትልቁ ፈላስፋ ለበኢንጃሚን ፍራንክሊን ክብር እያሉ በባርኔጣቸው ላይ ረጃጅም ሽቦ አስረው እያንጠለጠሉ ይጓዙ ነበር።

በ1809 ዓ.ም ተወልደው በ1889 ዓ.ም የሞቱት ቤንጃሚን ባቢት 100 የፍልስፍና የምስክር ወረቀት ነበራቸው፤ እኚህ ሰው በሳሙና ፋብሪካ ውስት አሠሪ ነበሩ የመጀመሪያውን በፊልም የተቀረጸ ማስታወቂያ ያሳዩ እሳቸው ናቸው፤ የመጀመሪያውም ፊልም የታየው በቴያትር ቤት ውስጥ ነው።

በአንትወርፐ ነዋሪ የነበሩት 1479 ዓ.ም ተወልደው በ1529 ዓ.ም የሞቱት ጆስት ቫን ክሌቭ በዘመናቸው የተከበሩ ትልቅ ስዕል ሳይ ነበሩ፤

ስዕላቸውን ሁሉ ይሠሩት የነበረው በሁለት በኩል ማለት በፊትና በኋላው ስለ ነበር ግድግዳ ላይ የሚሰቀል አንድም ስዕል አልነበራቸውም።

በ1498 ዓ.ም ተወልደው በ1526 ዓ.ም የሞቱት ዝነኛው የኢጣሊያ ወታደሮች መሪ በጦርነት ላይ እግራቸውን ክፉኛ ተመትተው ቆሰሉ፤ ይሄው የተመታው እግራቸው መቆረጥ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኘ፤ ይሄንኑ እግራቸውን ለመቁረጥ አሥር ሰዎች መጥተው «እግርዎ መቆረጥ ስላለበት ልንቆርጥዎ መጥተናል» አሏቸው ጆቫኒ ዴይ ሜዲቺ ሲመልሱ «ታዲያ ይሄ ሁሉ ሰው ምን ያደርጋል» ብለው ጠየቁ «ሲያምዎት እንዳያስቸግሩ ለመያዝ ብለን ነው» ብለው ወድያው ተረባርበው ያዙዋቸው። በዚህ ጊዜ ጆቫኒ አሥሩንም ሰዎች ገፍትረው ከላያቸው አስነስተው እግራቸውን ራሳቸው ቆርጠው ጣሉት።

በአፍሪካ ውስጥ የኮንዴ ጎሣ ባላባት ዘንግ በሰው ቆዳ ይሸፈንና በንቅሳት ሰው መስሎ ይሠራል፤ በራሱም ላይ የሰው ጠጉር ይደረጋል፡

በ1617 ዓ.ም ተወልደው በ1661 ዓ.ም የሞቱት ኢጣሊያዊው አቶ ካርሎ ኢማኑኤል ቪዛኒ በ16 ዓመት ዕድሜያቸ ከፓዱ ዩኒቨርሲቲ በፍስፍና የዶክተርነት ማዕርግ ሲያገኙ በ18 ዓመት ዕድሚያቸው ፕሮፌሰር ሆኑ።

በሕንድ አገር በናሊብጋንጅ አንድ መርዝ የሆነ ውሃ አለ፤ ለመቶ ዓመታት ያህል ወንጀለኞች ከዚያ ውሃ በግዴታ እየጠጡ እንዲሞቱ ይደረግ ነበር።

በ1639 ዓ.ም ተወልደው በ1717 ዓ.ም የሞቱት ኢጣሊያዊው የኔፓል ነዋሪ የነበሩት ዶሜኒኮ ኡሊሺዮ በ19 ዓመት ዕድሜያቸው በኔፓል ዩኒቨርሲቲ የግጥም መምህር ነበሩ፤ በኢጣሊያ የወታደር አካዳሚም ሌክቸረር ነበሩ።

በሰሃራ በረሃ ፌዛን በሚባለው ሥፍራ የሚኖሩ ሰዎች አንድ ሰው የአእምሮ በሽታ ሲያድርበት ረጅም ጉድጓድ ይቆፍሩና በዚያ ጉድጓድ ውስጥ አንድ ሳምንት ሙሉ እንዲቆይ ያደርጉታል፤ በዚህም የአእምሮ ሕመሙ ይተወዋል ብለው ያምናሉ።

በታይላንድ ውስጥ በባንኮክ አንድ መቅደስ አለ፤ መቅደሱ የተሠራበት ሥፍራ ቡድሃ የረገጠው መሬት ስለሆነ ያቺን መሬት ለመሸፈን ተብሎ ነው።

በፈረንሳይ አገር የእግር ተጓዢዎች ማኅበር ፕሬዝዳንት የነበሩት ኢማሌ አንቲኒዬ ስምንት መቶ በእግር ተጓዢዎችን በውድድር አሸንፈዋል፤ ለውድድር የተጓዙትም ሲደመር 960000 ኪ.ሜ ነው።

በቻይና ውስጥ ማይ ቺ ሻን በተባለ ተራራ ላይ ከተራራው ድንጋይ ተፈልፍለው የተሠሩ 196 ቤተ መቅደሶች አሉ፤ እነዚህን ቤተ መቅደሶች ለመሳለም የሚወጣ ምዕመን ሁሉ ለሺህ ዓመታት ያህል በፍርግርግ እንጨት መሰላሎች ላይ እየተራመደ ነበር።

በስዊድን አገር በለንግባይ ይኖሩ የነበሩት አቶ አንድሬስ ጅንግ ከመጀመሪያ ሚስታቸው 7 ሴቶች ልጆች አስወለዱና ሚስታቸውን ፈተትው ሌላ ሴት አገቡ፤ ከሁለተኛ ሚስታቸው ደግሞ 7 ወንዶች ልጆች አስወለዱ።

በቻይና ዋና ከተማ በፔኪንግ በ1860 ዓ.ም ቻይናውያንና ኤሮፓውያን ጦርነት ገጥመው ነበር በጦርነቱ ቻይናውያን አሸነፉ፤ ያሸንፉት ከወረቀት የተሠሩ የነበርና የደራጎን ምስሎች እያወዛወዙ በማስፈራራት ነው።

በሕንድ አገር በካክሪማ የሚኖሩ የአሳም ጎሳ ወንዶች ሁለት እህትማማቾችን ፍቅር ያስያዙ እንደሆነ በግልድማቸው ላይ አራተኛ ነች መስመር ያደርጋሉ።

በኔፓል ተራራ ላይ አንድ ቤተ መቅደስ አለ፤ በዚያ ተራራ ቤተ መቅደስ ለመሳለም የሚሄዱ ሀብታም ሰዎች ተራራውን የሚወጡት በቅርጫት ውስጥ ሆነው በሰው ጀርባ ታዝለው ነው፤ በቅርጫት ውስት ሆኖ ኩሊ ተሸክሞ የሚወጣ የበለጠ ይጸድቃል ስለሚባል ነው ነገሩ የኩሊዎች ወሬ ነው።

በግሪክ አገር በክሮታና ይኖር የነበረው ጥንታዊው የነፃ ትግል ታጋይ በእጁ አንዲት ፍሬ ጨብጦ ይይዝና ማንም ጉልበት ያለው ጀግና ሰው ጣቱን በማስነሳት ፍሬዋን እንዲያስለቅቀው ይጠይቃል፤ ማንኛውም ሰው ታግሎ ሲያቅተው ፍሬዋን ሲለቃት ፍሬዋ ጥቂትም ሳትጎዳ ትገኝ ነበር። እይዚህ ሰው ስም ሚሎ ይባል ነበር።

በኒውዝላንድ ውስጥ ኬሪኬሪ በሚባለው ከተማ ውስጥ ባለው ኬምፐ እየተባለ በሚጠራው ቤት ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች ሦስት ትልውድ 132 ዓመት ሙሉ ፋኖስ እያበሩ በመስኮት ላይ በማድረግ በዚያ አካባቢ ለሚመላለሱ የጨለማ መንገደኞች ብርሃን እንዲያገኙ ያደርጉ ነበር። ኤሌክትሪክ ከተፈለሰፈ በኋላም ያንኑ የቅምቅም አያት ልማድ ሳይተው የልጅ ልጅ ልጅ ልጅ ልጆች በዚያችው መስኮት ላይ አንድ አምፑል አንጠልጥለው በፋኖሱ ምትክ ያበራሉ።

በኒውዝላድ ውስጥ የሚገኙ የማኦሪ ጎሳ ሰዎች ዋሽንታቸውን የሚሠሩት በሰው አጥንት ነው።

በ1893 ዓ.ም ሚያዝያ 6 ቀን አቶ አንዲ ቦዌን እና አቶ ጃክ ቡርኬ በኔዋርሊያንስ ውስጥ ቦክስ ተጋጥመው ግጥሚአይው ሚያዝያ 6 ቀን ከምሹት 3 ሰዓት ከሩብ ሲሆን በኦሊምፒክ ክበብ ውስጥ ተጀምረ፤ በማግስቱ ሚያዝያ 7 ቀን ከለሊቱ በአሥር ሰዓት ከ34 ደቂቃ የቦክሱ ጨዋታ በዳኛው ትእዛዝ እንዲቋረጥ ተደረገ፤ እነዚህ ሁለት ሰዎች 7 ሰዓት ከ19 ደቂቃ ሙሉ ቦክስ ተጋጥመው የተደባደቡት 110 ዙር ነው።

ይህ ጓንት አድርጎ በሪንግ ውስጥ በተደረጉ ጨዋታዎች እስከዛሬ ድረስ በቦክስ ታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው ነው፤ ስለዚህ ጨዋታ «ፖሊስ ጋዜት» የተባለው የፖሊስ ጋዜጣ ሚያዝያ 7 ቀን 1893 ዓ.ም ባአወጣው ቁጥሩ እንዲህ ሲል አትቷል።

«......ቦዌንና ቡርኬ በኦርሊየንስ ውስጥ ጨዋታው በኦሊምፒክ ክበብ ሐሙስ ማታ የጀመሩትን የቦክስ ውድድር አርብ ጨረሱት፤ ጨዋታው አርብ ዕለት በ110ኛው ዙር እንዲቆም ያደረጉት ዳኛው አቶ ጃክ ዳፊ ናቸው ዳኛው ጨዋታውን ሲያስቆሙ ውድድሩ እንዳልተደረገ ይቆጠር ብለው ነው...... ጥቂሩ ቦዌን ውድድሩ እስከመሸናነፍ እንዳያቋርጥ ፈልጎ ነበር፤ ግን የቡርኬ ሁለቱም የእጁ አጥንቶች ተሰብረው ነበርና ዳኛው ውድድሩ እንዲቋረጥ አደረጉ።

«ቦዌን የኒውኦርሊያንስ ሰው ነው፤ ቡርኬ ደግሞ የቴክሳስ ሰው ነው፤ እነዚህ ተወዳዳሪዎች ሊከፈላቸው የነበረው ገንዘብ 2500 (የአሜሪካ ብር)

ነበር። ለተሸነፊው 500 ይሰጥና ለአሸናፊው ሁለት ሺ ብር ሊሰጥ ነበር፤ ውድድሩ የደቡብ አገሮች የአነስተኛ ሚዛን ሻምፒዮን ማጣሪያ ነበር።

«.......አዳራሹ በተመልካች ተሞልቶ ነበር፤ ተወዳዳሪዎቹ ስገነት ላይ ሲወጡ ጭብጨባው ነጎደ፤ ጊዜው ሐሙስ ከምሽቱ 9 ሰዓት (በኛ አቆጣጠር 3 ሰዓት) ተኩል ነበር፤ በ25ኛው ዙር ላይ ቦዌን ተዘረረ፤ ጥቂት እንደተቆጠረበት ተነሳ፤ ከዚያ ጀምሮ እስከ 45ኛው ዙር ድረስ ውድድሩ ያልተሟሟቀ ነበር።

«......በ48ኛው ዙር ግጥሚያ ጊዜ ተመልካቹ «ቤት ደጊቱ ቤት» (ሆም ስዊት ሆም) እያለ ጮኸ እኩለ ለሊት ሲሆን ብዙ ተመልካች ወጣ፤ እንዲህ ያለ የቸከ ጨዋታ ብናይም ጨዋታው ሲያበቃ ሁለቱም ተጨዋቾች ፈገግታ እያሳዩ ከመጫወታቸው ሜዳ ወጡ......» በማለት ጽፏል። ይሔ በዚሁ ይቁምና የቴዲንና የቦብን ላጫውቶት።

በእንግሊዝ አገር በዌልስ ውስጥ በሜስቴግ፤ መስከረም 2 ቀን 1957 ዓ.ም እንግሊዛዊው ቴዲ ባርከር እና ናይጄሪይዊው ቦብ ሮበስትስ የቦክስ ግጥሚያ አድርገው ነበር፤ ቴዲ አንድ ጊዜ ቦብን እንደመታው ጭዋታው በኖክ አውት ተፈጸመ። ይህ ግጥሚያ የቆየው የመጀመሪያዋን ሴኮንድ ብቻ ነው፤ ዳኛው የጨዋታውን ማለቅ ያስታወቁትና ጨዋታውን የዘጉት በሕጉ መሥረት ሳይቆጥሩ ነው። ነገር ነገርን ያመጣል እንደሚሉት የቦክስ ጉዳይ ከተነሳ ጥቂት ላጫውቶት።

የቦክስ ጨዋታ የጀመሩ ግሪኮች እንደሆኑ ይነገራል። እንዳሁኑ ጊዜ በጓንቲና በሕግ የሚመራ አይሁን እንጂ በባዶ በቡጤ እየተደባደቡ ኀበዙን ይለዩበት የነበረ የጎረምሶች ጨዋታ ነበር። እንዲህ ዓይነቱ የቡጢ ድብደባ ጨዋታ በአገራችንም የተለመደና የተወደደ ነበር፤ አሁን ግን እየተተወና እየተረሳ ሔድዋል፤

ከቦክሰኞች ታሪክ ውስጥ አንዳንድ ሊያዩዋቸው የሚገቡ ፎቶ ግራፎች የሚቀጥለው ገጽ ላይ ላሳይዎ።

በአገራችን ለነበረው በባዶ እጅ የመደባደብ ቡጢ ነግሬዎታለሁ ይህ የባዶ እጅ ማለት ያለጓንቲ የመደባደብ ጨዋታ በኛ አገር ብቻ ሳይሆን በሌሎች

አገሮች ሁሉ ነበር፤ ከላይ የሚያዩት ፎቶ ግራፍ በባዶ እጅ የመደባደብ ቡጢ ነው፤ ጨዋታው ሐምሌ 29 ቀን 1889 ዓ.ም በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ፖርት ኤልሳቤጥ በተባለው ቦታ ተጀመረ፤ ተጋጣሚዎቹ ጃክ ኩፐር እና ዎልፍ ቤንዶፍ ነበሩ፤ ለአሸናፊው ሰው 22500 የአሜሪካ ብር ሊሰጥ ነበር፤ 27 ዙር ተጫውተው ተለያዩ።

የአየርላዱ ረጅም ሰው ጂም ከአጭሩ ጆይ ባክሲ ጋር የባዶ እጅ ውድድር አድርገው ረጅሙ አጭሩን ቁልቁል እየያዘው ሲያጠቃ ቢቆይም በመጨረሻው አጭሩ ጆይ አሸንፏል።

በኒውጊኒያ ውስጥ የፓፑዋ ተወላጆች በውሃ ውስጥ እየዋኙ በባዶ እጃቸው አሣ መያዝ ይችላሉ።

ወታደር ጌስኮር በፈረንሳይ ጦር ሠራዊት ውስጥ ተቀጥሮ ስድስት ዓመት ሙሉ በማገልገል የአምሳ አልቅና ማዕርግ አገኘ፤ በ1812 ዓ.ም በጦርነት ላይ ቆስሎ ሲታከም ሴት ሆና ተገኘች።

በ1548 ዓ.ም ተውለደው በ1602 ዓ.ም የሞቱት የታወቁት ታላቁ ስዕል ሳይ ኮርኔሊስ ኬቴል የተከበሩ ታላላቅ ስዕሎቻቸውን የሳሉት በብሩሽ ሳይሆን በጣቶቻቸው እንደ ብሩሽ በማድረግ ነው። እኚህ ታላቅ ስዕል ሳይ ስዕሎቻቸውን በሙሉ ጣታቸውን በቀለም እየነከሩ በመሳላቸው በሰዓሊዎች ታሪክ ውስጥ በዚህም በኩል ይደነቃሉ።

በሕንድ አገር የናቫጆ ሴቶች ጠጉራቸውን የሚቦርሹት በሰንበሌጥ ሣር ነው።

ዛሬ በብሪትሽ ሙዚየም ውስጥ የሚገኝ አንድ ምንጣፍ አለ፤ ይህ ምንጣፍ ሰላሳ ዓመት ሙሉ ተሠርቶ ያለቀ በ1539 ዓ.ም ነው፤ ምንጣፉ ሰላሳ አራት ጫማ ተኩል ርዝማኔ ሲኖረው ስፋቱ ደግሞ 17 ጫማ ተኩል ነው፤ ይህ ምንጣፍ ሲሠራ ይስለበት ቋጣራ 33.037.200 ነው፤ እያንዳንዱ በሰው እጅ የተቋጠረ ነው፤ አሁን በእኛ 2.500.000 ዋጋ ያወጣል።

የአሜሪካ ሕንዶች የሚሲሲፒን ወንዝ ለማቋረጥ ከጎሽ ቆዳ እንደ ቅርጫት ያለ ጀልባ ይሠሩና ዋና የሚችል ፈረሳቸውን በወንዙ ውስጥ ለቀው ፈረሱ ሲሄድ እነሱ ጭራውን ይዘው ይከተላሉ።

በፖርቱጋል ውስጥ ኢቮራ በሚባል አምባ ይኖሩ የነበሩ ሚቲውስ ሚናስ እይሚባሉ ባልና ሚስት ሁለቱም ጥር 1 ቀን የተወለዱ ናችው ሁለቱም 1801 ዓ.ም ተወልደው 1900 ዓ.ም ታኅሣሥ 31 በጥቂት ደቂቃዎች ልዩነት ተከታትለው ሞቱ።

በጃፓን አገር በኩዩሹ ቀበሌ በአሶ ተራራ ላይ አንድ ከመሬት ውስጥ የሚወጣ የእንፋሎት ጭስ አለ፤ ብዙ ጊዜ ጭሱ ሲንቧለል የሚታየው የሰው መልክ ቅርጽ እየያዘ ነው።

ፈረንጆች ሊምፔት የሚሉት የአሳ ዘር ከአካሉ ምላሱ ሦስት እጅ ይበልጣል።

በኒው ሜክሲኮ በዳቲል ይኖር የነበረ ተማሪ ሪቻርድ ማካስተር በየቀኑ ተማሪ ቤት የሚመላለሰው 120 ኪሎ ሜትር መንገድ በአውቶብስ በመመላለስ ነው፤ የዚህ ልጅ የ7 ዓመት መመላለስ የዓለምን ዙርያ መዞር ነው

በእንግሊዝ አገር በሆልብሩክ ይኖሩ የነበሩት ቄስ ሩዝ ዌርስቲድ በየእሑዱ በአምስት የተለያዩ አብያተ ክስርስቲያናት ያስቀድሳሉ፤ አምስቱን አብያተ ክርስቲያናት ለማዳረስ በየእሑዱ 26 ማይል ይጓዙ ነበር።

በፈረንሳይ አገር በሮቼ ይኖሩ የነበሩት ቻርስ ደ ቮልቬር አንዱ ልጃቸው በመንፈሳዊነቱ ቅዱስ ተብሏል፤ አንዱ ልጃቸው ደግሞ ቄስ ሲሆን የተቀሩት ሰባት ሴቶች ልጆቻቸው መነኮሳት ናቸው።

በ1774 ዓ.ም የተወለዱት አቶ ጆሴፍ ፐለመር አንዲት ልጅ ወደዱና ለጋብቻ እየቋት፤ ልጅቱ አላገባም ብላ እምቢ አለች፤ በዚህ ምክንያት ተናደው በኒው ሀምፐሻየር ያለችውን ቤት መኮቶቹን በሙሉ ዘጋግተው ዓለም በቃኝ ብለው የፀሐይ ብርሃን ሳያዩ ኖርወ በ1862 ዓ.ም ሞቱ።

በዚሁ በአፍሪካ ውስጥ በሲሬናይካ በሚገኘው በጊጁራ አንድ መስጊድ አለ፤ መስጊዱ የሚሠራ ኮባ ከሚመስል ቅጠል ነው፤ በዚያ ሥፍራ መስጊዱ

ከተመሠረተ 150 ዓመት ሲሆነው በዚህ ዘመን ውስጥ 450 ጊዜ አዲስ እየሆነ ተሠርቷል።

በ1741 ዓ.ም ተወልደው በ1820 ዓ.ም የሞቱት እንግሊዛዊው የግብርና ሊቅ አርዘር ያንግ በ1788 ዓ.ም በፈረስ ላይ ሆነው 3 ወር ሙሉ በመጓዝ የፈረንሳይ ግዛት አቋረጥወአል፤ እኒህ ሰው ፍፁም ዕውር ነበሩ።

ማቼል ዱራክ የተባለ ከብት ነጂ ሁለት ሺ ከብቶች እየነዳ በአውስትራሊያ ከኩንስላንድ እስከ ኪምበርሌይስ ድረስ አራት ሺ ኪሎ ሜትር ተጉዞአል፤ መሪ በሌለውና በማያውቀው መንገድ ሐምሌ 29 ቀን 1883 ዓ.ም ጉዞ ጀምሮ መስከረም 17 ቀን 1885 ዓ.ም ጉዞውን ጨረሰ።

የሱፍ ጠጉር ያላቸው በጎች ከክረምት ይልቅ በበጋ ጠጉራቸው የበለጠ ያድጋል።

በምሥራቅ ሚቆዶኒያ እይሚኖሩ ሴቶች በየዓመቱ የነፃነት ቀን እያሉ ጥር 7 ቀንን ያከብራሉ፤ በዚያ ቀን ሴቶቹ በየጎረቤቱና በየቡና ቤቱ እየዞሩ ሲጫወቱና ሲደሰቱ ይውላሉ። ባሎቻቸውን ግን ከቤት ሆነው ቤት በመጥረግ አልጋ በማንጠፍ ምግብ በመሥራትና በጠቅላላው የሴቶች ሥራ ሲያከናውኑ ይውላሉ።

ግብጾች ከፔርሺያኖች ጋር ጦርነት አደረጉና ግብጾች አሸንፈው ፔሊሱዩም የተባለችውን የፔርሺያኖችን ከተማ ያዙ በዚህ ጉዳይ የተበሳጩት የፔርሺያው ንጉሥ ካምቢሴስ ግብጻውያን በድመት እንደሚያመልኩ ያውቁ ነበርና ድመት ገድለው በከተማው አጥር በግንቡ ላይ የድመቷን ሬሳ ግብጻውያኖቹ ላይ ጣሉባቸው። ግብጻውያኖቹ በዚህ ተደናግጠው የድመት ሬሳ ያዩበትን በድል አድራጊነት አሸንፈው የያዙትን ከተማ ለቀው ወጡ፤ ፔርሺያውያኖችም በጦርነት የተወሰደውባቸውን ከተማ በድመት ሬሳ አስለቅቀው ያዙ።

ከ375 ዓመት በፊት ቅዱስ ፊሊፕ ዓይንናቸው ላይ ያደርጉት የነበረው መነጥር ዛሬ በኢጣሊያ አገር በሮም ከተማ በቅዱስ ፊሊፕ ቤተ ክርስቲያን ተቀምጧል።

እውቅ የነበረው አስማተኛ ሲመስ በርክ በመጀመሪያ በገመድ ተተብትቦ ይታሰርና ከዚያ በኋላ በእርጥብ ስልቻ ውስጥ ይጨመራል፤ የስልቻው አፍም

ደኅና ተደርጎ ይታሰራል፤ ሰዎች በሸክም ይወስዱትና ከባህር ውስጥ ይቸምሩት በጥቂት ደቂቃ ውስጥ የታሠረበትን ፊቶ ከስልቻው ውስጥ ከባሕሩ ውስጥ ይወጣ ነበር።

በኢንዶኔዚያ ውስጥ በባሊ ደሴት መናፍስት ቀን የምት ሲዞሩ ውለው ለሊት የሚያርፉበት ብለው 11 ፎቅ ያለው ቤት እየሠሩ ያስቀምጡላቸዋል።

አራት የደች ተወላጆች በኔዘርላንድ ውስጥ ገወሌም በተባለው ቦታ ከቅዱስ ጴጥሮስ ተራራ ላይ ካንድ ዋሻ ውስጥ ገብተው ጥንታዊ ታሪካችን ሲያጠኑ ለመመለስ የዋሻው መንገድ ጠፍቷቸው በዚያው ቀሩ፤ ፈላጊዎች ፈልገው ሲያገኙዋቸው ሬሳቸው ሲታይ እያንዳንዳቸው የእጆቻቸው ጣቶች በልተዋቸው ሞተዋል።

በውስዊዘርላንድ ያእልው የሞርስበርግ ገዳም የግድግዳው ውፍረት 16 ጫማ ተኩብ ነው።

በ1877 ዓ.ም የተወለደው የሜክሲኮው ሽፍታ ኢሚሊያኖ ዛፓታ 1.100 ሰዎችን በሽፍትነት ጊዜው ከጓዶቹ ጋር ገድለዋል፤ ከእነዚህ ማቾች መሐል 250 ሰዎችን የገደለው ራሱ ኢሚሊያኖ ነው፤ ኢሚሊያኖ እንዲህ በሕዝብ ሲጫወት የነደዳት ሚስቱ ኢሚሊያኖን ገደለችው፤ ይቺ ሚስቱ 26ኛይቱ ነበረች።

በቦርኒዮ አንድ አዳኝ ሰው ሲሞት መቃብሩ እንደ ጋሪ የሚሠራ ባለእግር ነው፤ በዚያም ላይ ልዩ ልዩ የማደኛ መሣሪያዎች ይደረጉበታል በሄደበት ዓለም አድኖ እንዲበላ ነው፤ ይላሉ።

በአውስትራሊያ ውስጥ ሆቸስተርዊዝ በሚባለው መንደር አንድ የጥንት ቤተ መንግሥት አለ፤ ያ ቤተ መንግሥት ዛሬ ሆቴል ቤት ሆንዋል፤ በዚያ ሆቴል ቤት ውስጥ የሚያሳልፉት ቦዮች የጥንት ወታደሮችን ከብረት የሚሠራውን የጦር ልብስ እየለበሱ ነው።

በፎርሞዛ ውስጥ ማቫያያ በሚባለው ጎሣ በራስ ላይ ላባ የሚያደርጉ የታወቁ ጀግኖ ብቻ ናቸው፤ በሌላ በኩል ጀግንነት ቢያጡ በትግል ያሸነፉ ሰዎች መሆን አለባቸው።

በ289 ዓ.ም ተወልደው 399 ዓ.ም የሞቱት የጃፓኑ ንጉሥ ኒንቶኩ ቴኖ በ110 ዓመታቸው ሲሞቱ 86 ዓመት በዙፋን ላይ ቆይተው ነው።

በሰሜን አፍሪካ የሚኖሩ ታርጉያ የሚባለው ጎሳ ሴቶች የሚያጌጡት ከብር በተሠራ ጌጥ ብቻ ነው፤ ከወርቅ በተሠራ ጌጥ ማጌጥ ገደቢስ ነው ይላሉ።

በኢጣሊያ አገር ፓየስተም በተባለ ቦታ በቁፋሮ ተገኝቶ ነበር፤ አሥራው የተቀበረው ከሁለት ሺ ዓመት አት በፊት ነው በንሥራ ውስጥ የተገኘው ማር መዐዛውን ሳይለውጥ እንደ ትኩስ ማር ይጣፍጥ ነበር።

የፈረንሳዩ ፈላስፋ ቮልቴር ዕድሜው 80 ዓመት ሲሆነው በቀን 72 ሲኒ ቡና ይጠጣ ነበር። ከ4 ዓመት በኋላ ሞተ።

በካናዳ ውስጥ አልቤርተ ይኖር የነበረው ዊልያም ዋትሰን ሲወለድ ጀምሮ እጁ ፍፁም ሽባ ነበር፤ ቢሆንም እንኳ ሁለት እጆቹ ሽባ ቢሆኑም ጢሙን መላጨት ልብሱን መልበስ ምግቡን መመገብ ፈረስ መጋለብ መዋኘት ገና መጫወትና በበረዶ ላይ ሸርተቴ መንሸራተት ይችል ነበር፤ ይህን ሁሉ የሚያደርገው እግሩን እንደ እጅ አሰልጥኖ እንጂ በእጁ አልነበረም።

በምዕራባዊ አውስትራሊያ የወርቅ ማዕድን ባለበት ሌክውድ በተባለ ሥፍራ ያለው የሠራተኞቹ መኖሪያ ፖስታ ቤታቸው የፖሊስ ጣቢያቸውና ሱቆቹ ሁሉ ያሉት በባቡር ላይ ነው።

የፈረንሳዩ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት ሳልሳዊ ናፖሊዮን በጣም ሲጃራ አጫሽ ነበሩ በቀን ቢያንስ እስከ 50 ሲጃራዎች ድረስ ያጨሱ ነበር፤ ፫ኛው ናፕሊዮን በ1909 ዓ.ም ተወልደው በ1873 ዓ.ም ሞቱ።

በ1430 ዓ.ም ተወልደው በ1556 ዓ.ም የሞቱት በስዊዘርላንድ ውስጥ በሳን ኒክላውስ ይኖሩ የነበሩት አቶ ኅንስ ሶመርማተር ዕድሜያቸው አንድ መቶ ዓመት ሲሆን ለሁለተኛ ጊዜ ሰላሳ ዓመት ዕድሜ ያላትን ሴት በሚስትነት አገቡ፤ በቀጠለው ዓመትም የልጅ አባት ሆኑ፤ በጠቅላላው 126 ዓመት ኖረው ሞቱ።

በ1768 ዓ.ም ተወልዶ በ1830 ዓ.ም የሞተው ኒኮሎ ጂኦሳፋቴ ቢያጂሊ በአሥራ ስድስት ዓመት ዕድሜው ከሮማ ዩኒቨርስቲ የፕሮፌሰር ማዕረግ አግኝቷል።

በኦሃዮ በራንዶልፍ ይኖሩ የነበሩት አቶ ዎልተር ዲክሰን በተወለዱ በሰባት ዓመት ዕድሜያቸው መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር በንባብ ወጥተውታል።

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መርከበኞች ትንባሆን እንደ ኤሮፓ ባመጡ ጊዜ ይጨስ የነበረው ቅጠል ይሸመለልና በቅጠሉ ውስጥ ትንባሆው ተጨምሮ በእሳት ተለኩሶ እንደ ጋያ በመሳብ ነበር፤ ትንባሆ ማጨስ፤ ለዓለም የተዳረሰው ከአሜሪካ ሕንዶች ተወስዶ ነው።

በ1950 ዓ.ም ሚያዝያ 15 ቀን ቅዳሜ ዕለት ሬይልተን የተባለው አውቶሞቢል እንግሊዝ አገር ተሠርቶ ለኤግዚቢሽን ኒውዮርክ ከተማ ሲገባ ታላቅ አቀባበል ተደርጎለት ነበር፤ ሬይልተን በዘመኑ የኛ ብር ሂሳብ በ250.000 ብር የተሠራ ሲሆን በዘመኑ ተወዳዳሪ የሌለው ሯጭ መኪና ነበር።

በ1949 ዓ.ም በኡታህ ውስጥ በሰዓት 644 ኪሎ ሜትር ተኩል በመብረሩ የተደነቀ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት መኪና ነበር፤ ከአዲስ አበባ አሥመራ በአንድ ሰዓት ከ40 ደቂቃ ይገባል ማለት ነው፤ እንዲያው ምሳሌውን ማለቴ ነው እንጂ በኢትዮጵያ መንገድ ላይ ጠመዝማዛ መንገድ በሚበዛበት አገር ያን ያህል ሊሮጥ አይችልም።

ሬይልተን ርዝመቱ ስምንት ሜትር ከ74 ሳንቲ ሜትር ሲሆን የጎኑ ስፋት ደግሞ ሁለት ሜትር ከ13 ሳንቲ ሜትር ነው፤ ጉልበቱ የ2600 ፈረስ ጉልበት ነው፤ የሚጭነው ግን አንድ ሰው ብቻ ነው፤ እሱም ነጂው ነው።

ጆን ኮብ የተባለው ነጂ በመኪናው ጭንቅላት (ቀስቱን ይዩ) በኩል ገባና ተቀመጠ ሞተሩን አስነሳ፤ በሰዐት 224 ኪሎ ሜትር እስቲሔድ ድረስ በአንደኛ ማርሽ ብቻ ተጉዞ ወደ ሁለተኛ ለወጠ፤ በሁለተኛው ማርሽ በሰዐት 400 ማይል ወይም 640 ኪሎ ሜትር እስቲደርስ ድረስ ተጓዘ።

ይህ መኪና በአሁን ግዜኤ የፈጣንነቱን ደረጃ ተነጥቋል ነጣቂው «ዘ ብሉ ፍሌም» (ሰማያዊ ነበልባል) የተባለው አውቶሞቢል ነው፤ ይህ አውቶሞቢል በ1970 ዓ.ም ጥቅምት 23 ቀን በኡታህ ውስጥ በሰአት 1046 ኪሎ ሜትር ከ400 ሜትር ሮጧል፤ ይህ ዘ ብሉ ፍሌም የተባለው መኪና በሰዐት 1440 ኪሎ ሜትር ወይም 900 ማይል መሮጥ እንደሚችል ሆኖ የተሠራ መሆኑ ፈጣሪዎቹ ተናግረዋል ስለ ረጅሙ መኪና ደምኅ ጥቂት ልንገርዎት፤ ይሄ የሚያዩት ቡጋቲ ሮያል የተባለው መኪና ርዝመቱ ሰባት ሜትር ከሰላሳ ሳንቲ ሜትር ነበር የዚህ መኪና ዘር በ1927 ዓ.ም ስድስት ብቻ ተሠርተው አበቃ።

በመኪና ዘር ውስጥ በዋጋ ውድነቱ የታወቀው ፕሬዘዴንሺያል ሊንከልን የተባለው መኪና ነው የዚህ መኪና ዋጋ በዘመኑ ሂሳብ ወደ ኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ አምሳ ሺ (1.250.000) ብር ነው፤ የዚህ መኪና ጠቅላላ ክብደቱ ስድስት ሺ ኪሎ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ ሁለት ሺህ ኪሎ የሚከብደው ለጥይት መከላከያ የገባለት መሣሪያ ነው፤ ይህ አውቶሞቢል ካለው የጥይት መከላከያ የብረትና የመስተዋት መሣሪያ ሌላ ለምሳሌ አራቱም ጎማው በጥይት ቢመታና ቢተነፍስ በሌላው ተጠባባዊ ጎማው በሰዓት ሰማንያ ኪሎ ሜትር እየሮጠ መሄድ ይችላል የውስጡ መቀመጫም ቢሆን የተሠራው እንደ ሌሎች አውቶሞቢሎች ሳይሆን በዚህ በፎቶ ግራፉ ላይ እንደሚያዩት ሆኖ የተሠራ ነው፤ ይህ አውቶሞቢል እንደማንኛዎቹም ተሠርቶ የሚሸጥ ሳይሆን በግል ትእዛዝ የሚሠራ ነው። ከአውቶብስ ዘር ትልቅ አውቶብስ የተሠራው ደቡብ አፍሪካ ውስጥ ነው፤ ይህ ጆሀንስበርግ ከተማ ውስጥ የተሰራው አውቶብስ ሃያ አንድ ሜትር ርዝማኔ ያለው ሲሆን አንድ መቶ ስልሳ ሰዎችን በአንድ ጊዜ አሳፍሮ መጓዝ የሚችል ነው።

እስካሁን ከተሠሩት ትልልቅ የጭነት መኪናዎች መሐል ተወዳዳሪ የሌለው ቪን ኮን የተባለው መኪና ነው፤ ይህ እምኪና በቴክሳስ ውስጥ በዳሰሳ ባለው የመኪና ፋብሪካ የተሠራ ሲሆን 1850 ኩንታል ለመጫን ይቻላል አሥራ ሁለት ሲሊንደር ያለው ሆኖ የ2600 ፈረስ ጉልበት አለው፤ 14 ሜትር ከሩብ ርዝማኔ ሲኖረው ስፋቱ ደግሞ 9 ሜትር ነው ዋጋው በኛ ብር ሲመነዘር 1.750.000 (አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺ ብር) ነው ወደ

አገራችን አንዱን መኪና ለማስመጣት ከነቀረጡ ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ሳያወጣ ይቀራል?

ከአውቶሞቢል ዘር ትልቁ ወይም ከባዱ አውቶሞቢል በ1965 ዓ.ም የተሠራው ኳድ ኤ ዋን የተባለው የእሽቅድድም አውቶሞቢል ነው፤ የዚህ አውቶሞቢል አራት እግሮቹም በማርሽ የሚንቀሳቀሱ ሲሆኑ አውቶሞቢሉ በጠቅላላ የሚንቀሳቀሰው በአራት የአይሮፕላን ሞተሮች ነው፤ የዚህ መኪና ዘር በብዛት አልተሠራም ለተሽቀዳዳሚዎች እንኳን እንደሚበእቃ ሆኖ አልተሠራም። ፈረንሳዮች ለሰሃራ በረሃ መገልገያ ብለው የሠሩት ካሚዮንም ግዙፍ ነበር፤ ይህ ፈረንሳዮች ቤርሌት የሚሉት ካሚዮን የዲዜል ሞተር ያለው ሲሆን 890 ኵንታል ክብደቱ ግን 1870 ኵንታል ነው፤ ይህ መኪና አሥራ ሁለት ሲሊንደር ያለው ሲሆን የስድስት መቶ ፈረስ ጉልበት አለው፤ ዋጋዋ በኛ ብር ሂሳብ ሲታሰብ 385.000 ብር ነው።

ስለ ረጅሙ ካሚዮን ደግሞ ጥቂት ላጫውቶት፤ ረጅሙ መኪና የሚገኘው በአሜሪካ አገር ነው፤ የዚህ መኪና ርዝመት 191 ሜትር ነው፤ ይህ መኪና ያሉት ጎማዎች 54 ናቸው፤ ባጭሩ አምሳ አራት ተሽካርካሪ እግሮች አሉት ማለት ነው። ይህ ለአሜሪካ ወታደሮች ማጓጓዣ የተሠራው ካሚዮን ጠቅላላ ክድበቱ 4500 ኵንታል ነው፤ የሚነዳው በስድስት ሰዎች ሲሆን የመጨረሻ ፍጥነቱ በሰዓት ሰላሳ ኪሎ ሜትር ነው፤ በአንድ ግዜኤ የሚሞላው ነዳጅ 7828 ጋሎን ነው፤ ይህን መኪና ሠርቶ ለማውጣት የሚጨርሰው ገንዘብ 9.387.500 (ዘጠኝ መቶ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሺ አምስት መቶ) የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ነው።

እስካሁን የተወራልዎት የመኪና ታሪክ የተወለደው ወይም እየተሻሻለ የመጣው ከዚች መኪና ነው፤ ይህቺ እምኪና በ1885 ዓ.ም በጀርመን አገር የተሠራች የመጀመሪያዋ በነዳጅ ኃይል የምትሄድ መኪና ነች፤ ይህቺ መኪና ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራት ጀርመናዊው ካርል ቤንዝ ነው፤ ይቺ የመጀመሪያይቱ አውቶሞቢል ሦስት እግሮች ያሏት ናት፤ ክብደቷ 275 ኪሎ ሲሆን በሰዓት መጓዝ የምትችለው ከስምንት እስከ አሥር ማይል ነበር፤ ይህቺ የመጀመሪያይቱ አውቶሞቢል ዛሬ እኔ እንዳየኋት በጀርመን አገር በሙዚየም ውስጥ ተቀምጣ በብዙ ጎብኚዎች ትጎበኛለች።

ዛሬ በአገራችንም ሆነ በመላው ዓለም የሚገኘው ማርቸዲስ መኪና ስሙ ማርቸዲስ ቤንዝ ነው፤ ይህም ለዚች የመጀመሪያይቱ የነዳጅ አውቶሞቢል ፈጣሪ ለካርል ቤንዝ መታሰቢያ ተብሎ የተሰጠ ነው። በዚህ ላይ የምጨምርሎት መኪናዎቹ ሁሉ በፈጣሪያቸው ስም እንደሚጠሩ ያውቃሉ? ፎርድ፤ በሚስተር ፎርድ ስም፤ ሲትሮይን በፈረንሳዊው በሙሴ ሲትሮይን ስም ይጠራሉ፤ ስለዚህና ስለሌሎቹም የመኪና አፈጣጠር ጉዳይ በሌላ ጊዜ በሌላ መጽሐፍ እንደማጫውቶት ተስፋ አደርጋለሁ። እግዚአብሔር የፈቀደና ዕድሜ የተገኘ እንደ ሆነ ነው። ላሁኑ ይበቃ።

ጀርመናዊው ኸርማን ጎርነር በአውራ ታቱ ላይ አምሳ ኪሎ ያህል የሚመዝን ብረት አንጠልጥሎ ግድግዳ ላይ ስሙን መጻፍ ይችል ነበር።

ዝነኛዋ የአቴንሷ ተጨዋች አግሊያስ በቀን የምትመገበው ስድስት ኪሎ ሥጋና አራት ኪሎ ዳቦ ነበር፤ ይህ ካደረገች በኋላ ሲመሽ 3 ሊትር ተኩል ያህል የወይን ጠጅ ጠጥታ ትተኛለች።

በ1631 ዓ.ም የተወለዱት በእንግሊዝ አገር በኬንት ኗሪ የነበሩት እመት መርጋሬት ፊንች ለአርባ ዓመታት ያህል በአንድ ሥፍራ ተቀምጠው እግራቸውን ሳይዘረጉ እንዳጠፉት ኖሩ፤ በኋላ 1740 በ109 ዓመታቸው አልዘረጋ በማለቱ አራት መአዘን የሆነ ሳጥን ተሰርቶ በዚያ ውስጥ ተጨምረው ተቀበሩ።

በእንግሊዝ አገር በእስክሪግ ነዋሪ የነበሩት ጄምስ ሪቻርድሰን አንዲት ባርኔጣና አንዲት ቧት ጫማ 42 ዓመት ሙሉ ሌላ ሳይለውጡ አድርገዋል ባርኔጣና ጫማው 42 ዓመት ሙሉ በየቀኑ ይወለወሉ የነበረው በአንዲት ጨርቅ ብቻ ነበር።

በእስኮትላንድ ውስጥ በሎቸሺል ለልዑል ቻርሊ መታሰቢያ ሐውልት ሲሠራ የሐውልቱ ሥራ እንዳለቀ ሰሪው አሌክሳንደር ማክዶናልድ ስለሞተ ሐውልቱ ለሁለቱም መታሰቢያ ተደረገ።

በእንግሊዝ አገር በክሪክላድ ይኖር የነበረው ጅጆን ማልደንሐል 25 ኪሎ ያህል የሚመዝን ብረት በክር ከአውራ ጣቱ ላይ አንጠልጥሎ ከጣሪያ ላይ ስሙን መጻፍ ይችላል።

በማላያ የፓሃንግ ሰዎች እርጥብ ሸንበቆ በመሰንጣጠቅ ክራር ይሠራሉ፤ እንደ ጅማት ሆኖ ድምፅ የሚሰጠው በቀጭኑ የሚሰነጥቁት ራሱ ሸንበቆው ነው።

በፈረንሣይ አገር የቅዱስ ፍሉር ካቴድራል አለ፤ ካቴድራሉ ለአራተኛው መቶ ዓመት ያህል የላይኛው ፎቅ ወህኒ ቤት ሲሆን የታችኛው ክፍል ደግሞ ጫማ ሰፊዎች ለክብራቸው በየዓመቱ ግብር ያደርጉበት የነበረ ታላቅ የመገባበዣ አዳራሽ ነበር።

በፈረንሳይ አገር ቫሬንስ በሚባል ሥፍራ አንድ ዛፍ ውስጥ የተዋጠ የጀርመን መውዜር ጠመንጃ አለ፤ እንደሚነገረው በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ጊዜ አንድ ወታደር ጠመንጃውን አንድ ዛፍ ላይ አስደግፎ ጥሎት ሄደ፤ ዛፉ ሲያድግ በጠመንጃው ላይ ስላደገ ዛሬ ዛፉ ጠመንጃውን ውጦት ይታያል፤ በዚሁ ላይ የምጨምርልዎ መውዜር ማለት ኢትዮጵያውኛ ያለመሆኑን እንዲያውቁት ነው።

የዝነኛው የዊንስተን ቸርችል አባት አባታቸው የሞቱበት ቀን መታሰቢያው ሲከበር ሰኔ 24 ቀን 1895 ዓ.ም ሞቱ ዊኒስተን ቸርችል ደግሞ የአባታቸው ሙት ዓመት ሰባኛው ዓመት ሲከበር በዘጠና ደቂቃዎች ቆየት ብለው በ1965 ዓ.ም ሞቱ።

የኮንጎ ሰዎች አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ መሪር ኅዘናቸውን የሚገልጹት በራሳቸው በመቆም ነው።

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተሠርቶ የነበረው ሽጉጥ ጥይት የሚተኩስና ከጫፉ ላይ መጥረቢያ የነበረ ነበር።

ኢሶቤል ሲንክለር ልጃቸው የእስኮትላንድ ንጉሥ እንዲሆን አስበው ለዙፋኑ ተቀናቃኝ የሆኑትን የሱዘርላንድ መሥፍን ከነሚስታቸው ከነልጃቸው ለግብዣ ጠርተው መርዝ ሰጧቸው መሥፍኑና ሚስታቸው መርዙን ጠጥተው ሲሞቱ ልጅዬው ግን አመለጠ፤ ኢሶቤል እንዲነግስ የጓጉለት ልጅ በስህተት መርዙን ጠጥቶ ከዚያው ከእናቱ ፊት ሞተ።

በኦሃዮ ውጽት በሰሜን ካንቶን የሚኖረው አቶ ጆሴፍ አውሬሊዮ የሆድ ዕቃዎቹ ማለት፤ ልቡ፤ ጨጓራው፤ ትርፍ አንጀቱ፤ እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ

በተቃራኒ ሁሉ በተቃራኒ ሥፍራ የተፈጠሩ ናቸው፤ በሌላ ሰው በቀኝ በኩል የሚገኙት የሆድ ዕቃዎች በጆሴፍ ሆድ ውስጥ ግን በስተ ግራ ይገኛሉ ማለት ነው።

በአፍሪካ ውስጥ የኢቱሪ ባላባት የነበሩት ሡልጣን ማዳንግባ በበዓላት ጊዜ ለክብራቸው መታወቂያ የሰላ ጭራ ከኋላቸው ያስራሉ፤ ዙፋናቸው የሆነው ብርጩማ ከሣር በተሰፋ እንቅብ ላይ ይደረግና ሡልጣኑ ከዚያ ላይ ይቀመጣሉ፤ የትም ሲሄዱ ብርጩማቸው እንቅብ ላይ እንደተደረገ አብሮአቸው ይጓዛል።

በኖርዌይ ውስጥ ግራን በተባለ መንደር ጎን ለጎን የተሰሩ ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች አሉ ሁለቱን ቤተ ክርስቲያኖች ያሠሩት ሁለት እህትማማቾች ናቸው፤ ቤተ ክርስቲያኖች ተለያይተው የተሠሩበት ምክንያት እህትማማቾቹ ተጣልተው አንቺ በገባሽበት ጣሪያ ሥር እኔ አልገባም ብለው ስለተማማሉ ነው።

በሶሪያ ውስጥ በደማስቆ የአገሬው ሰዎች አምነው የሚናገሩት የአቤል መቃብር አለ፤ አቤል የመጽሐፍ ቅዱስም ሆኦን በቁርአን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የሞተው የአዳም ልጅ ነው።

በቱርክ ውስጥ በኢስታንቡል ነዋሪ የነበሩት አቶ አህመድ ሕይወት ያለውን እባብ በመዋጥ ትርኢት ያሳዩ ነበር።

በቪየና ነዋሪ የነበረው ዲሜትሪ ዲያማንቲዲ አራት ታላላቅ ተራራዎችን በመውጣቱ የተደነቀ ሰው ነበር፤ የወጣቸው ተራራዎች 6800 ጫማ ርዝመት ያለውን ቸበርግን፤ 6600 ጫማ ከፍታ ያእልውን ራክስን፤ 6200 ጫማ ከፍታ ያለውን ቬሽንና 6250 ጫማ ከፍታ ቻልፔ የተባሉትን ተራራዎች ወጥቷል። ዝነኛ ለመሆን የበቃት እነዚህን ሁሉ ተራራዎች በሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ውስጥ በመውጣቱ ነው።

የስፓኙ ኮርማ ታጋይ ጁልዮ አፓሪቾ ከኮርማ ጋር በሚታገልበት ጊዜ ጉብዝናውን ለማሳየት የኮርማውን ቀንድ በጥርሱ እየያዘ ይታገል ነበር።

በአዲሲቱ ቀለዶኒያ ያሉ ተማሪዎች በየቀኑ ተማሪ ቤት ሲሔዱና ሲመለሱ ወንዝ የሚሻገሩ ራሳቸው በሚሰሩት ጀልባ ነው።

በፈረንሳይ አገር በቱሲሊ ያለው በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሠራው ቤተ ክርስቲያን ስገነቱ ከወገቡ ላይ አርባ ሳ. ሜ ከጊዜ ብዛት ዘሟል።

የስፔይን ገዥ የነበሩት ታላቁ ማንሱር ከክርስቲያኖች ጋር 56 ጦርነቶች ተዋግተዋል፤ በሚዘምቱበት ጊዜ አንዲት ትንሽ ሳጥን ይዘው ይዘምታሉ፤ ያቺም ሳጥን ጦርነት የገጠሙበትን ሜዳ አፈር እየዘገኑ የሚያጠራቅቡባት ነች፤ እኚህ ሰው በ1004 ዓ.ም ሞተች ሲቀበሩ ያቺ አፈር የያዘች ሳጥን አብራቸው ተቀበረች።

ባካሃን የጂንግስ ፈረሰኞች እጅግ በጣም የራቁ ጉዞዎችን በፈረስ ግልቢያ በመጓዝ ተወዳዳሪ የሌላቸው ናቸው ጋላቢዎቹ ስድስት ፈረሶች ይይዙና በአንዱ ላይ ተቀምጠው እየጋለቡ ሌሎቹን አምስቱን ይስባሉ፤ የተቀመጡበት ፈረስ ገና ሊደክመው ሲል እሱን ይለውጡና በሌላው ይጋቡና ያን ደግሞ ይስባሉ። በዚህ ዓይነት አለዋወጥ ፈረሶቻቸውን ሳያደክሙ በጣም ረጅም የሆነ ጉዞ ይጓዛሉ።

የሚቺንጋ ፒንውድ ወደ ኦንታናጎን ሪቨር ግንዲላ የሚያመላልሱ ፈረሶች ዘጠኝ መኪና የሚጭነውን ሁለቱ ፈረሶች በሚጎትቱት ጋሪ ላይ የሚጫነው ግንዲላ 144 ቶንስ ክብደት ያለው ነው።

በአፍሪካ ውስጥ ካላንጋስ የሚኖሩ ሰዎች የዳቦ መጋገሪያ ምድጃቸውን የሚሠሩት የሰው ምስል አስመስለው ነው፤ ይህንንም የሚያደርጉበት ምክንያት ምድጃን ለፈለሰፈው ሰው መታሰቢያ እንዲሆን እያሉ ነው።

በስዊዘርላንድ ውስጥ ያለው የሶሜሪ ቤተ ክርስቲያን ለአንድ መቶ ዓመታት ጊዜ በየሳምንቱ እሑድ እሑድ ለካቶሊካውያንና ለፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች በሩን እኩል በመከፈት ለሁለቱም እማኒያን ወገኖች እኩል ያገለግል ነበር።

ኩክ የሚባል እንግሊዛዊ እንስሳ ገሪ ሁለት ዝሆኖችን ተቀምጠው እንዲበሉ አሰልጥኗቸው ስለ ነበር ዝሆኖቹ ምግብ ከጠረጴዛ ላይ ሲደረግላቸው በርከክ በለው በሹካ ምግባቸውን ይበሉ ነበር።

የሞንታክ ንጉሥ ልጅ የነበሩት እስቴቨን ፋሮህ ከብሮክላይን እስከ ሞንታክ ድረስ ያለውን 224 ቀን በእግራቸው ተጉዘው ጨርሰዋል።

የእግር ጉዞ ነገር ከተነሣ የሳሚንም ልንገርዎት፤ ሳሚ ፍልሰን በአሜሪካ አገር ባኦሃዮ ውስጥ በምትገኝ ፍሪፖርት በተባለች ከተማ ይኖር ነበር፤ ከፍሪፖርት ተነስቶ እስከ ቄሊንግ ድረስ ያለውን መንገድ በደርሶ መልስ ከፈረስ ጋር እሽቀዳደማለሁ ብሎ ተወራርዶ ጉዞ ጀመሩ፤ ፈረሱም ሆነ ዊሊ የሚጓዙት በእርምጃ እንጂ በሩጫ አልነበረም፤ ጧት የተጀመረው ጉዞ ደርሶ መልሱ ማታ ሲያልቅ ዊሊ ፈረሱን በሁለት ኪሎ ሜትር ተኩል ቀድሞት ገባ፤ ጠቅላላው የጉዞው ርዝመት 128 ኪሎ ሜትር ነበር።

ፈረንጅ ፖፕኮርን የሚሉት ሲቆላ ፍንድስድስ የሚለው በቆሎ ሲቆላ በጥሬነቱ ጊዜ ከሚያዘው ቦታ 27 ጊዜ ብልጫ ያመጣል።

በቦርኒዮ ውስጥ ያሉ የዲያክ ሰዎች ኳስ ሲጫወቱ ኳስዋን የሚመቷት በውስጥ እግራቸው ነው።

በ1897 ዓ.ም ተወልዶ በ1928 ዓ.ም የሞተው የታወቀው የተራራ ወጪዎች መሪ ኤልያስ ኮማን በ31 ዓመት ውስጥ 11.253 ርዝማኔ ያለውን በኦሪጎን የሚገኘውን ሁድ የሚባለው ተራራ 586 ጊዜ ወጥቶታል።

በጀርመን አገር በጉታከ የሚኖሩ ሴቶች የሚያደርጉት ባርኔጣ ከላዩ ላይ ትልልቅ ፍሬ እምስሎ የሚሠራ ሱፍ ይደረግበታል፤ የዚህ የፍሬ መሳዩ ሱፍ መከፈያ ቀይ ሐር ወይም ጨርቅ የሆነ እንደሆነ ባል የለኝም ማለት ሲሆን ጥቁር እይሆነ እንደሆነ ባል አለኝ ማለት ነው።

በሕንድ አገር በሰንደርባንስ የሚገኙ ድመቶች ከባሕር ውስጥ አሣ በእጃቸው ይዘው አውጥተው መብላት ይችላሉ።

በስፔይን ውስጥ አሬኒስ ደ ማር በተባለው ቀበሌ የሚኖሩ ልጆች በየዓመቱ ታኅሣ 8 ቀን በፒፓ ትንባሆ እያጨሱ በመንገድ ላይ ይዘዋወራሉ።

በፈረንሳይ አገር ያለው የኮንቲኝ ቤተ ክርስቲያን ሰኔ 21 ቀን 1789 ዓ.ም በመብረቅ ከፉኛ ተመታ፤ የቤተ ክርስቲያኑ ሰገነትም ተደርምሶ ጣሪያውን ቀድዶ ከውስጥ ወደቀ ይህ ሁሉ ሲሆን ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ለጸሎት ቆመው የነበሩት 153 ሰዎች ምንም ዓይነት ጉዳት አልደረሰባቸውም።

በ1805 ዓ.ም ተወልዶ በ1875 ዓ.ም የሞተው የሁንጋሪያ የስፖርት ሰው በቡዳፔስት ከተማ ካለው ነጭዋ ዳኪዬ ከተባለው ሆቴል ለዳንስ ጨዋታ ሲገባ 2ኛ ፎቅ ድረስ በፈረሱ ተቀምጦ ወጥቷል።

በኒውጊኒያ በማፕሪክ የሚኖሩ ገበሬዎች ከአመረቱት እህል አይበሉም ያመረቱትን እህል ገበያ ወስደው ከሌላ መሰል ገበሬ ጋር ይለዋወጡታል።

በፍሬሊን የሚኖሩት ፈረንሳዊው ጁልየስ ዳሞትን 12 ጫማ ከሁለት ኢንች ርዝማኔ ያለው ጢም አላቸው።

በ1626 ዓ.ም ተወልደው በ1684 ዓ.ም የሞቱት ፈረንሳዊ ባለ ቅኔ ጄን ባር ትሌሜ 6000 መስመር የሆኑ የቅኔ ግጥሞችን ጽፈዋል፤ እነዚህን ግጥሞች ሲጽፉ በቀን አንድ መስመር ብቻ ይጽፉ ስለ ነበር ጠቅላላን ግጥም ጽፈው የጨረሱት በ16 ዓእምት ጊዜ ውስጥ ነው።

በፖርቱጋል ውስጥ አልጋርቬ በሚባል ሥፍራ ያለው የቅዱስ ፍራንሲስ ቤተ ክርስቲያን የየግድግዳዎቹ ማጠፊያ በሙሉ የተሠሩት በሰው ጭንቅላትና በሰው የቅልጥም አጥንት ነው።

በአፍሪካ የባንን ጎሣ ሰዎች የሚሠሩት ቤት በሩ በጣም አነስተኛ ነው ማንም ሰው ሲገባም ሆነ ሲወጣ ተኝቶ በደረቱ እየተሳበ ነው።

በኒጀሪያ ያሉ ኩሊዎች ዕቃ ተሸክመው በሚሄዱበት ጊዜ ለማረፍ ሲፈልጉ የተሸከሙት ዕቃ ከራሳቸው ላይ ብድግ አድርገው ይቆያሉ ከዚያም እንደ ገና በራሳቸው ላይ አድርገው ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ።

በእስፔይን ውስጥ በኢቪዛ የሚኖሩ ሴቶች ባላቸው ሲሞት ለሰባት ዓመት ሌላ ባል ሳያገቡ ጥቁር ልብስ እንደለበሱ ይቆያሉ። ይህ ባህል በኛም አገር ነበር።

በጀርመን አገር በሱስ ይኖሩ የነበሩት አቶ ጆሴፍ ፓግለር በሰማንያ አራት ዓመት ዕድሜያቸው ሲሞቱ ከሚያመርቱት የወይን እርሻቸው ብቻ የተጠመቀ የወይንጠጅ ሲጠቱ ኖረዋል፤ እኚህ ሰው የጠጡት ወይን ጠጅ በጠቅላላው ሲታሰብ 43.420 ሊትር ነው።

በሜክሲኮ የሚገኝ ሰይፋማው ባለጭራ (ስዎርድ ቴይል) የሚሉት አሣ አለ፤ የዚህ አሣ ሴት እንቁላል የምትፈልፍለው በሦስት ዓመት ዕድሜዋ ነው፤ እንቁላልዋ ተፈልፍሎ የመጀመሪያ ልጆችዋን ካየች በኋላ ጾታዋ ይለወጥና ወንድ ትሆናለች።

በጀርመን አገር በሬቸንባክ አቅራቢያ በጎይልዝ ሸለቆ ውስጥ በእርዝማኔው እውቅ የሆነ ከሸክላ የተሠራ የባቡር ሐዲድ ድልድይ አለ፤ ይህ ድልድይ 2275 ጫማ ርዝማኔ ሲኖረው ከፍታው ደግሞ 307 ጫማ ነው፤ በሸክላ ብቻ የተሠራ ድልድይ ከተሠራ 120 ዓመት ሲሆነው በዚህ ዕድሜው ሳይጠገን እንደተሠራበት ጊዜ ሆኖ ይኖራል።

በእስፔይን ውስጥ በቶሮ የሚገኙ ሴቶች ባላቸው ሲሞት በኀዘን ይቆዩና እንደገና ባል ለማግባት ሲፈልጉ ጠጉራቸውን ከነጭ ክር ጋር በመደባለቅ ይጎነጉናሉ ቁልቁል ይለቁታል።

በ1896 በእንግሊዝ አገር አንዲት 3 እግሮች ያሉዋት ሞተር ብስክሌት ተሠርታ ነበር፤ ይቺ ሞተር ብስክሌት ስምንት ሰዎችን ትይዛለች ከብደቷ አንድ ሺ ኪሎ ሲሆን ርዝመቷ 17 ጫማ ነው፤ የኋላ እግርዋ ርዝመት ደግሞ 11 ጫማ ዲያሜትር ነበር።

በሕንድ አገር በአጅሜሬ ከተማ ዝንብ መግደል እንደ ኃጢአት ይቆጠራል።

አቶ ጃሚ ሁሉት እጆቹ ተቆርጠዋል፤ በእነዚሁ ቆራጦ እጆቹ መርከበኛ ነበር፤ በቆራጣ እጆቹ ላይ በሚያደርገው ብረት ማንኛውንም ነገር በመያዝ ማንኛውንም ሥራ መሥራት ይችላል፤ ጀልባ ይነዳል፤ አሣ ያጠምዳል ዕቃ ጀልባው ላይ ይጭናል፤ መልሶም ያወርዳል፤ ጀልባው ላይ ያለውን የጥንት የጀልባ ላይ መድፍ ይተኩሳል አቶ ጂሚ በ1880 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

በ1824 ዓ.ም ተወልደው በ1896 ዓ.ም የሞቱት የታወቁት የአውስትራሊያ ሙዚቃ ደራሲ አቶ አንቶን ብሩክ ነር ለሃያ ስድስት ዓመት ሙሉ በየቀኑ መጽሐፍ በማንበብ ይውሉ ነበር፤ ይህም ሃያ ስድስት ዓመት

ሙሉ ሞት እስኪለያቸው ያነቡት የነበረ ሁለት መጽሐፍትን ብቻ ነበር፤ እነሱም መጽሕፍ ቅዱስና የንጉሥ ማክሚላን ታሪክ ናቸው።

በአፍሪካ ውስጥ መሎይ ማሳ የሚባለው ጎሳ ሴቶች በክንዳቸው ላይ ልዩ ክትባት እንደንቅሳት አድርገው ይከተባሉ፤ ይህም ክትባት ማንኛውንም በሽታ ይከላከላል ብለው ስለሚያምንኑ ከዘመናዊ ሕክምና ጋር አይዋደዱም።

ፈረንጆች ፊዘር ስታር የሚሉት የአሳ ዘር የባሕር ውስጥ አሣ ይመስላ፤ ይህ አሣ የሚዋኘው በአሥር ዘርፍ ወይም የሣር ቅርንጫፍ በሚመስሉ እግሮቹ ነው። ለመሆኑ እንዲህ ያለ የዓሣ ዘር አይተው ያውቃሉ?

የእኮትሽ ማኅበራዊ ኑሮ መምሪ የነበሩት አቶ ጄምስ ታይት 70 ዓመት ሙሉ በአንዲት ጠረጴዛ ላይ ከእናታቸው ጋር ይበሉ ነበር፤ እናትዮዋ ከሞቱ በኋላ 25 ዓመት ሙሉ የእናታቸውን ሰሃን በዚያ ጠረጴዛ ላይ ሳያደርጉ ምግባቸውን አይበሉም ነበር።

በሮዴስያ ውስጥ ሾና ሚባለው ጎሳ ሴቶች አባታቸውም ሆነ ባላቸው በሚቆምበት ጊዜ ቁጣውን የሚሰሙት ወይም ይቅርታ የሚጠይቁት በጉልበታቸው ተንበርክከው ነው።

በፈረንሳይ አገር በሪዮም በያመቱ ትልቅ ድብልብል የአበባ ጉንጉን ሁለት ሰዎች ተሸክመው በመንገድ ላይ ይዞራሉ፤ ይህ ባህል የመጣው በ1160 ዓመት በፊት በዚያች ከተማ መንገዶች ሁለት የከተማው ነዋሪዎች 737 ጫማ ርዝማኔ ያለው የተድበለበለ ሻማ ይዘው ይዞሩ ስለ ነበረ ያን ባህል ይዘው ነው።

በገመድ ላይ በመጓዝና ዝናው የገነነለት ብሎንዲን አንድ አንበሳ የሚገፋ ጋሪ ላይ አድርጎ በኒያግራ ፏፏቴ ላይ በተዘረጋው ገመድ አንበሳ የያዘ ጋሪውን እየገፋ ተሻግሯል።

በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጠመንጃና መጥረቢያ የሆነ ሁለቱንም አገልግሎት የሚሰጥ መሣሪያ ተሠርቶ ነበር።

በሕንድና ባንዳንድ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት የነበሩ የእንግሊዝ ወታደሮች ትግል በመታገል የሚወዳደሩት በፈረስ ላይ ተቀምጠው ነበር።

የጓቴማላ ሕንዶች የሠሩት አንድ ሐውልት አለ፤ ሐውልቱ የሃይማኖት ሐውልት ሲሆን የተሠራው በእህል ዱቄት ሲሆን የተደረገለት ጠጉር ግን የሰው ጠጉር ነው።

በ1739 ዓ.ም ተወልዶ በ1814 ዓ.ም የሞተው አንቶኒዮ ሞሬሊ የታወቀው የኦፔራ ዘፋኝ ጠጉሩ ፍፁም ነጭ ነበር፤ በኅዳር 1755 ዓ.ም ትልቅ የመሬት መንቀጥቀጥ ተነስቶ አንድ ቤተ ክርስቲያን ሲያፈራርስ አንቶኒዮ በፍራሹ ውስጥ ተቀብሮ ቆየ፤ በኋላ ተፈልጎ ሲወጣ ጠጉር ፍፁም ነጭ ሆኖ ተገኘ።

የእንግሊዟ ንግሥት አንበአሽሪግ መናፈሻ ውስጥ አሥራ ሰባት ዛፎችን በመደዳው ራሳቸው ተክለዋል፤ እነዚህንም ዛፎች የተከሉበት ምክንያት በሕፃንነታቸው ለሞቱባቸው አሥራ ሰባት ልጆቻቸው መታሰቢያ እንዲሆን ብለው ነው።

በኔፓል ውስጥ ባሉ አንዳንድ ሸለቆዎች ገበሪዎች እርሻቸውን የሚያዘጋጁት በእጅ ቁፋሮ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም በበሬ ማረስ በሕግ የተከለከለ በመሆኑ ነው።

በአሜሪካ ውስጥ በካሊፎርኒያ ባለው አታምብራ በተባለው ቦታ የሚኖሩት አቶ አንጀሎ ቬሎቺ በእርሻቸው ውስጥ 20 ጫማ ርዝማኔና 27 ጫማ ስፋት ያለው አንድ ቲማቲም አብቅለዋል።

በ1864 ዓ.ም ተወልደው 1938 ዓ.ም የሞቱት በኡታህ ይኖሩ የነበሩት አቶ አምት ዋርነር ከብት በመዝረፍ ባንድ ሰብረው ገንዘብ በመውሰድ ሰው በመግደል ወንጀል ተከሰው በ3 ዓመት እሥራት እንዲቀጡ ተፈረደባቸው። የእሥራቱን ዘመን ጨርሰው ከወጡ በኋላ ፖሊስ፤ ዳኛ ሰላይና የጎበዝ አለቃ በመሆን በታማኝነት ሰላሳ ስምንት ዓመት አገልግለው ሞቱ።

ከ1700 ዓመታት ቻይናውያን የአቅጣቻ መለያ ኮምፓስ የነበራቸው ይህ ቻይናውያን የነበራቸው ኮምፓስ አንድ ክብረት የተሠራ የሰው ምስል በሚዞር ዕቃ ላይ ቆሞ ከአቅጣጫው የሚየመለከት ነው። የሐውልቱ ሰውዬ እጅ ሁልጊዜ የሚያመለክተው ወደ ደቡብ ነው። የቻይና ነገሥታት ከ235 ዓ.ም ጀምረው ኮምፓሱን በጋሪያቸው ላይ በማድረግ ይጠቀሙበት ነበር።

ይሄ አበባ በዓለም ላይ የሚበቅለው በአንድ ቦታ ብቻ ነው። በጃቫ ውስጥ ፓንጌራጂ በተባለው ቦታ ይበቅላል። የጃቫ ሰዎች አደጋ ነጋሪው አበባ ይሉታል። ምክንያቱም ይህ አበባ በበቀለበት ቦታ እሳተ ጎመራ ይነሳልና ነው። የጃቫ ሰዎች ይሄ አበባ የሚበቅልበትን ቦታ እየዞሩ ይፈልጋሉ። አበባውን ካገኙ ጓዝ ጉዝጓዛቸውን ጠቅልለው ከዚያ ሠፈር ይጠፋሉ።

በ1811 ዓ.ም ተወልደው በ1878 የሞቱት ሰር ጊልበርት ስኮት የተከበሩ መሐንዲስ ነበሩ። እኚህ እንግሊዛዊ 33 ካቲድራሎችና ገዳሞች 26 ተማሪ ቤቶች 474 ቤተ ክርስቲያኖች 23 ድልድዮች 16 ኮሌጆች 58 ሐውልቶች 27 የመኖሪያ ቤቶች በዕድሜያቸው ሠርተው አስረክበዋል።

አርመኖች በመቃብር ቦታ ላይ ሠርተው የሚያስቀምጡት የበግ ምስል ነው። የበጉን ምሥል ትርጉም ሲናገሩም የክርስቶስ ምሳሌ ነው ይላሉ።

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን በሚሠሩበት ጊዜ ለቤተ ክርስቲያኑ መሥሪያ የሚቆረጠው ዛፍ ወደ ፀሐይ መጥለቂያ እንዲወድቅ ያደርጉታል፤ የቤተ ክርስቲያኑ ዋና በር ደግሞ ወደ ፀሐይ መውጫ ይሆናል።

በእንግሊዝ አገር ፌን በሚባለው አምባ ይኖር የነበረው አቶ ስሞከር ኢተርድስ መሸታ ቤት ሲሄድ ለማዳ ዶሮውን እየያዘ ነበር፤ በመጠጥ ቤትም ዶሮው ከጌታቸው ጋር እስቲጠግብ ድረስ ጠጥቶ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ።

በ1637 ዓ.ም ተወልደው በ1706 ዓ.ም የሞቱት ቄስ ሰለሞን ብሬንዎልድ በስዊዘርላንድ ውስጥ ስትምሪም በሚባእልው ሥፍራ መቃብራቸው አለ በመቃብሩ ላይ ያለው ጽሑፍ «በ3 አብያተ ክርስቲያናት ያገለግሉ ነበር 3 ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አለቃ ሆነዋል 3 ጊዜ ሚስት አግብተዋል ከመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ሚስቶቻቸው ሦስት 3 ልጆች አስወልደዋል 3 ወንዶች ልጆች ሲኖሩዋቸው 3 ሴቶች ልጆች አሏቸው ዕድሜያቸው 3 ጊዜ 23 ሲሆን ሞተው በ3ሩ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ በዚች ሥፍራ ተቀብረው የዘለዓለም ረፍት አገኙ» ይላል።


በ19ኛው መቶ ክልፈ ዘመን ቻይናውያን በሸንበቆ ይገበያዩ ነበር።

በጀርመን አገር በሊንዳው ውስጥ አቶ አስዋልድ ክሮል በሰው ገዳይነት ወንጀል ተከሶ የሞት ፍርድ ተፈረደበትና ተገደለ፤ የአስዋ ድል ጣጣ ካለቀበት በኋላ አስዋልድ የተከሰሰበት የወንጀለኛ ክስ የሀሰት መሆኑ ተረጋገጠና አስዋልድ ከወንጀሉ ነፃ ሆነ። ቢሆንም አስዋልድ በፍርድ ተገድሎ ከተቀበረ ቆይቶ ነበርና የአገሩ ዳኞች የአስዋልድን አጽም ከመቃብር አውጥተው በጥሩ እንዲያያዝ ካስደረጉ በኋላ በፍርድ ቤቱ ውስጥ ዳኛው ከሚያስችሉበት ጠረጴዛ ጎን እንዲቆም አደረጉ፤ ምክንያቱም ዳኞች በፍርዳቸው እንዲጠነቀቁ፤ ጠበቆች በሀሰት ክስ እንዳይሟገቱና ምሥክሮችም በሀሰት መስክረው ሰውን እንዳይስገድሉ ማስጠንቀቂያና ትምህርት እንዲሆናቸው ተብሎ ነው፤ የአስዋልድ አጽም በዚያ ቦታ አምሳ ዓመት ሙሉ ከቆመ በኋላ ተነስቷል።

በቲቤት ውስጥ በላማ ያሉ አስማተኞች ወይም ጠንቋዮች ፊታቸውን በጠጉራቸው ሹሩባ ይሸፍናሉ፤ በልብሳቸው ላይ ደርበው የሚለብሱት ሸርጥ ቢጤ ልብስ ደግሞ በሰው አጥንት ተደባልቆ እይሚሠራ ነው፤ እንዲህ የሚለብሱት ከአደባባይ ሲወጡ ወይም ከእንግዳ ጋር ሲገናኙ ነው።

በቼኮስሎቫኪያ ውስጥ በፕራግ ከተማ ባለው ክሌሜንቲኑም ኮሌጅ ውስጥ ባለ አንድ አዳራሽ አሳሳች የሆነ አንድ ምስል አለ፤ ምስሉ እንዲህ እንደሚያዩት ከፍርግፍርግ ብረት የተሰራ በር ይመስላል፤ ግን ምንም ነገር የሌለው ፍጹም ጠፍጣፋ የሆነ ምስል ነው።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY



# ስለደራሲው በጥቂቱ

ጳውሎስ ኞኞ ኅዳር 11 ቀን 1926 ዓ.ም ቁልቢ አካባቢ ተወልደው ድሬዳዋ ከተማ አደጉ። በጣሊያን ወረራ ምክንያት ትምህርታቸውን ከ4ኛ ክፍል በላይ ለመቀጠል አልቻሉም ነበር። ብልህ አዕምሮና የፈጠራ ችሎታ የነበራቸው ሰው ስለነበሩ፤ በልጅነታችው የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ጣሊያንን ሲገድሉ ወይንም ሲማርኩ ሥዕል በመሣል ያሳዩ ነበር። ጳውሎስ ካላቸው የጽሑፍ ጥማት የተነሳ የ«ድምጽ ጋዜጣ» አዘጋጅ በመሆን የብዕር ድምጻቸውን ያሰሙ ነበር። ጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሠርተዋል። በተለይ «አንድ ጥያቄ አለኝ» በሚለው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አምዳቸው ላይ ብዙ ታዋቂነትን አግኝተዋል። አቶ ጳውሎስ ኞኞ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ዕድገት የነበራቸውን ተሰጥኦ በአግባቡ በሥራ ላይ ያዋሉ እውቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበሩ። እኚህ ታዋቂ ሰው በተወለዱ በ58 ዓመታቸው አረፉ።

ከጋዜጠኝነታቸው ጎን ለጎን በድርሰትና በታሪክ ጸሐፊነታቸውም 19 መጻሕፍት የታተመላቸው ሲሆን ሁለቱ ካረፉ በኋላ የታተሙ ናቸ። ለሕዝብ የሚሆኑ ዕውቀት ተኮር መጻሕፍት በማቅረብ ይታወቁ የነበሩት አቶ ጳውሎስ ኞኞ ካረፉ ከ፳ ዓመታት በኋላ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በሀገር ውስጥ የተጻጻፏቸውንና ወደውጭ አገር የላኳቸውን ደብዳቤዎች የሚያሳዩት ሁለት መጻሕፍት በአስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት አማካይነት ታትመዋል።

## የደራሲው ሥራዎች

1. ከሴቶቹ አምባ (**ልብወለድ**)
2. የአራዳው ታደሰ (**ልብወለድ**)
3. የጌታቸው ሚስቶች (**ልብወለድ**)
4. ድብልቅልቅ (**ልብወለድ**)

5. የኔዎቹ ገረዶች (**ልብወለድ**)
6. አጤ ቴዎድሮስ (**ታሪክ**)
7. አጤ ምኒልክ (**ታሪክ**)
8. የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ጦርነት (**ታሪክ**)
9. አስደናቂ ታሪኮች (**ታሪክ**)
10. እውቀት (**ፍልስፍና**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY